# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪው መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ቢሮትምህርት ቢሮ

የግብረ ገብ ትምህርት የተማሪው መጽሐፍ ስድስተኛ ክፍል

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪው መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ትምህርት ቢሮ

# መጽሐፉን በጥንቃቄ ይያዙ




ይህ መማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው እንዳይጠፋና እንዳይጐዳ ጥንቃቄ ያድርጉ ለመጽሐፉ ጥንቃቄ ይረዳችሁ ዘንድ እነዚህን አስር ነጥቦች ተግብሩ

1. መጽሐፉን በጋዜጣ ወይም በመጽሔት ሽፍኑ
2. መጽሐፉን ንፁህና ደረቅ ቦታ አስቀምጡ
3. መጽሐፉን ሲጠቀሙ እጃችሁ ንፁህ መሆኑን አረጋግጡ
4. በመጽሐፉ ሽፋንም ሆነ በውስጥ ገጽ ምንም ዓይነት ነገር እንዳትጽፉ
5. የመጽሐፉን ገጽ ምልክት ለማድረግ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርቶን ተጠቀሙ
6. ስዕልም ሆነ ገጽ ቆርጣችህ አታውጡ
7. የተቀደዱ ገፆችን ማጣበቂያ በመጠቀም ጠግኑ
8. መጽሐፉን ቦርሳችሁ ውስጥ በጥንቃቄ አስገቡ
9. መጽሐፉን ለተማሪ ስታውሱ ጥንቃቄ አድርጉ
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀሙ በጀርባው አስቀምጡ ለጊዜው የተወሰነውን ገጽ ክፈቱና በጥንቃቄ ተጠቀሙ

እነዚህ የመጽሐፉን ሽፋን ደህንነት ይጠብቃሉ

# የግብረ ገብ ትምህርት

## የተማሪ መፅሐፍ

## 6ኛ ክፍል


አዘጋጆች፡- እያሱ ገ/ክርስቶስ (M.A)

ተመስገን ኤሊያስ (M.A)

አርታኢዎች፡- አብዮት ታከለ (M.A) የይዘት አርታኢ

ግርማ ገብሬ (PHD) የቋንቋ አርታኢ

መሰረት አሰፋ (PH.D) የስርዓተ ትምህርት አርታኢ

ሰዓሊ፡- ኤልያስ ወንድምአገኝ (M.Sc.)

ሌይአውት ዲዛይነር፡- ኃይለጊዮርጊስ ተመስገን ((አስማምቶ የሰራው)

ዮሐነስ ቢያድግልኝ (M.Sc)

ተርጓሚዎች፡- ዮናስ እንግዳ (M.A)

ሙሉጌታ ድረስ (M.A)

አርታኢና ገምጋሚ፡- ገበየሁ አስፋው (M.A)

አስተባባሪ፡- ጌታቸው ታለማ (M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የመጀመሪያው ዕትም በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ፣ በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ለፍትሃዊነት፣ በአለም ባንክ፣በእንግሊዝ አለማቀፍ ልማት ክፍል( አሁን የውጭ የጋራ ሃብትና ልማት ጋር የተቀናጀ)፣የፊንላንድ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ የኖርዌይ ንጉሳዊ ቤተሰብ አንባሲ፣በተባበሩት መንግስታት የህፃናት ገንዘብ ተራድዖ፣ በአለማቀፉ የትምህርት ትብብር፣ በዴንማርክ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በበርካታ የገንዘብ ለጋሾች ድጋፍ የተዘጋጀ ነው፡፡

© በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ ትምህርት

ሚኒስቴር፡፡ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የፀሀፊዉም የሞራል መብት የተጠበቀ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የቅጅና ተዛማጅ መብቶች እንደተገለፀው ይህን መፅሐፍ ክ ትምህርት ሚኒስቴር የፅሁፍ ፈቃድ ዉጭ የይዘቱን ክፍል እንደገና ማባዛት፣በማናቸውም የማስተላለፊ ዘዴዎች ማለትም በኤሌክትሮኒክስ፣ሜካኒካል፣ማግኔታዊ፣ፎቶ ኮፒ፣በድምፅ ቀረፃ ወይም በሌሎች ዘዴዎች ማባዛት የተከለከለ ነው፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር በዚህ ስራ ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለተሳተፉ ግልሰቦች፣ቡድኖችና ለሌሎች አካላት ምስጋና ማቅረብ ይወዳል፡፡ በተለይም ከአዲስ አበባ፣ባህር ዳርና ጂማ ዩኒቨርሲዎች ጋር በመተባበር ለዚህ መፅሐፍ ዝግጂት ትልቅ አስተዋፅዖ ላበረከተው ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ሚኒስቴር ልዩ ምስጋና ማቅረብ ይወዳል፡፡

የቅጅ መብቶች የህትመቱ ቁሳቁሶች ን መጠቀም የሚቻለው በባለቤቶች ፈቃድ መሆን አለበት፡፡ ቅጅና ተዛማጅ መብቶች ባለቤት ሆነው የርስዎ የስራ ዉጠት በአግባቡ ካለተገለፀ እባክዎ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱን ያናግሩ፡፡

አድራሻችን ዋናዉ መስሪያ ቤት ፣ አራት ኪሎ ( የመ.ሳ.ቁ 1367) አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

ህትመት አሳታሚ**************

የመ.ሳ.ቁ **************

በትምህርት ሚኒስቴር የስምምነት ቁጥር ***

ትምህርትና ልማት ቁርኝት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው:: ለዚህም ነው ትምህርት ለኢትዮጵያ ልማትና ማህበራዊ ሽግግር ቁልፍ መሳሪያ ነው የሚባለዉ:: አሁን የምንኖርበት ፈጣንና ልዕላዊ አለም በያንዳንዱ ግለሰብ ላይ አዲስ እዉቀት፣ክህሎትና አመለካከት ይፈልጋል:: በዚህ የአላማ እይታም የስርዓተ ትምህርቱ ታቀደ ንድፍ ብቻም ሳይሆን ለሃገሪቱ ለዉጥ አስኳል መሆን አለበት::

ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ቀርፃ ትግበራ ከጀመረች ሶስት አስርት አመታትን አስቆጥራለች :: ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ሃገራችን በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በተደራሽነት ፣ ፍትሃዊነትና አስፈላጊነት አመርቂ ዉጤት አስመዝግባለች:: የትምህርት ጥራትን ለማሻሻልም ብርቱ ጥረት ተደርጓል፤ ጥረቱም የቀጠለ ነው::

ይህን እድገት ለማስቀጠል የትምህርት ሚኒስቴር በ2013ዓ፣ም አዲስ የስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል:: ማዕቀፉም ቅድመ አንደኛ ደረጃን፣ አንደኛ ደረጃን፣መካከለኛና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የክፍል ደረጃዎችንና የትምህርት አይነቶችን ይሸፍናል:: አላማ ያደረገዉም በትምህርትና ፖሊሲ ስልተና የተገለፁትን መርሆችን ማጠናከርና በስርዓተ ትምህርቱ ዝግጂት የምክር አገልግሎት መስጠት ነው::

በዚህም የሚጠቃለሉት የመምህሩ መምሪያና የተማሪዉ መማሪያ አሳታፊ የመማር ዘዴዎችንና ብቃትን መሰረት ያደረጉ ዘዴዎች ላይ እንዲዘጋጁ ነው::

በዚህ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት በ2010 ዓ.ም የተጠናዉ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ አስተያቶች እንደ መነሻ አገልግለዋል:: አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ይዘትን ከተማሪዎች እድሜ ጋር ያመጣጠነ፣እንደ አስፈላጊነቱ ሃገር በቀል እዉቀቶችን ያካተተ፣ቴክኖሎጂን ለመማርና ማስተማር ሂደቱ አጋዥ እንዲሆን ያደረገ፣የሙያ ትምህርት ይዘትን ያካተተ፣የተማሪዎችን ልዩ የመማር ፍላጎት ለማሳካት የግብረ ገብነት ትምህርትንና የሙያና ቴክኒክ ትምህርቶችን ያካተተ ነው::

በማንኛውም ሃገር አዲስ የትምህርት ማዕቀፍ ፣ በዋነኛነት የተማሪዉ መማሪያና የመምህሩ መምሪያ ለትምህርት ጥራት መሻሻል ዋነኛ መፍትሄ ናቸው:: ቀጣይ መሻሻያዎችም የሁሉንም ባለድርሻዎች ጥረት ይፈልጋል:: መምህሩም ሚና ከአስተማሪነት እስከ አነቃቂነት ፣ ከመሪ እስከ አመቻች በታም ተለዋዋጭ መሆን አለበት::ይህን ለማሳካት መምህራን በትምህርት ማዕቀፉ የተቀመጡትን ስልቶችና ስልጠናዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው::

መምህራን ይህን መመሪያ በአግባቡ በማንበብና የተሰጡ ተግባራትንና ስልቶችን ተግባር ላይ በማዋል ተማሪዎቻቸዉን መርዳት አለባቸዉ::

# መቅደም

የሰው ልጅ ምክኒያታዊ ፍጡር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህም ባህሪ የሰው ልጆችን ከሌሎች እንስሳት የሚለይና የሰው ልጆች ራሳቸውን በማሻሻል ወደ አለሙት ግብ ለመድረስ በሚያደርጉት ሂደት የሚገነባ ነው፡፡ ይህን ልዩ የሚያደርጋቸውን ባህሪ ለመገንባት የሰው ልጅ ድርጊት በምክንያት እንዲሁም በግብረ ገብ ዕሴቶች እና መርሆች የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ የሰው ልጆች ባህሪ በራሳቸው አስተሳሰብ እንጂ የሌሎችን አስተሳሰብ በመውሰድ (በመገልበጥ) የሚገነባ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሰው ልጆች ከሌሎች እንስሳት ልዩ የሚያደርጋቸው ምክኒያታዊነት እና ህሊና ስላላቸው ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ አዕምሮ ነው ወደ ባህሪ ግንባታ የሚያመራው፡፡

የሰው ልጅ ለተተኪው ትውልድ መመሪያ ስልጠና እና ትምህርት በመስጠት በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖር የሚያደርግ ብቸኛው ምክኒያታዊ ፍጡር ነው፡፡ የሰው ልጅ ባህሪና ችሎታ በተፈጥሮ የሚወረሱ ሳይሆን በትምህርት የሚገኙ ናቸው፡፡ የሰው ልጅ የመማር ችሎታው አይተኬ ነው፡፡ ይህ ባህሪ ያለሙትን ግብ ለማሳካት እና ቀጣይነት ያለው ግብረገባዊነትን ለመላበስ ይረዳቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የሰው ልጆች በማህበራዊ ግንኙነትና በማህበራዊ ስርዓቶች ስልጡን ቢሆኑም በበቂ ሁኔታ ግን ግብረ ገብ ሆነው አይታዩም፡፡ የሰው ልጅ መልካም ይሆን ዘንድ መማር አለበት የሚለው ድምዳሜ ሳይታለም የተፈታ እውነት ነው፡፡

ከፍ ያለ የግብረ ገብ ባህሪ በሂደት የምናገኘው እንጂ አብሮን የሚወለድ አይደለም፡፡ በሂደት ውስጥ ሊያገኙት ወይም ሊማሩት የገባል፡፡ እርግጥ ነው የሰው ልጆች የግብረ-ገባዊ ግዴታዎችን የመፈፀም አቅም አላቸው፡፡ በጥረት የሚገኝና በትምህርት የሚዳብር ነው፡፡ ከፍ ያለ የግብረ ገብ ልዕልና ላይ ለመድረስ በእያንዳንዱ የግብረ ገብ ባህሪት ላይ ተደጋጋሚ ልምምዶችን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰው ልጆች ማህበራዊ ፍጡር መሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ይህም በማያሻማ ሁኔታ ሰዎች ግብረ-ገባዊ ፍጡሮች መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በሌላ አገላለጽ ግብረገባዊነት ከሰው ልጆች መሰረታዊና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ጋር የተያያዘ ማህበራዊ ተግባር ነው፡፡ አለም ላይ ብቸኛው ሰው ብትሆን ግብረገባዊነት አይኖርም፡፡ ያለ ማህበራዊ ምህዳር የሰው ልጆች ሰብዓዊ ባህሪያትን መለላበስ የማይችሉ ሲሆን ሰብዓዊ ማህበረሰብ ማህበራዊ መሆን ከቻሉ ሰዋዊ ግለሰቦች ድምር ውጤት ውጭ ሊኖሩ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ገጽታዎች እርስ በርሳቸው ተመጋጋቢ ናቸው፡፡

በተጨማሪ ግብረገባዊነት ማለት እውነትን መሻትና በዚህ ውስብስብ ዓለም እንዴት አብሮ መኖር እንደሚቻል መረዳት ነው፡፡ ግብረ ገብነት አንዱ አይነት የማህበራዊ ቁጥጥር መንገድ ነው፡፡

ማንኛውም ማህበረሰብ ጤናማ ፣ ተገቢና የሚጠበቁ ባህሪያት ብሎ የሰየማቸው የራሱ የሆኑ ትርጉሞች አሉት፡፡በመሆኑም እነዚህ ተጠባቂ ባህሪያት ገዥ የማህበራዊ ህጎች ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን

ማህበረሰቡ በመግባባት እንዲኖር የሚያስችሉ የባህሪ መመሪያቸው ሆነው ያገለግላሉ። ማንኛውም ማህበረሰብ ህልውናውን ጠብቆ መቀጠል ካለበት ማህበራዊ ህጎቹንና ልማዶቹን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ አለበት። እርግጥ ነው ሰዎች ማህበራዊ ደንቦችን ካልተማሩ በስተቀር ተገቢ ሊሆኑ አይችሉም። በዚህ ሂደት ውስጥ ማህበረሰባዊነት ወጣቶች የህብረተሰቡን ደንብ እንዲያውቁት በማስተማርና መጣስ እንደሌለባቸው በማሳወቅ ጉልህ ሚና ይጫወታል። ሰዎች ማህበራዊ ህጎችን የሚማሩት በግብረ-ገባዊ አስገዳጅነት። በሌላ አባባል ሰዎች የማህበረሰባቸውን ደንቦች ሲማሩ በተመሳሳይ ለህጎቹ ታዛዥ የሚያደርጋቸውን የግብረ ገብ ግብዓቶችን በውስጣቸው ያሰርጻሉ። ይህ በህብረተሰቡ ልማዶች ወይም በአኗኗር ዘየ ውስጥ የተካተተ የዕለት ተዕለት ተግባር ነው። በአጭሩ የህብረተሰቡ የባህሪ መመሪያ ነው፡ ፡ ምን ማድረግ እንደለብንና እንደሌለብን የሚነግረን ስምምነት ነው።

ግብረገብነት አብዛኛው ሰው ከተከተላቸው አብዛኞቹን የሚገነቡ የህግ ስብስቦችን የያዘ ነው፡ ፡ ምንም እንኳ ህጐቹ ነፃነት ገዳቢ ቢሆኑም ሰዎች ሊያከብሯቸው ይገባል። ይህ እውነታ የሰዎችን ነፃነትና ደህንነት ያጠናክራል። በአጠቃላይ ግብረገብ የሚከተሉት አምስት ዓላማዎች አሉት፡-

1. ህብረተሳቡን ከመለያየት ይታደጋል።

2. የሰዎችን ስቃይ ይቀንሳል።

3. የሰው ልጅን ያበለጽጋል።

4. ፍትሀዊና አግባብነት ባለው መንገድ ግጭቶችን ለመፍታት ይረዳል።

5. ሙገሳን፣ ወቀሳን፣ሽልማትን፣ ቅጣትን ያስቀምጣል። ግብረ ገብነት በህብረተሰብ ደረጃ ጥንቃቄ ከማድረግ ጋር ተመሳሳይ ከመሆናቸውም ባሻገር የማህበረተሰቡ የጋራ ግብ መዳረሻ ናቸው።

በአሁኑ ወቅት የግብረ ገብ ትምህርት ለሰው ልጅ ህልውናና ብልጽግና አስፈላጊ ነው። እንደሰለጠነና ነፃ ህዝብ ለመኖር ለግብረ ገብ ዕሴቶታችን ከዚህ በፊት ከምንሰጣቸው በበለጠ ዋጋ መስጠት አለብን።

ግብረ ገብነት የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚደረግ ጥረት ነው። እስካሁንም ሰዎች የግብረገብ ህግና መርህ አላቸው። ግን ህዝቦች ለእነዚህ ህጐች አጽንኦት እና ትኩረት ካልሰጡ የህጎቹ መኖር ብቻ ለመልካምነት ዋስትና አይሆኑም። ለግብረገብ መርሆች (ለግብረገባዊነት ባህሪያት) ትኩረት መስጠት ለህልውናና ለአብሮነት ብዙ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋሉ።

ይሁን እንጂ የግብረገብ እሴቶች የሰው ልጅ በራሱ ወገን መጥፎ እንዳይሰራ ወደሚችልበት ደረጃ አልሰረሱም። በዚህ ምክንያት የግብረገብ ትምህርት ከወትሮው የበለጠ አስፋላፊ ሆኖ ተግኝቷል። የግብረገብ ዕሴቶቻችን በውስጣችን ማስረጽ ከቻልን የሰው ልጅ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊትን መቀነስ እንችላለን።

# መቅድም

**የግብረ ገብ ትምህርት የመጨረሻ ዓላማ፡**

(ሀ) ሃላፊነትን የመወጣት፣ ጥሩ ዉሳኔን የመስጠት ችሎታን፣ ፅናትን፣ የስራ ሰነምግባርና ሂሳዊ አስተሳሰብ እና ሌሎች ክሎቶችን በመገንባት ተማሪዎችን ለአዋቂነት እድሜ ዘመናቸዉን የሚረዳ ክህሎት እንዲኖራቸዉ ማስቻል፡፡

(ለ) ተማሪዎችን በትምህርቱ ይዘት ዉስጥ ስላሉት ስለምግባር መርሆች ማለትም መቻቻል፣ ታማኝነት፣ ክብር መስጠትና ትህትና በተግባር ማስተማር፡፡

(ሐ)ተማሪዎች በማህበረሰቡ ዉስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት፡፡

(መ)ተማሪዎችን ስለኢትዮጵያና ስለሰፊዉ ዓለም ባህል ማስተማርና በዓለም ላይ ያሉ ባህሎች ባንድነት ፀጋ ስለመሆናቸዉ ዋጋ እንዲሰጡ ማስተማር፡፡

(ሠ) ለሰፊዉ ልዑላዊ ዓለም ዝግጁ የሆኑ፣ ሃላፊነት የሚሰማቸዉና የሰለጠኑ ዜጎችን መገንባት

ሞራል የሚለዉ ቃል የሰዎች ወግ ወይም ልማዶች ሲሆን ግለሰቦች እንዴት አብረዉ መኖር እንዳለባቸዉ የሚገልፅ ማህበራዊ ትስስር ማለት ነዉ፡፡ በአሁን ጊዜ የትምህርት ቤቶች ዓላማ ወጣቶችን በዕዉቀትና ስነ-ምግባር መገንባት ነዉ፡፡ እንደታማኝነት ፣ ሃለፊነትና ሌሎችን ማክበር ለመሳሰሉት የሞራል በጎነቶች መጨነቅ የግብረ ገብ ትምህርት አንኳር ጉዳይ ነዉ፡፡ የግብረ ገብ ትምህርት ልጆች በተናጥል ጥሩ ህይወት እንዲኖሩ የሚረዳቸዉን በጎ ምግባር ወይም ስነ-ምግባራዊ ልምዶች እንዲያዉቁ መርዳትንና በተመሳሳይ ጊዜ ዉጤታማ የማህበረሰቡ አባላት እንዲሆኑ መርዳት ነዉ፡፡

ስለዚህ ይህ የ6ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት ልጆች በጎ፣ሀቀኛ፣ ሃላፊነት የሚሰማቸዉ ፣እና ሩህሩህ እንዲሆኑና ስለአስፈላጊና አከራካሪ የስነ-ምግባር ጉዳዮች እንዲያዉቁና እንዲያንፀባርቁ ያስችላቸዋል፡፡ ትምህርቱ ልጆችን በመልካም ስነ-ምግባር ያላቸዉ፣ ጥሩ ባህሪ ያላቸዉ፣ በጉልበት የማያምኑ፣ ጤነኛ፣ ሂሳዊ አስተሳሰብ ያላቸዉ፣ ዉጤታማ፣ እንዲሁም ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸዉ ሆነው እንዲያድጉ ያግዛቸዋል፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ትምህርቱ በስድስት ምዕራፍ የተከፋፈለ ነዉ፡፡

# ማውጫ


መግቢያ------------------------------------------------------------------------------------III
መቅድም-----------------------------------------------------------------------------------V

1. የግብረ ገብ ምሉዕነት------------------------------------------------------------------1
1.1 የግብረ ገብ ምሉዕነት ምንነት----------------------------------------------------------2
1.2 የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫዎች -----------------------------------------------------3
1.3 የግብረ ገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ------------------------------------------------------8
1.4 የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለዉ ሰዉ ባህሪያት--------------------------------------------10
1.5 የግብረ ገብ ምሉዕነት አለመሆን የሚያስከትለዉ ዉጤት--------------------------------11
1.6 የምዕራፍ ማጠቃለያ ---------------------------------------------------------------12
2 ለህግ ተገዥነት-----------------------------------------------------------------------15
2.1 ለህግ ተገዥነት ምንነት-----------------------------------------------------------15
2.2 ለህግ ተገዥነት አስፈላጊነት------------------------------------------------------17
2.3 ለህግ ተገዥ የሆነሰው ባህሪያት-----------------------------------------------------18
2.4 ለህግ ተገዥ አለመሆን የሚያስለት ለዉ ውጤት----------------------------------------19
2.4.1 የሰላም እጦት----------------------------------------------------------------20
2.4.2 የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት-------------------------------------------------------21
2.4.3 ሙስና -----------------------------------------------------------------------21
2.4.4 የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ -----------------------------------------------------------22
2.4.5 ህገ-ወጥ የህፃናት ከቦታቦታ ዝዉዉር-------------------------------------------22
2.4.6 የግብር ስወራ -----------------------------------------------------------------23
2.4.7 የነፃነት እጦት----------------------------------------------------------------23
2.4.8 የፍትህ እጦት----------------------------------------------------------------23
2.5 ምዕራፍ ማጠቃለያ--------------------------------------------------------------24

3 መልካም ባህሪ ------------------------------------------------------------------------------------------------27
3.1 የመልካም ባህሪ ምንነት ------------------------------------------------------------------------------------27
3.2 መልካም ባህሪያ ለዉ ስዉ መገለጫዎች --------------------------------------------------------------------29
3.2.1 የሌሎችን ንብረት ማክበር ------------------------------------------------------------------------------30
3.2.2 ታማኝነት --------------------------------------------------------------------------------------------------31
3.2.3 ክብር መስጠት -------------------------------------------------------------------------------------------32
3.3 የመልካም ባህሪ ጠቀሜታዎች ------------------------------------------------------------------------------34
3.4 የመልካም ባህሪ ማዳበሪያ ዘዴዎ ች --------------------------------------------------------------------35
3.4.1 ራስን መቆጣጠር --------------------------------------------------------------------------------------36
3.4.2 ለህግ ተገዥ መሆን ------------------------------------------------------------------------------------37
3.4.3 የማህበረሰቡን ዕሴቶችንና መርሆችን ማክበር ---------------------------------------------------38
3.4.4 የትምህርት ቤትን ህግና ደንብ ማክበር -----------------------------------------------------------40
3.5 የመልካም ባህሪ አለመኖር የሚያስከትለዉ ዉጤት
3.6 የምዕራፍ ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------------------42
4 በማህበራዊ-ኢኮኖሚተሳትፎማደረግ -------------------------------------------------------------------46
4.1 የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ፅንሰ-ሃሳብ ---------------------------------------------47
4.2 በበጎ ፈቃድ ተግባራት ተሳትፎ ማድረግ (ማህበራዊ አገልግሎት) ------------------------------49
4.3 የትርፍ ጊዜ ሰዓትን ለጋራ ጥቅም ማዋል --------------------------------------------------------51
4.4 የሀቀኛ ግብር ከፋዮችና ቁጠባ ለማህበራዊ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ያላቸዉ ሚና --------------------------53
4.5 ምዕራፍ ማጠቃለያ----------------------------------------------------------------------------------56

5 የሀገር ወዳድነት ---------------------------------------------------------------------------59
5.1 የሀገር ወዳድነት ምንነት-----------------------------------------------------------------59
5.2 የሀገር ወዳድነት ስሜት መገለጫዎች-------------------------------------------------------61
5.3 ሀገር ወዳድ የመሆን ጠቀሜታ ----------------------------------------------------------62
5.4 የሀገር ወዳድነት መገለጫዎች --------------------------------------------------------63
5.5 ሀገርን መዉደድ ---------------------------------------------------------------------66
5.6 ምዕራፍ ማጠቃለያ---------------------------------------------------------------------67
6 ሰላምና መተባበር ------------------------------------------------------------------------69
6.1 ሰላም
6.1.1 የሰላም ፅንሰ ሀሳብ -----------------------------------------------------------------70
6.1.2 የሰላም ጠቀሜታ -------------------------------------------------------------------71
6.1.3 ሰላማዊ ባህሪያት ማሳየት -----------------------------------------------------------71
6.2 መተባበር ---------------------------------------------------------------------------73
6.2.1 የመተባበር ፅንሰ ሀሳብ-------------------------------------------------------------73
6.2.2 የመተባበር ጠቀሜታ
6.2.3 የመተባበር እሴቶች
6.3 የሰላምና መተባበር ግንኙነት----------------------------------------------------------75
6.4 የምዕራፍ ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------75

# ምዕራፍ አንድ
## የግብረ ገብ ምሉዕነት

የመማ ር ውጤቶች፡- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡
- የግብረ ገብ ምሉዕነት ጽንሰ-ሃሳብ ትረዳላችሁ፤
- የግብረ ገብ ምሉዕነት መለያ ባህሪያትን ትረዳላችሁ፤
- የግብረ ገብ ምሉዕነት አስፈላጊነትን ትገነዘባላችሁ፤
- እውነተኛ ምሉዕነት ያለው ሰው የሚያሳያቸውን ባህሪያትን በተግባር ታሳያላችሁ፤
- የግብረ ገብ ምሉዕነት አለመኖር የሚያመጣቸውን ችግሮች ትለያላችሁ፡፡

## መግቢያ

አሁን ካለሁበት የተሻለ ሰው እንዴት መሆን እችላለሁ? ይሄስ እኔን ሊያሳስበኝ የሚገባ ጉዳይ ነው? እያንዳንዳችን የምንኖርበት ማህበረሰብ ግለሰብ አባላቶች ነን፡፡

ከቤተሰቦቻችን፣ ከጎረቤቶቻችን እና በትምህርት ቤታችን ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር መስተጋብሮች አሉን፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የግብረ ገብ ምሉዕነት ትርጉምንና ጠቀሜታን መረዳት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የግብረ ገብ ምሉዕነት መጓደል ሊያመጣቸው የሚችላቸውን አሉታዊ ውጤቶች ይረዳሉ፡፡





ስዕል 1.1. ከላይ በምስሉ ተማሪዎች እየፈጸሟቸው ያሉት ተግባራት ጥሩ ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

## 1.1 የግብረ ገብ ምሉዕነት ምንነት

**ተግባር 1.1**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች የግል ሃሳባችሁን ስጡ። ቀጥሎም ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1) 'ምሉዕነት' የሚለው ቃል ትርጉም ምን ይመስላችኋል ?
2) ምሉዕነት ያለው ሰው የሚያሳየውን አንዳንድ ባህሪያት ጥቀሱ፤
3) ግለሰባዊ ምሉዕነት መኖርን የሚያሳዩ ድርጊቶችን ግለጹ፤

ምሉዕነት አንድ ሰው ስለ ነገሮች ባለው መሰረታዊ ግላዊ እምነትና ከዕለት ወደ እለት በሚፈጽማቸው ድርጊቶች መካከል ኢ-ተለዋዋጭ አቋምን የማሳየት ብቃትን ይወክላል። መሰረታዊ ግላዊ እምነት የምንላቸው አንድ ገለሰብ ተገቢነት ያላቸው ብሎ የተቀበላቸው እምነቶች ናቸው።ምሉዕነት ያላቸው ግለሰቦች ከሚኖሯቸው መሰረታዊ እምነቶች መካከል የሚከተሉት ይካተታሉ፡- ሃቀኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ወጥነት፣ድፍረት እና ርህራሄ። ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ግለሰብ ሌሎች ሰዎች በአጠገቡ ኖሩም አልኖሩም እነዚህን መሰረታዊ ባህሪያት ያሳያል።

ከላይ የተጠቀሱትን የግብረ ገብ እሴቶች ከታች በተቀመጡት ትንታኔዎች የበለጠ ይብራራሉ። ህይወታችንን በምሉዕነት ለመምራት፡-

1) ግለሰቡ ለራሱ ሀቀኛ መሆን ይኖርበታል። ሰዎች ስህተት መስራታቸውን በራሳቸው መቀበል ካልቻሉ ለሌሎች ሰዎች (በሕዝብ ፊት) ሃቀኛ መሆን አይችሉም።

ሰዎች እውነተኛ ግብረገባዊ ምሉዕነት እንዲኖራቸው የሚፈጽሟቸውን ድርጊቶች በአጽንኦት መገምገም አለባቸው። ራሳቸውን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ይገባቸዋል፡

- የፈጸምኩትን ተግባር ሌሎች ሰዎች ቢያውቁት ሀፍረት እንዲሰማኝ ያደርግ ይሆን?
- የፈጸምኩት ድርጊት እውነተኛ ውስጣዊ እምነቴን ያንጸባርቃል?

ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች ምላሹ አጥጋቢ ካልሆነ ግለሰቡ ድጋሚ ይህን አይነት ተግባር ላለመፈጸም መወሰን አለበት።

1) ምሉዕነት በራስ ከመተማመን ብቃት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ባህሪ ነው። ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ሌሎች ሰዎች ላይስማሙበት ስለሚችሉ ብቻ ትክክለኛ ነገር ከመፈጸም ወደኋላ አይልም። ውጤቱ ምንም ሆነ ምን የተሳሳቱ ድርጊቶችን ተቃርነው ይቆማሉ። ምሉዕነትን የተላበሰ ሰው ሌላ ሰው መልካም ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽም በዝምታ አይመለከትም። ለምሳሌ በትምህርት ቤታችን ውስጥ የሚገኝ ተማሪ የዛፎችን ቅጠሎች ሲቆራርጥ ቢታይ ምሉዕነት የተላበሰ ሌላ ተማሪ ድርጊቱን እንዲያቆም በድፍረት ይናገራል።

1) እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሱ ሰዎች በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተገቢውን ዋጋ ይሰጣሉ። እንደዚሁም የሌሎች ሰዎችን ሚስጥሮች በመጠበቅ ይታወቃሉ። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም እውነትን ብቻ ይናገራሉ። በፍጹም ከሰዎች በስተጀርባ ጉዳት የሚያስከትል ነገር አይናገሩም። እነዚህ ባህሪዎቻቸው ሌሎች ሰዎች ወደ እነርሱ እንዲሳቡ ያደርጋቸዋል።

## 1.2 የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫዎች

ተግባር 1.2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሻችሁን ስጡ። ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1) የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው የሚያሳያቸው ባህሪያት ግለጹ፤
2) ውስጣዊ ወጥነት ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ፤
3) በክፍላችሁ ውስጥ በግብረ ገብ ምሉዕነት የሚፈጸሙ ተግባሮች ጥቂት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ተወያዩ፤

ግብረገባዊ ምሉዕነት ያለው ሰው የሚፈጽማቸው ድርጊቶች የሚከተሉት ተመሳሳይ ባህሪያት ይኖራቸዋል፦

ሃቀኝነት: ውጤቱ ምንም ሆነ ምን እውነቱን ብቻ የመናገር ብቃት ነው።

እስኪ ታደሰ ያለበትን ሁኔታ ተመልከቱ፡

<u>ውስን ጥናት 1</u>፡ ታደሰ የ 6ኛ ክፍል ተማሪ ነው። አስተማሪያቸው የክፍሉ ተማሪዎች የቤት ስራ ሰርተው እንዲመጡ አዘዛቸው። አስተማሪያቸው ሁሉም ተማሪ በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት የቤት ስራውን አጠናቀው ሰርተው መምጣት እንዳለባቸው አስተላልፎ ነበር። ታደሰ የቤት ስራውን በተባለው የሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት ለማጠናቀቅ ቢሞክርም አስተማሪያቸው ባሳያቸው መንገድ ጥያቄዎቹን ለመስራት አልቻሉም። የታደሰ ጓደኛ የጥያቄ መልሶቹን ከሌሎች ጓደኞቻቸው ወስዶ በመገልበጥ የመምህራቸውን ቅጣት ማምለጥ እንደሚቻል ነገረው። ሆኖም ታደሰ ታማኝ ተማሪ ስለነበር ለመምህሩ ያጋጠመውን አስቸጋሪ ሁኔታ አስረዳ። አስተማሪውም ታደሰ ያጋጠመውን ችግር መረዳት ቻለ። በመቀጠልም አስተማሪው ለተማሪዎቹ መልሱን ማግኘት የሚችሉበት አዲስ ዘዴ አሳያቸው። የታደሰ ሀቀኝነት ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ጥያቄዎቹን መመለስ የሚያስችላቸው አዲስ መንገድ እንዲማሩ እድል ፈጠረላቸው።

- የታደሰ ሃቀኝነት ያመጣው ውጤት ምን ነበር?
- ሀቀኛ መሆን ለተማሪዎች የሚኖረውን ፋይዳ ግለጹ፤

ሀቀኛ ሰዎች ውጤቱ ምንም ሆነ ምን ሁልግዜ እውነት ብቻ ይናገራሉ፡፡ ስህተት መስራታቸውን ለመቀበል የማይቸገሩ ሲሆን ራሳቸውን ለማሻሻል እንዲቻላቸው ለመስራት ፈቃደኞች ናቸው፡፡ ይህ ሀቀኝነታቸው ሌሎች በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች በእነርሱ ላይ እምነት እንዲጥሉ ያደርጋቸዋል፡፡

**ድፍረት፡ አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው፡፡**

አሁን ደግሞ የኬናና የዳንኤልን ሁኔታ እንመልከት፡

<u>ውስን ጥናት 2</u>፡ ኬናና ዳንኤል በትምህርት ቤታቸው መጫዎቻ ሜዳ ላይ እግርኳስ እየተጫወቱ ነበር፡፡ ኬና አግብቻለሁ ብሎ ቢያስብም ዳንኤል ኳሱ መስመሩን ስላላለፈ ግብ አይደለም በማለት ተከራከረ፡፡ ይህም በሁለቱ መካከል ጭቅጭቅ እንዲፈጠር ምክንት ሆነ፡፡ይህ ክርክር የሌሎች ልጆችን ትኩረት ሳበ፡፡ሁለቱም ተማሪዎች በመካከላቸው የተከሰተውን ግጭት በሰላማዊ ሁኔታ መፍታት እንዳለባቸው ተረድተዋል፡፡ ሆኖም ኬና ክርክሩን ቀድሞ ቢያቆም ጓደኞቹ ፈሪ ብለው ይጠሩኛል በማለት ሰግቷል፡፡ በተቃራኒው ዳንኤል የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ወጣት በመሆኑና ከኬና ጋር ያለው ጓደኝነት ከኳስ ጨዋታው እንደሚበልጥ በመረዳቱ ኬና ያቀረበውን ውሳኔ በመቀበል ኳሱ ግብ ነበር ሲል አጸደቀ፡፡ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የነበረው ድፍረት ጓደኛው ተገቢ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ አድርጎታል፡በድፍረት ለራሱ እውነተኛ በመሆንና ውሳኔውን ሌሎች ለሚይዙት ድምዳሜ ሳይሆን በራሱ ለመወሰን ትክክለኛውን መንገድ ተከትሏል፡፡

- በኬናና በዳንኤል መካከል ያለውን የባህሪ ልዩነት ማስረዳት ትችላላችሁ?
- ከላይ ካለው ታሪክ ተነስታችሁ ስለድፍረት ጥቅም ምን ታስባላችሁ?

ድፍረት የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው መሰረታዊ መገለጫ ነው፡፡ ድፍረት ሰዎች ግጭትን በሰላም እንዲፈቱ ያስችላቸዋል፡፡ ሳይፈቱ የሚቆዩ ግጭቶች ወደ ከፋ ደረጃ ሊያድጉ የሚችሉና ወደ ሌሎችም ሊዛመቱ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንደ ደካማ ልታይ እችላለሁ በማለት የገቡበትን ግጭት ላለመፍታት

ያመነታሉ፡፡ በመሆኑም ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለበት እያመኑም ቢሆን በግጭት ውስጥ ለመቆየት ይመርጣሉ፡፡

ደፋር ሰው ግብረ ገባዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን በሌሎች ሰዎች አስተያየትና ይሁንታን አይጠብቅም፡፡ ማድረግ የሚገባውን ተግባር በወቅቱና በዚያው ሰዓት ይፈጽማል፡፡ ስለዚህ እውነተኛ ደፋር ሰው ድርጊቱን ሁሉ የሚመራው ከራሱ/ከራሷ እውነተኛ አስተሳሰብ በመነሳት ነው፡፡

ስለሌሎች ማሰብ፡ እራስን በሌሎች ሰዎች ቦታ ላይ አስቀምጦ በማሰብ ስሜታቸውን መረዳት፡፡

## የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ከታች ላሉት ጥያቄዎች መልሳቸውን አስቡ፡፡ ከተቻለም ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

1) ጓደኛችሁ አንዳች ችግር እንዳጋጠመው እንዴት መረዳት ትችላላችሁ?

2) ጓደኛችሁን ለመርዳት ምን ታደርጋላችሁ?

ውስን ጥናት 3፡ መቅደስ እና ሩሃማ ምርጥ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ አዘውትረው በክፍል ውስጥ አንድ ላይ የሚቀመጡ ሲሆን በምሳ ሰዓትም አብረው ይጫወታሉ፡፡ ሁለቱም ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን መቅደስ ጸጉሯ ሳይበጠርና ልብሷ እንደቆሸሸ ወደ ት/ቤት መጣች፡፡ መቅደስ በቤቷ ስለተፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ ለሩሃማ አሰረዳቻት፡፡ ወላጆቻቿ ሌሊቱን በጥል በማሳለፋቸው መቅደስ ሌሊቱን ያሳለፈችው በጎረቤቶቿ ቤት ውስጥ ነበር፡፡ ሩሃማ የሰማችው ነገር እጅጉን ረበሻት፡፡ወደቤቷ ከደረሰችም በኋላ ስለጉዳዩ ማሰብ ማቆም አልቻለችም፡፡ ራሷን ከዚህ በታች እንደሚከተሉት አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ጀመረች፡

- የጓደኛዋ ውስጣዊ ህመም የፈጠረባትን ስሜት ምን እንደሆነ፣
- እሷ በጓደኛዋ ቦታ ብትሆን ምን አይነት ስሜት ሊሰማት እንደሚችል፣
- ጓደኛዋ ያለችበትን የስሜት ህመም እንዴት ማቃለል እንደምትችል፣

ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማየት ማለት የሌሎች ሰዎችን ስሜት ራስን በነሱ ቦታ ሆኖ ለመረዳት የመቻል ብቃት ነው፡፡ ይህ ሰዎች አንዳቸው ከሌላው ጋር የሚኖራቸውን የሀሳብ መረዳት ከፍ ያደርጋል፡፡ እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው የሌሎች ሰዎችን ችግሮች የመረዳትና ደስታቸውን አብሮ የመካፈል ችሎታ አለው፡፡

- የሌሎች ሰዎችን ስሜት መረዳት እንዲቻላቸው በጥንቃቄ ያደምጣሉ፤
- የሆነው ነገር በእነርሱ ላይ የተፈጸመ ቢሆን እንዴት ሊሰማቸው ይችል እንደነበር በእምሯቸው ይስላሉ፤

ለምሳሌ ሌሎችን ለመበደልና ለማስከፋት ሙከራ አያደርጉም ምክንያቱም በደሉ በእነርሱላይ ቢፈጸም ሊፈጥርባቸው የሚችለውን መጥፎ ስሜት አስቀድመው ያስባሉና፡፡

ውስን ጥናት 4፡ አብረኸት እና ዮዲት ጎን ለጎን በሚጎራበቱ ቤቶች ውስጥ ይኖራሉ፡፡ የዮዲት ወላጆች ለልጃቸው ውድ የሆኑ ብዙ መጫዎቻዎችን ይገዛሉ፡፡ በዓል ሲመጣም አዳዲስ ልብሶች ይገዙላታል፡፡ የአብረኸት ወላጆች ግን እንደዚህ ዓይነት ውድ መጫዎቻዎችን ሆነ ልብሶችን መግዛት የሚያስችል ገንዘብ የላቸውም፡፡ ዮዲት ጎረቤቶቿን ለማስቀናት በማሰብ መጫዎቻዎችን ወደ ውጭ ይዛ ትወጣለች፡፡አብረኸት በመጫወቻዎቹ ለመጫዎት አዘውትራ ብትለምናትም ዮዲት ፈቃደኛ አትሆንም፡፡ ዮዲት አዲስ ልብስ ለብሳ እንደማታውቅ በአብረኸት ላይ ባሾፈችባት ቁጥር አብረኸት ታለቅስ ነበር፡፡ከዕለታት በአንድ ቀን የዮዲት ወላጆች ድንገት በተከሰተ አደጋ ምክንያት ያላቸውን ሀብት በሙሉ አጡ፡፡ ወላጆቿ ከነዮዲት ቤተሰብ ጋር እንድትኖር መላክ ነበረባቸው፡፡ ዮዲት በአብረኸት ላይ ያደረገችውን በማሰብ ተመሳሳይ ነገር ያጋጥመኛል በማለት ፍርሃት አደረባት፡፡ ሆኖም አብረኸት በተቃራኒው ዮዲትን በፍቅርና በክብር አዘውትራ ተንከባከበቻት፡፡ ዮዲት አብረኸት ለሰጠጫት ፍቅርና ክብር ፍጹም አመስጋኝ ነበረች፡፡ ለአብረኸትም ትልቅ ፍቅርና አክብሮት አደረባት፡፡ ቀደም ሲል ለአብረኸት ታሳያት የነበረው ባህሪ ሀፍረት እንዲሰማት አድርጓት ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሰዎችን በሙሉ በክብር ለመያዝ ለራሷ ቃል ገባች፡፡

- ከላይ ካነበባችሁት ታሪክ ተነስታችሁ ራስን ከሌሎች አስበልጦ አለማየት ያለው ጥቅም ምንድን ነው ትላላችሁ?
- ሁሉንም ሰዎች በእኩልነት ማየት ምን ጥቅም ያስገኛል?

የግብረ ገብ ምሉዕነት ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች ጋር እኩል እንደሆኑ ያምናሉ፡ ፡ሁሉንም ሰዎች በእኩልነት ያያሉ፡፡ ሰዎችን የተለየ መስፈርት ምክንያቶችን በመጠቀም ለማበላለጥ አይሞክሩም፡፡ ለድሆች መልካም ቀረቤታ ሳይኖረው ሃብት ያላቸውን ሰዎች በተሻለ መንገድ ለመያዝ አይሞክርም፡፡

ውስን ጥናት 5፡ የዘይነብ ክፍል የተሰጠ ስራ በመምህሩ ተመድቦለታል፡፡ የተሰጠው ስራ በሳምንት ውስጥ ተሰርቶ መጠቃለል ይገባዋል፡፡ ከየቡድኑ አንዳንድ ተማሪዎች የቡድን መሪ ሆነው ተሰይመዋል፡፡ ዘይነብ ከቡድን መሪዎች መካከል አንዷ ናት፡፡ የዘይነብ ቡድን በተሰጠው ጊዜ ስራውን ለመጨረስ አልቻለም፡፡ ይህም የሆነው አንዳንድ የቡድኑ አባላት በበሚጠበቅባቸው ልክ ስራቸውን መውጣት ባለመቻላቸው ነበር፡፡ ዘይነብ ራሷን ነጻ ለማውጣት የትኞቹ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሃላፊነት በወቅቱ እንዳልተወጡ ለመምህሯ መንገር ትችል ነበር፡፡ ሆኖም እንደ ቡድን መሪነቷ ለስራው በወቅቱ አለመፈጸም ሙሉ ኃላፊነት ወሰደች፡፡ ጓደኞቿ በተሰጠው ግዜ ስራቸውን እንዲጨርሱ የማገዝ ሃላፊነት ባለመወጣቷ የተፈጠረ እንደሆነ እንደተሰማት በመናገር አስተማሪዋን ይቅርታ ጠየቀች፡፡ መምህሩ ሃላፊነትን ወደ ራሷ የወሰደችበትን መንገድ አድንቆ ስራው የሚጠናቀቅበትን ቀን በሁለት ቀናት አራዘመ፡፡ የቡድኗ አባላትም ስራቸውን እንዳልሰሩ ስላላጋለጠች እጅግ አመስጋኞች ነበሩ፡፡ ያላቸውን ሃይል በሙሉ በስራው ላይ በማዋል በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውሰጥ ስራቸውን ጨርሰው ማቅረብ ቻሉ፡፡

- ዘይነብ እንደ ቡድን መሪነቷ ምን ሃላፊነት ይጠበቅባት ነበር?
- በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍላችሁ አሳውቁ፡፡

ሃላፊነትን መውሰድ ማለት በግላችን ለምንወስናቸው ውሳኔዎች ውጤቱ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሃላፊነት ለመውሰድ ፍቃድኛና ዝግጁ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

ኢ-ተለዋዋጭነት/ወጥነት፡ ብቻችንን ስንሆን የምናሳየውን ባህሪ ከሌሎች ጋርም ስንሆን በተመሳሳይ ማሳየት መቻል ነው፡፡ የአንድ ወጥ ባህሪ ባለቤት መሆንን ያሳያል፡፡

ተግባር 1.3

የሚከተለውን ታሪክ አንብቡና የራሳችሁን ሃሳብ አንጸባርቁ፡፡ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

ወ/ሮ እቴነሽ ሁለት ልጆች አሏት፡፡ 12 ሰዓት ላይ ከስራዋ ከወጣች በኋላ ያላትን ጊዜ ከልጆቿ ጋር ታሳልፋለች፡፡ ለልጆቿም የታማኝነት፣መልካምነትና ጠንክሮ መስራት ያላቸውን ዋጋ ታስተምራቸዋለች፡፡ ውጤቱ ምንም ሆነ ምን ሁልጊዜ እውነቱን እንዲናገሩ ታበረታታቸዋለች፡፡ ልጆቿ ትምህርት በማይኖራቸው ሰዓት ወደ ስራ ቦታዋ ይዛቸው ትሄዳለች፡፡ ከእናታቸው የሚሰጣቸውን ምክር በአግባቡ ያዳምጣሉ፡፡ ሆኖም እናታቸው በስሯ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞችን እንዴት እንደምትይዝ ይመለከታሉ፡፡

ለሰራተኞቿ ክብር እንደሌላት ተረድተዋል፡፡ ለመንግስት መክፈል የሚገባትን ግብር ላለመክፈል ስትል ለማጭበርበር ስትሞክር ተመልክተዋል፡፡ ልጆቹ በእናታቸው ንግግር እና በተግባሯ መካከል አለመጣጣም መኖሩን ታዝበዋል፡፡

- የወ/ሮ እቴነሽ ተግባራት በግብረገባዊ ምሉዕነት የሚመሩ ናቸው?
- ወ/ሮ እቴነሽ የትኞቹን የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫ የሆኑ ባህሪትን ጥሳለች?

የግብረ ገብ ምሉዕነት ያላቸው ግለሰቦች በሚያስቡበት መንገድና በሚያሳዩት ባህሪያት መካከል ተመሳሳይነት አለ፡፡ ግልጽ የሆነ ግብ አስቀምጠው የሚንቀሳቀሱ ሲሆን ድርጊቶቻቸውም የሚመሩት በአስቀመጧቸው ግቦች መሰረት ነው፡፡ አስተሳሰባቸውና ድርጊታቸው ውጥነት ያለው ግለሰቦች በዙሪያቸው ላሉ ሌሎች ሰዎች ጥሩ አርአያ የሚሆኑ ናቸው፡፡

## 1.3 የግብረ ገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ

ተግባር 1.4

የሚከተሉትን ጥያቀዎችን መልሱ፡፡ ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1) ተግባሮቻችንን በግብረ ገብ ምሉዕነት መምራት ያለውን ጥቅም ዘርዝሩ፤
2) በግብረ ገብ ምሉዕነት የሚመሩ አባላት ባሉት ማህበረሰብ ውስጥ መኖር ምን ጥቅሞች ይኖሩታል?
3) በክፍላችሁ ውስጥ በግብረ ገብ ምሉዕነት መመራት ያለውን ጥቅም ተወያዩበት፤



ስዕል 1.2 አስተማሪ ተማሪውን ሲያበረታታ

በግብረ ገብ ምሉዕነት ራሳቸውን  የሚመሩ ሰዎች ያሉት ማህበረሰብ ጠንካራ ሰራተኛ የሆነ ማህበረሰብ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ማህበረሰብ ከሌሎች ልፋት የሚገኝ ትርፍን የመሰብሰብ አላማ አይኖረውም፡፡ ይህን አይነት ማህበረሰብ አባላቱ ያላቸውን አቅም ሁሉ አሟጠው ህይወታቸውን ለማሻሻል የሚተጉ ናቸው፡፡ ይህንን ግባቸውን ማሳካት የማይሳናቸው ሲሆን ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ከሌሎች ሰዎች ጋርም ሆኑ ብቻቸውን ጠንካራ ሰራተኞች በመሆናቸው ነው፡፡

ግብረገባዊ ምሉዕነት ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራል፡፡ ይህ ትስስር የሰዎች የእርስ በዕርስ መተማመን ውጤት ነው፡፡ በዚህ ምሉዕነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ቃል የገቡትን ነገር አያፈርሱም፡፡ የገቡትን ማሃላ በቁምነገር ይወስዳሉ፡፡ በቀላሉ ቃል አይገቡም ቃላቸውን ከሰጡ ግን እስከመጨረሻው ሳያፈርሱ ይጠብቁታል፡፡ አንዳቸው በሌላቸው ላይ ያላቸውን እምነት አያጓድሉም፡፡

ግብረገባዊ ምሉዕነት ከሌሎች የምንፈልገውን ክብር ለማግኘት እንድንችል ያግዘናል፡፡ ሰዎች ሁልግዜ እውነት የሚናገሩ ግለሰቦችን ያከብራሉ፡፡ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሱ ሰዎች ባሉበት ቦታዎች የሚፈጸሙ መጥፎ ተግባራትን ለማጋለጥና ድርጊቱን እንዲቆሙ ለማድረግ ድምጻቸውን ያሰማሉ፡፡በመሆኑም በግብረ ገብ ምሉዕነት የታነጹ ህዝቦች ያሉት ማህበረሰብ የተከበረ ማህበረሰብ ነው፡፡

ምሉዕነት የአንድን ሰው ችግር የመፍታት ብቃት ለማሳደግ እጅግ ጠቃሚ ግብዓት ነው፡፡ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ፈታኝ ሁኔታዎች ሲከሰቱ መጋፈጥ ይችላል፡፡ ከችግሮቹ ፊታቸውን አያዞሩም፡፡ ያካበቱት ድፍረት ችግር የመፍታት ብቃታቸውን ለማሳደግ ያስችላቸዋል፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እንዴት መጋፈጥ እንደሚችሉ ውጤታማ የሆኑ የችግር መፍቻ ክህሎቶችን ያዳብራሉ፡፡

## 1.4 እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህሪያት

የግብረ ገብ ምሉዕነት ያላቸው ሰዎች ህይወታቸውን የሚመሩት ጥሩ ናቸው ብለው በመረጧቸው መርሆች

**ተግባር 1.5**

የሚከተሉትን ጥያዌዎች መልሱ

1) የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ያሉትን ባህሪያት ጥቀሱ፤
2) የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ማሶገድ የሚኖርበት ባህሪያት የትኞቹ እንደሚሆኑ አብራሩ፤
3) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሊያሣዩአቸው ስለሚችሉቸው የግብረ ገብ ምሉዕነት ባህሪያትን ተወያዩ፤

መሰረት ነው። እነዚህ መርሆች በሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ላይ ይተገብራሉ። እነዚህን የህይወት መመሪያዎቻቸውን በምንም ምክንያት ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም። ሌሎች ሰዎች ላይስማሙባቸው ይችላሉ ብለው በማሰብ የሚፈልጉትን ከማድረግ ወደ ኋላ አያፈገፍጉም።

ራሳቸውን በምሉዕነት የሚመሩ ሰዎች ለማድረግ የገቡትን ቃል ወደ ተግባር እንደሚቀይሩት እምነት ይጣልባቸዋል። ማድረግ የማይችሉትን ወይም የማይፈልጉትን ለማድረግ በፍጹም ቃል አይገቡም። "የምትናገረውን ሆነህ ተገኝ" እንደሚለው አባባል የግብረ ገብ ምሉዕነት ያላቸው ሰዎች ቃላቸውን በመፈጸም ይታወቃሉ። በሌላ አነጋገር ቃላቸውን ተፈጻሚ ለማድረግ የማያወላዱ ናቸው ማለት ነው።

በምሉዕነት ራሳቸውን የሚመሩ ግለሰቦች የሕይወት መርሆቻቸውን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ይተገብራሉ። ሁኔታዎችን እያዩ መቼ ሀቀኛ መሆን እንዳለባቸውና መቼ መዋሸት እንዳለባቸው ምርጫ ውስጥ አይገቡም።ለምሳሌ በፈተና ወቅት የሚኮርጅ ተማሪ ለወላጆቹ ታዛዥ ቢሆንም እንኳ የግብረ ገብ ምሉዕነት አለው ብሎ ሊወሰድ አይችልም። የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ለመሆን ተማሪዎች ሰው ቢያያቸውም ባያያቸውም ሁልጊዜ ትክክለኛውን ባህሪ ማሳየት ያስፈልጋቸዋል።

በምሉዕነት ራሱን የሚመራ ግለሰብ ከሚታወቅባቸው ባህሪያት አንዱ ከፍተኛ የሆነ የራስ መተማመን ነው። ሌሎችን ለማስደሰት ሲሉ የሚያምኑበትን የህይወት መርሆች ከመተግበር አይቆጠቡም። ከውጭ የሚመጣን ጫና ለመቋቋም የሚያስችል በራስ የመተማመን ብቃት ይኖራቸዋል። በሌላ አነጋገር ትክክል ነው ብለው በሚያምኑት እና በድርጊታቸው መካከል የማይቆራረጥ ትስስር መኖሩን ያሳያል።

ምሉዕነትን የተላበሰ ግለሰብ እያንዳንዱ ሰው ያለውን ዋጋ ይረዳል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ሰዎችን በማክበር ይታወቃሉ፡፡ የዕድሜ ጓደኞቻቸውን፣አስተማሪዎቻቸውንና ወላጆቻቸውን መናቅ/አለማክበር አይፈልጉም፡፡ አሰተማሪዎቻቸውን በሚያከብሩበት ልክ ለቤት አልባ የጎዳና ላይ ነዋሪዎች ተገቢውን ክብር ይሰጣሉ፡፡

በምሉዕነት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የማያወቁት ነገር ሲያጋጥማቸው ይህንኑ ሳይሸሽጉ ይናገራሉ፡፡ ባለማወቃቸው እንዳይሾፍባቸው በመስጋት የማያውቁትን ነገር አውቃለሁ በማለት ለማስመሰል አይሞክሩም፡፡ በሌላ አነጋገር ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሀቀኞች ናቸው፡፡ ሀቀኝነታቸው አዳዲስ ነገሮችን እንዲማሩ ያስችላቸዋል፡፡

## 1.5 የግብረ ገብ ምሉዕነት አለመኖር የሚያስከትለው ችግር

**ተግባር 1.6**

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ የራሳችሁን ሃሳብ አንጸባርቁ፡፡ ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

1) በግብረ ገብ ምሉዕነት ያልታጀበ ድርጊት የሚያመጣውን ችግር ግለጹ፤
2) በት/ቤታችሁ የሚታዩ የግብረ ገብ ምሉዕነት መጓደልን የሚያሳዩ አንዳንድ ድርጊቶችን አጋሩ፤

ሰዎች ከምንም ነገር ተነስተው መጥፎ ማንነት አይላበሱም፡፡ ምሉዕነት በጊዜ ሂደት ውስጥ ይጠፋል፡፡ አልፎ አልፎ የምናደርጋቸው ነገሮች ቀስበቀስ ምሉዕነታችንን ይሸረሽሩታል፡፡ ምሉዕነት እንደውሸትና ስርቆትን የመሳሰሉ ድርጊቶችን ማስወገድን ይጠይቃል፡፡

ለምሳሌ አንድ ተማሪ ጎደኞቹን ለማሳቅ ሲል በሚነግራቸው ታሪክ ውሰጥ ጥቂት ውሸት ይጨምርበታል እንበል፤ እሷ/እሱ ውሸት እየተናገሩ እንዳሉ ያውቃሉ፡፡ ይህ ማለት ያላቸውን የግበረ ገብ ምሉዕነት የጓደኞቻቸውን ትኩረት ለማግኘት ሲሉ ብቻ ለድርድር ያቀረቡታል ማለት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ጥቃቅን የሚመስሉ ድርጊቶች በጊዜ ሂደት ውስጥ ይጠራቀሙና በምሉዕነት ላይ ትልቅ ጫና ይፈጥራሉ፡፡

አንድ ሰው የሚፈጽመው ድርጊት እውነተኛ ማንነቱ የማያሳይ ከሆነ ግብዝ/አስመሳይ ነው፡፡ የአንድ ሰው ባህሪ ከድርጊቱ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በዙሪያው ባሉ ሰዎች ዘንድ እምነት የማይጣልበት ይሆናል፡፡ ወዳጅነት በመተማመን ላይ የሚመሰረት በመሆኑ ግብዝ ሰዎች እውነተኛ ወዳጅነት መመስረት አይቻላቸውም፡፡ አስመሳይ ሰዎች ቃላቸውን ይፈጽማሉ ወይም ሚስጥር ይጠብቃሉ ተብሎ እምነት አይጣልባቸውም፡፡

አንድ ሰው እንደ መስረቅ፣ማጭበርበርና ስርቆትን የመሳሰሉ ተግባራትን የሚፈጽም ከሆነ በራስ የመተማመን ችሎታው ቀስ በቀስ ይሸረሸራል፡፡ በራስ የመተማመን ችሎታ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የምናሳየው ባህሪ ጥቅል ውጤት ነው፡፡ እውነተኛ ምሉዕነት ያልተላበሰ ማህበረሰብ ሙሰኛ ማህበረሰብ ነው፡፡ ለዚህ መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል በስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ አሳዳጆች መሆናቸው ነው፡፡ መልካም የሆነ የግብረ ገብ ባህሪ ማነስ ስላለባቸው ውስጣዊ ደስታ ማግኘት አይቻላቸውም፡፡ በመሆኑም ይህንን ክፍተታቸውን ለመሙላት የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማለትም ውደ መኪናዎችን ይገዛሉ ወይም አደንዛዥ እጾችን ይጠቀማሉ፡፡ እንደዚሁም አንድ ማህበረሰብ በግብረ ገብ ምሉዕነት በሚጎድላቸው ሰዎች ከተሞላ ምንም አይነት መጥፎ ተግባራት በማህበረሰቡ መሃል ቢፈጸም ድፍረት ስለሚያንሳቸው ድርጊቱን ለማስቆምም ሆነ ለማጋለጥ አይደፍሩም፡፡ በመሆኑም በስልጣን ላይ ተቀምጠው ብልሹ ባህሪ የሚያራምዱ ባለስልጣኖችን የሚያስቆም ምንም አካል አይኖርም፡፡

## 1.6 የምዕራፍ ማጠቃለያ

እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያላቸው ግለሰቦች ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ሀቀኞች ናቸው፡፡ ሀቀኝነት ማለት ውጤቱ ምንም ሆነ ምን እውነቱን ብቻ መናገር ማለት ነው፡፡ ሀቀኛ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ድካም ላይ ትርፍ ለመሰብሰብ አይሹም፡፡ የራሳቸው ያልሆነ ነገርን አይወስዱም፡፡ እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው በሚያደርጋቸው ድርጊቶች መካከል ወጥነት ይታይበታል፡፡ ከሰዎች ጋር ሆኑም ወይም ብቻቸውን ባህሪያቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው ሁሉንም ሰዎች በእኩልነት ይመለከታል፡ ፡ በፆታ፣በሃይማኖት ወይም በኢኮኖሚያዊ ደረጃ ልዩነት ምክንያት አያበላልጥም፡፡

ቁልፍ ቃላት

- ምሉዕነት
- ትሕትና
- ተጠያቂነት/ሃላፊነትን መውሰድ
- ወጥነት
- ግብዝነት
- የግብረ ገብ እምነቶች
- ማህበራዊ ትስስር

መልመጃ 1.1

ትዕዛዝ አንድ፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኂላ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. ምሉዕነት ማለት አንድን ነገር ስንከውን በእውነተኛ እምነታችን መሰረት የመፈጸም ብቃት ነው፡፡
2. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ጥቅሙን እሚያስጠብቅለት ከሆነ ብቻ እውነት ይናገራል፡፡
3. ትህትና ማለት ራስን ከሌሎች አስበልጦ የማየት ብቃት ነው፡፡
4. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው መጥፎ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ካየ ድርጊቱን ለማጋለጥ ወይም እንዲቆም ለመናገር ድፍረቱ አላቸው፡፡
5. የግብረ ገብ ምሉዕነት መጓደል አንድን ሰው በሌሎች እንዲታመን ያስችለዋል፡፡

ትዕዛዝ ሁለት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ከሚከተሉት አንዱ ባህሪ ሊኖረው አይገባም

(ሀ) ሃላፊነትን መውሰድ

(ለ) ድፍረት

(ሐ) ሃቀኝነት የጎደለው

2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብረ ገብ ምሉዕነት መላበስ የሚያመጠው ጥቅም ነው፡፡

(ሀ) የሌሎችን ክብር ማግኘት

(ለ) ጓደኛ አልባ መሆን

(ሐ) ግብዝ/አስመሳይ መሆን

1. ራስን በሌሎች ቦታ አስቀምጦ መመልከት ማለት------------ ነው

(ሀ) ትህትና

(ለ) ሀቀኝነት

(ሐ) ድፍረት

1. የግብረ ገብ ምሉዕነት መጓደል የሚታይባቸው ሰዎች ከሚከተሉት ባህሪት ውስጥ አንዱን ያሳያሉ

(ሀ) የሌሎችን ሚስጥር ይጠብቃሉ

(ለ) ከፍ ያለ በራስ የመተመማን ብቃት አላቸው

(ሐ) ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ዝንባሌ አላቸው

ትዕዛዝ III: ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምልስ ስጡ። ምላሻችሁን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1. ምሉዕነት ምን ማለት ነው?

2. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት የተላበሰ ሰው ባህሪያትን አብራሩ፤

3. ድርጊቶቻችንን በግብረ ገብ ምሉዕነት መምራት ያለውን ጥቅም አስረዱ፤

4. በትምህርት ቤት ደረጃ የግብረ ገብ ምሉዕነት መገለጫ ከሆኑት ድርጊቶች ውስጥ የተወሰኑትን ግለጹ፤

5. እውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያልተላበሰ ተግባር የሚያመጣውን መጥፎ ውጤት ግለጹ፤

# ምዕራፍ ሁለት
## ለህግ ተገዥነት

የመማር ዉጤቶች: ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:

- ስለ ህግ ተገዥነት ትርጓሜ ትሰጣላችሁ፤
- ስለ ህግ ተገዥነት አስፈላጊነት ትገልጻላችሁ፤
- ለህግ ተገዥ የሆኑ ሰዎች ባህሪያት ታሳያላችሁ፤
- ለህግ ተገዥ ያለመሆን የሚያመጣዉን ተፅዕኖ ታብራራላችሁ፤

## መግቢያ

ህግ ማለት ምን ማለት ነው? ሰዎች ለምን ህግን ያከብራሉ? በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ከህግ ተገዥነት ጋር ተዛማጅንት ያላቸዉን ጉዳዮች እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ ምዕራፉ በህግና ህግ ተገዥነት ላይ በመግቢያነት ይጀምራል፡፡ ቀጥሎም የህግ ተገዥ ዜጋ መገለጫዎች እና የህግ ተገዥነት ጠቀሜታ ላይ ገለፃ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም ለህግ ተገዥ አለመሆን ውጤት ገለፃ ይደረጋል፡፡

### 2.1 የህግ ተገዥነት ምንነት

**ተግባር2.1**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ተወያዩበት፡፡

1) በአንድ ሀገር ዉስጥ ህግ ያለዉን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፤

2) ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ግዴታዎች ምንድን ናቸዉ?

3) ተማሪዎችን ለህግ ተገዥነት የሚያለማምዱ ተግባራትን በምሳሌ አቅርቡ፤

የህግ ተገዥነት እሴቶችን ለመረዳትና ለማክበር መጀመሪያ ስለ ህግ ተፈጥሮና ዓላማ መማር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ህግን ሳይረዱ ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ መሆን ስለማይቻል ነው፡፡

ህጎች በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ ወይም ሃገር ዉስጥ ያለ ማንኛዉም ሰው ሊከተላቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር ህጎች ናቸው፡፡ እነዚህ ህጎች ለዜጎች መብቶቻቸውንና ግዴታቸውን የሚያሳዉቁ ናቸው፡፡በአንድ ሃገር ዉስጥ የትኛዉም ህግ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

በየትኛውም ሀገር ህጎች ቋሚ፣ተለዋዋጭና ወጥነት ያላቸው እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ቋሚ ስንል ህጎች ለረዥም ጊዜ መቆት አለባቸው ይህም ዜጎች ከህጎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራቸውና በደንብ እንዲያዉቋቸው ይረዳል፡፡ በሌላ በኩል ተለዋዋጭ መሆን አለባቸው ሲባል ማህበረሰቡ በጊዜ ብዛት ሊለዉጣቸው ይችላል ማለት ነው፡፡ ከመቶ አመታት በፊት በኢትዮጵያ ጥቂት ተሽከርካሪዎች ነበሩ፡፡ በመሆኑም የመንገድ ትራፊክ ህግ ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ አልነበረም፡፡ ዛሬ በሌላ በኩል የተሽከርካሪ ቁጥር መጨመር የተሽከርካሪ ቁጥር መጨመር የተሽከርካሪ አደጋ ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ስለዚህ በሀገሪቱ የትራፊክ አደጋ የሚቀንሱ ህጎች ትልቅ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም ህጎች ወጥነት ያላቸው መሆን አለባቸው ሲባል በሀገሪቱ ለሚኖር ለማንኛውም አካል እኩልነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡

> **ለህግ ተገዥነት ማለት ዜጎች የሃገሪቱን ህግ ለማክበር ያላቸው ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይም በፈቃደኝነት ህግን ላለመጣስ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡ ህጎች በህዝቡ ተቀባይነት ያላቸውና በመንግስት የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ ስለዚህ የህግ ተገዥነት በህዝቡ መልካም ፍቃድ መመስረት አለባቸው፡፡**

የሀገሪቱን ህግ ማወቅ የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው፡፡ ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ህጉ ተግባራቸውን ለመምራት ማድረግ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ነገሮች በተመለከተ መመሪያ የሚሰጥ መሆኑን ይገነዘባሉ፤ደንቦችን የማወቅና የማክበር ግዴታ እንዳልባቸዉም ይረዳሉ፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ህዝቦች በቋንቋ፣ በሃይማኖት ወይም በባህል ይለያያሉ፡፡ ልዩነቱም በአላማቸው፣ በቤተሰብ የኋላ ታሪክ፣ ወይም ፍላጎት ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የኛ ፍላጎት ከሌሎች ፍላጎት ጋር ሊጋጭ ይችላል ፡፡ ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ግን እነዚህን ፍላጎቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንደሚፈቱ ያምናል፡፡ ሰላም በማህበረሰቡ ውስጥ በመንግሰት ባልስልጣናት ብቻ አይጠበቅም፡፡ ሰላምን ማስጠበቅ የሁሉንም ሰው ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

ተግባር 2.2

**የቡድን ስራ: ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን የሚከተለዉን ታሪክ አንብባችሁ ከተወያያችሁ በኋላ ከታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

ታምሩ የአራት ልጆች አባት ነው። በየቀኑ ስራ በጥዋት ይሄድና ማታ 6:30 ይመለሳል። ከስራ በኋላ ከልጆቹ ጋር ጊዜውን አብሮ ማሳለፍ ይፈልጋል። ስራዉም በልብስ መደበር ዉስጥ የሽያጮ ሰራተኛ ነዉ። አለቃዉ ያለዉን ሁሉ ለመስራት ይጥራል። አንድ ቀን አለቃው ለደንበኞቹ ያለደረሰኝ ልብስ እንዲሸጥ ነገረዉ። ታምሩም ይህ ተግባር ሃገር እንደሚጎዳ አያዉቅምና አደረገዉ።ባለስልጣን መስሪያ ቤቱም በቁጥጥር ስር አዉሎ ወደ እስር ቤት አስገባው።

ታምሩ እንደ ዜጋ ያልተወጣቸውን ግዴታዎች አብራሩ

- ታምሩ አለቃዉ ያለደረሰኝ ልብስ ሽጥ ሲለው ምን ማድረግ ነበረበት?
- ታምሩ ህግን አለማወቁና ችላ ማለቱ ከቅጣት አድኖታል?

## 2.2 የህግ ተገዥነት አስፈላጊነት

ተግባር 2.3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ተወያይታችሁ መልሱ።

የህግ ተገዥነት አስፈላጊነት ምንድን ነው?

1) የህግ ተገዥነትን ለማስጠበቅ ዜጎች ሊወስዷቸው የሚገቡ ተግባራት ላይ ተወያዩ፤

2) በትምህርት ቤታችሁ የህግ ተገዥነት ባህሪያትን በምሳሌነት አቅርቡ፤

የህግ ተገዥነት በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።አነዚህም ዜጎች:-

- **ሙሉ ነፃነትን ማግኘት**: የህግ ተገዥነት ዜጎች ሙሉ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ይረዳል። ነፃነት ህግ ከለላ የሚሰጠው የህይዎት መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ነፃነት ሰዎች ይጠቀመናል ባሉት የአኗኗር ዘዴ እንዲኖሩ ይረዳል። ማንኛውም ሰው የፈለገዉን የሃይማኖት ቡድን አባል የመሆን፣የራሱን ንግድ ስራ የመስራት ወይም በፖለቲካ የመሳተፍ መብት ነፃነት አለው። የትኛውም ሰው ይህን ነፃነት የመጣስ መብት የለዉም። ይህም ሲሆን ግን ገደቦች ይኖራሉ። የግለሰቦች ተግባር የሌሎችን መብቶች በአሉታዊ መልኩ እንዳይጥሱ ሃላፊነት አለባቸው። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የእያንዳንዱ ዜጋ መብት ተመሳሳይ ነው።ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች የሌሎችን መብቶች ያከብራሉ።

- **ሰላምን መጠበቅ**: የህግ ተገዥነት በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን ለመጠበቅ ዋና አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች ስለ ሰላም በቂ ግንዛቤ ከሌላቸው የቀን ተቀን ተገባራቸውን ለማከናወን አያስችላቸውም፡፡ ሰላም ከሌለ ትምህርት ቤት መሄድ፣ ከጓደኛ ጋር መጫወት ወይም ከቤተሰብ ጋር መዝናናት አይቻልም፡፡
- **ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል**: ኢትዮጵያ ለእድገት እምቅ ሃይል ያላት ሀገር ናት፡፡ በብዙ የተፈጥሮ ሃብቶች፣ጥሩ የአየር ፀባይ እና በበርካታ ብርቅየ እንሰሳት የታደለች ሃገር ናት፡፡ በይበልጥም ኢትዮጵያ ትልቅ ነገር መስራት የሚችሉ በርካታ ወጣቶች ያሏት ሃገር ናት፡፡ይህን ሃይል ለመጠቀም ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ፍትሃዊ ሃብት ክፍፍል ሊኖር የሚችለው ዜጎችና መንግስት ተግባራትን ህግን ተከትለው ሲሰሩ ነው፡፡ ስለሆነም ፍትሃዊ ሃብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ የህግ ተገዥነት አስፈላጊ ነው፡፡
- **ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ**: ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ የሃገሪቱ ህግ የሃገር ሉዓላዊነት ማስጠበቂያ ዘዴ እንደሆነ ይረዳል፡፡ ሉዓላዊነት ማለት ከጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ራስን ማስተዳደር ማለት ነው፡፡ ሉዓላዊነት የነፃነት ምልክት ነው፡፡

**የዜጎችን ፍላጎት መጠበቅ**: ህጎች የህዝቦች ይሁንታ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ህጎች ህዝቦች ከመንግስት ጋር በፈቃደኝነት የሚያደረጓቸው ዉሎች ናቸው፡፡ ስለዚህም ስዎች ህግን ሲጥሱ የራሳቸውን ጥቅም ያጣሉ፡፡ ከነዚህ ጠቀሜታዎች በተጨማሪ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ህግ ራሳቸውን ካልተገባ የመንግስት ተግባራት እንደሚጠብቃቸው ይረዳሉ፡፡ ህጎች የመንግስትን ስልጣን ይገድባሉ፡፡ ይህም ማለት ህጎች ዜጎች በመንግስት ላይ አመኔታ ባጡ ጊዜ ተጠያቂ እዲሆን ይረዳሉ፡፡.

ህጎች ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ክልከላ ያደርጋል፡፡ ሰዎች ወንጀል ከፈፀሙ ህግ አጥፊዎችን ለመቅጣት አስፈላጊዉን ዘዴ ይጠቀማል፡፡ በዚህም መንገድ ሰላማዊ የማህበረሰብ እንቅስቃሴ እንዲኖር ይረዳል፡፡ ለምሳሌ ንብረት ዘራፊዎችን ተጠያቅ የሚያደርግ የመንግስት አሰራር ከሌለ አንድ ባለ ሱቅ ሱቁን ከፍቶ ንብረቱን ለመሸጥ አይችልም፡፡

## 2.3 ለህግ ተገዥ የሆነ ሰው ባህሪያት

**ተግባራት 2.4**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

1) ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ሃላፊነቱን ለመወጣት የሚወስዳቸውን ተግባራት ግለፁ፡፡

2) ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ በማኀበረሰቡ ዉስጥ ያለዉን ሃላፊነት ዘርዝሩ፡፡

3) ለህግተገዥየሆነዜጋማስወገድ ያለበት ተግባራትን በምሳሌነት ዘርዝሩ፡፡

ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ህጎች የግልን ጥቅም እደሚያስጠብቁ ይረዳል፡፡ በሌላ አባባል እነዚህ ህጎች ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ የአንድ ሃገር ህጎች በነዋሪዉ ህዝብ ተቀባነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን አንዴ ወደ ትግበራ ዉስጥ ከገቡ በኋላ አስገዳጅ ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት ማንኛዉም በሃገሪቱ የሚኖር አካል ህጎችን ማክበር አለበት፡፡ ህጎች ሰዎች እንደፈለጉ መርጠው የሚያከብሯቸዉና የሚተዋቸዉ አይደሉም፡፡ ህጎች ሲመቹን ብቻ የምናከብራቸዉ አይደሉም፡፡ ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ ህጎች በሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜ መከበር እዳለባቸዉ ግንዛቤዉ አለው፡፡

በተመሳሳይ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች የመብታቸውንና ሃላፊነታቸዉን ገደብ የማወቅ ግዴታ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡ ህግን አለማወቅ ከቅጣት እንደማያድናቸውም ይገነዘባሉ፡፡ ህግን ባለማወቅ ያላከበረ ህግን እያወቀ ካላከበረ ጋር እኩል ጥፋተኛ ነው፡፡ የሀገሪቱን ህግ የማወቅና የማክበር የሁሉም ማህበረሰብ አባል ግዴታ ነው፡፡

ህጎች የህዝቦች ይሁንታ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የሃገሪቱን ህግ መጠበቅ የህዝቦችን ይሁንታ መጠበቅ ነው፡፡ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ህግ ሲጣስ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንዳለባቸው ያዉቃሉ፡፡ ይህም እንደ ግዴታቸው ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም ጥቅም ለማስጠበቅ ነው፡፡

ህጎች የማህበረሰብ ለዉጥ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሁላችንም የማህበሰብ ለዉጥ እንፈልጋለን፡ ፡ ሃገራችን ከውጭ ዕርዳታ ጥገኝነት ነፃ እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ህጉም ማህበረሰባዊ ሽግግር እዲኖር ይፈቅዳል፡፡ ስለዚህም ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ የሃገሪቱን ህግ መጠበቅ ለወደፊት ተሻለ ነገር ያመጣል ብሎ ይገነዘባል፡፡

## 2.4 ለህግ ተገዥ አለመሆን የሚያስከትላቸው አሉታዊ ውጤቶች

**ተግባር 2.5**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ

1) ህግ የሌለበት ማህበረሰብ ምን እንደሚመስል ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

2) የህግ ተገዥ አለመሆንን ለመታገል ዜጎች ያለባቸው ሃላፊነቶች ምንድን ናቸው?

## የማነቃቂያ ጥያቄዎች

**ተግባር 2.6 የሚከተለዉን ታሪክ አንብባችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡**

አንድ ወጣት ከአባቱ ጋር ይጓዝ ነበር፡፡ ከኮረብታው ላይ እንደደረሱ ልጁ ከበስተጀርባው የሚመጣ ድምጽ እንዳለ ሰማ፡፡ በመሆኑም ‹‹ ሄሎ›› እያለ ጮኸ፡፡ ‹‹ ሄሎ›› የሚል ተመሳሳይ ምላሽ ሰማ፡ ፡ ልጁም ‹‹ እዚያ ማን አለ ?›› አለ፡፡ ልጁ በሰማዉ ድምፅ ተናደደና ‹‹ ፈሪ ነህ›› አለ፡፡ እንደገና ተመሳሳይ ምላሽ ሰማ፡፡ አባቱ በጥንቃቄ የሚያደርገዉን ነገር ሁሉ ይከታተለዉ ነበር፡፡ እሱም ድምጹ የገደል ማሚቶ እንደነበርና ህይወትን እንደሚገልፅ ነገረው፡፡ከዚያም አባቱ ‹‹ጎበዝ›› ብሎ ሲጮህ ተመሳሳይ ምላሽ መጣ፡፡ አባቱም ለልጁ አንደዚህ አለው: “ከዓለም የምንቀበለው ለዓለም የሰጠነውን ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡” ሰላማዊ ማህበረሰብ ከፈልግን ለማህበረሰቡ ሰላም መስጠት አለብን፡፡ የህግ ተገዥ ማህበረሰብ ከሆንን እና ማህበረሰብ ዉስጥ መኖር ከፈልግን መጀመሪያ እኛ ለህግ ተገዥ መሆን አለብን፡፡

1. አባቱ“ከዓለም የምንቀበለው ለዓለም የሰጠነውን ተመሳሳይ ነገር ነው”? ሲል ትክክል ነበር?ለምን?

2. የሃገራቸው ህግ እንዲከበር ለማረጋገጥ ከዜጎች የሚጠበቁት ተግባራት ምንድን ናቸው?

ለህግ ተገዥነት በሃገር ውስጥ መልካም ስዎች እንዲሰሩ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡.ለህግ ትገዥ አለመሆን በርካታ አሉታዊ ዉጤቶችን ያስከትላል፡፡

**ጥቂት አሉታዊ ዉጤቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡**

## 2.4.1 የሰላም እጦት

ሰላም የህግ ተገዥነት ዋነኛ ዉጤት ነው፡፡ ነገር ግን ሰላም ማለት ግጭት ያለመኖር ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የግንኙነቶች ዉስታዊ ጥቃቶች አለመኖር ማለት ነው፡፡ ሁለት የሰላም አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም አሉታዊ ሰላምና አዎንታዊ ሰላም ይባላሉ፡፡ የሰላማዊትንና ዳንኤልን ምሳሌ እንመልከት.

## ሀሳብ ማፍለቅ

ዳንኤልና ሰላማዊት ወንድምና እህት ናቸው። የቤተሰቦቻቸውን በጎች በየተራ ይጠብቃሉ። እሁድ ወደ አያቶቻቸው ቤት ከመሄዳቸው በፊት ዳንኤል ቅዳሜ በጎችን ጠብቋል። ሰኞ እለት የሚከተለው ንግግር ነበራቸው።

**ዳንኤል**:"ዛሬ በጎችን መጠበቅ ያንቺ ተራ ነው።"

**ሰላማዊት**:"አይደለም! የኔ ተራ ትናንት ነበር፣ ስለዚህ ያንተ ተራ ነው" ሁለቱ እህትና ወንድም

እናታቸው ወደ ክፍል ስትገባ ይጨቃጨቁ ነበር።

**እናት**:"እናንተ አትጨቃጨቁ፤ እኔ በጣም ደክሞኛል ትንሽ መተኛት እፈልጋለሁ፤ከዚህ በኋላ ጭቅጭቅ ብሰማ ሁለታችሁም ትቀጣላችሁ። ልጆችም የእናታቸዉን ትዕዛዝ ፈርተዉ ፀጥ ቢሉም መግባባት ግን አልቻሉም።ይህ አሉታዊ ሰላም ይባላል። ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ሰላማዊት ወደ ወንድሟ ሄዳ እንደዚህ አለችው።

**ሰላማዊት**:"ዛሬ በጎችን እጠባቃለሁ፤ ይቅርታ ቅድም ጮህኩብህ፤ ከአንተ ጋር መጣላት አልፈልግም። ይህን ሲሰማ ዳንኤል እንደዚህ አለ፡

**ዳንኤል**:"እኔ እረዳሻለሁ፤እኔም ከአንቺ ጋር መጣላት አልፈልግም" ወንድምና እህት አለመግባባታቸውን

ፈቱና እንደገና አብረዉ መጫወት ጀመሩ፤ መግባባታቸውም ዘላቂ ሰላም ያመጣላቸዋል።

- የሁለቱ አለመግባባት ዉጤት ምን ነበር?
- ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መስራት ጥቅሙ ምንድን ነው?

## 2.4.2 የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት

ህጎች ተግባር ላይ ካልዋሉ የህዝቦች ህይወት፣ነፃነትና ንብረት ሊጠበቅ አይችልም። ሰዎች ፍላጎታቸዉን በራሳቸው ለማስጠበቅ ይገደዳሉ። ይህ ሁኔታ ወደ ማይቀር ብጥብጥ ይመራል፤ ጉልበት ያለዉ ደካማዉ ላይ ሃይሉን ያሳያል። ጉልበተኛውም ከሱ የበለጠ ሌላ ጉልበተኛ ላለመምጣቱ ዋስትና የለዉም። ስለዚህ ህይዎታችን በፍርሃትና በብጥብጥ የተሞላ ይሆናል።

## 2.4.3 ሙስና

ሙስና ማለት ስልጣን ባላቸው ግለሰቦች የሚፈፀም ያለመታመን የወንጀለኝነት ባህሪ ነው። ( በዋነኛነት በመንግስት ባለስልጣናት)። ሙሰኛ ባለስልጣናት ስልጣናቸውን ህዝብ ለማገልገል ሳይሆን ራሳቸውን ለመጥቀም ይሰሩበታል። የተለያዩ የሙስና መገለጫዎች አሉ። እነሱም፡

- **የዝምድና ወገንተኝነት፤** ይህ ማለት ስልጣንን ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ጓደኛን ወይም ቤተሰብን መጥቀም ማለት ነው፡፡
- **ጉቦ መስጠት:** ይህ ማለት ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለባለስልጣናት ገንዘብ መስጠት ማለት ነው፡፡
- **ማጭበርበር:** ይህ ማለት አገልግሎት ሳይሰጡ በተሳሳተ መንገድ ገንዘብ መውሰድ ማለት ነው፡፡

### 2.4.4 የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ

የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ የሰውን ልጅ አእምሮና አካል የሚጎዳ በሽታ ነው፡፡ ዕፅ መጠቀም ህጋዊና ህገ-ወጥ መድሃኒት አጠቃቀምን መቆጣጠር አለመቻልን ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ አልኮል፣ጫት፣ ሲጃራ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሰዎች በነዚህ ዕፅ ሱስ ዉስጥ ሲገቡ ሌሎችን መቆጣጠር አይችሉም፡፡ ለህግ ተገዥ አለመሆን ወደዚህ ሱስ ዉስጥ ይከታል፡፡

### 2.4.5 ህገ-ወጥ የህፃናት ዝውውር

ህገ-ወጥ የህፃናት ዝውውር ማለት ህፃናትን ለአስገዳጅ ስራና ወሲብ ተግባራት ማሰማራት ማለት ነው፡፡ ህገ-ወጥ የህፃናት ዝውውር ህይወታቸውን በመጥፎ ሁኔታ እንዲመሩ ያጋልጣቸዋል፡፡ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማለትም ምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳትና የተመቻቸ የቤተሰብ ፍቅር የማግኘት መብታቸውን ያጣሉ፡፡ ልጆች በተለያዩ ምክንያቶች ለዚህ ችግር ይጋለጣሉ፡፡ የመጀመሪያው በወላጆቻቸው ሊሸጡ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ሰዎች በሀሰት ትምህርት እናስተምራችሁ ብለው ቃል ገብተው ይወስዷቸዋል፡፡

ልጆች በተለያዩ ምክንያቶች በህገ-ወጥ መንገድ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ለሴተኛ አዳሪነት፣ለቤት ውስጥ ስራ፣ እና ለግብርና ስራ ናቸው፡፡ ይህ ችግር በአደጉትም ሆኑ ባላደጉት ሃገሮች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳል፡፡ ልጆችንም ለአካላዊና ስነ-ልቦናዊ ችግሮች ይዳርጋል፡፡ የህፃናት ህገ-ወጥ ዝውውር ሊያስቆም የሚችለው ሁሉም ሰው ህግን ሲያከብር ነው፡፡ ሰዎችም ልጆችን ከህገ-ወጥ ዝውውር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች እንደዚህ ያሉ ተግባራት ሲፈፀም ሲያዩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል መረጃ ይሰጣሉ፡፡

## 2.4.6 ግብር ስወራ

የግብር ስወራ ማለት ግብርን ላለመክፈል የሚደረግ ህገ-ወጥ ሙከራ ማለት ነዉ፡፡ እነዚህ ተግባራት በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡ የግብር ስወራ የሚያካትተዉ ሀሰተኛ የግብር ሰነድ፣ገቢን አሳንሶ ማቅረብና የተጋነነ ወጭ ናቸው፡፡ የግብር ስወራ መንግስት መሰብሰብ የሚችለውን ገቢ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡መንግስት ለዜጎች የሚያቀርበው አገልግሎቶች በገቢ ግብር ይወሰናል፡፡ ስለዚህ የግብር ስወራ ተግባራት በሁሉም ሰው ህይወት ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል፡፡ የግብር ስወራ ለመፈፀም የሞከሩ ዜጎች በገንዘብ ወይም በእስራት ይቀጣሉ፡፡

## 2.4.7 የነፃነት እጦት

ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች በፈለጉት የአኗኗር ህይወት ለመኖር ነፃ ናቸው፡፡ የራሳቸውን ሃይማኖት የማምለክ ፣ ባህላቸውን የማሳደግና በየትኛዉም የሀገራቸው ክፍል ለመኖር ነፃ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ህግን ካላከበረ ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ሊነጠቅ ይችላል፡፡ ምክንያቱም መንግስት ህግ በማያከብሩት ላይ ቅጣት ስለሚወስድ ነው፡፡ ቅጣቱ እንደጥፋቱ ይወሰናል፡፡ አንደኛው የቅጣት ዘዴ አጥፊውን በእስር ማቆየት ነው፡፡ ማሰር ሲባል እስረኛው የትኛውም ቦታ መንቀሳቀስ አይችልም ወይም ቤተሰቡን እንደፈለገ ማየት አይችልም ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በእስር ያሉ ሰዎች ነፃነታቸውን ያጣሉ፡፡

## 2.4.8 የፍትህ እጦት

ግለሰቦች በማህብረሰብ ዉስጥ አንዱ ከአንዱ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ ህግን አክባሪ ማህበረሰብ ይህን ችግር ለመፍታት ዘዴዎች አሉት፡፡ ህጎች ዜጎች ማድረግ የሚችሉትንና የማይችሉትን ያሳዉቃል፡፡ አንድ ሰው ሌላዉን ሰው ጎድቶ ቢገኝ ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ ቅጣት ይቀጣል፡፡ ህግን እየጣሱ የፈለጉትን የሚያደርጉ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ላይ መጥፎ ነገር ያመጣሉ፡፡ የህንዱ ፈላስፋ ማህተመ ጋንዲም እንደዚህ ብሏል፡፡“ጥፋትን በጥፋት ማሰተካከል አለምን ባዶ ማስቀረት ነው፡፡”

## 2.5 የምዕራፍ ማጠቃለያ

የህግ ተገዥነት ማለት የሀገሪቱን ህግ ለማክበር ዜጎች ያላቸው ተነሳሽነት ማለት ነው፡፡ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች እነዚህን ህጎች ማወቅ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡ ህጉም ለእነሱ ጥበቃ ለማድረግ እንደተዘጋጁ ያዉቃሉ፡፡

የህግ ተገዥነት ሰላምን በማህበረሰቡ ዉስጥ ለማስጠበቅ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ሰላም እያንዳንዱ ማህበረሰብ በሰላምና መተሳሰብ እንዲኖር ያስችላል፡፡ ይህም ለማህበረሰብ እድገት ወሳኝ ነው፡፡መንግስት ብቻዉን ህግ ማስጠበቅ እንደማይችል ዜጎች ሊረዱ ይገባል፡፡ የሁሉንም ዜጋ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ህግን የሚያከብሩት ለራሳቸው ጥቅም እንደሆነ ይረዳሉ፡፡ የህግ ተገዥነት የዜጎችን ህይወታቸውን፣ ነፃነታቸውን እና ንብረታቸውን ይጠብቅላቸዋል፡፡ ህግ በማይከበርበት ማህበረሰብ ፍትህና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል አይኖርም፡፡ ስለዚህ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ህግን ከመጣስ ይከላከላሉ/ ይቆጠባሉ፡፡

### ቁልፍ ቃላት

- ሉዓላዊነት: ሃገርን የመምራት ሙሉ ስልጣን
- ለህግ ተገዥ የሆነ ዜጋ: የሀገሪቱን ህግ የሚያከብር ዜጋ
- የግል ፍላጎት: የራስን ጥቅም ማስቀደምና ስለሌሎች ጥቅም አለመጨነቅ
- ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል: የሀገሪቱን ሀብት በእኩል ማግኘት
- ሙስና: ታማኝ አለመሆን፣ ህገ-ወጥ ተግባር፣ በተለይም የመንግስት ባለስልጣናት ላይ የሚታይ ተግባር
- ህገ-ወጥ የህፃናት ዝዉዉር: ልጆችን መበዝበዝና በአስገዳጅ ስራ ላይ ማሰማራት

መልመጃ 2.1

ትእዛዝ አንድ፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡና ትክክል የሆነዉን ዓረፍተነገር "እውነት"ትክክል ያልሆነዉን ደግሞ"ሃሰት"በማለት መልሱ፡፡

1) የህግ ተገዥነት ማለት ዜጎች የሃገሪቱን ህግ ለማክበር ያላቸው ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ማለት ነው፡፡
2) ሰላም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሊጠበቅ የሚችለዉ በመንግስት ብቻ ነው፡፡
3) ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች የመብታቸውንና ሃላፊነታቸዉን ገደብ የማወቅ ግዴታ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡
4) የህግ ተገዥነት አለመኖር ሰዎች የፈለጉትን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

4) የህግ ተገዥነት  አለመኖር ሰዎች የፈለጉትን እንዲያገኙ  ያስችላቸዋል፡፡

5) ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል አንዱና ዋነኛው የህግ ተገዥነት  ዓላማ ነው፡፡

ትእዛዝ ሁለት:  ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን  ፊደል  ምረጡ፡፡

1)  ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከህግ ባህሪያት ውስጥ አይመደብም
(ሀ)ቋሚነት

(ለ) የፍትህ እጦት

(ሐ) ተለዋዋጭነት

2)  ከሚከተሉት ዉስጥ የህግ ተገዥነት  ጠቀሜታ ያልሆነዉ የቱ ነው?
(ሀ) ሰላምን ማሰጠበቅ

(ለ) ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ

(ሐ) የሰብዓዊ መብት ጥሰት

3) ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዥ የሆኑ ዜጎች ባህሪ ያልሆነው የቱነው?

(ሀ) መብታቸውን እና የግል ፍላጎታቸውን ለማስጠበቅ የተዘጋጁ ናቸው

(ለ) መብታቸዉንና ግዴታቸውን ያዉቃሉ

(ሐ) መልሱ አልተሰጠም

4) የሰውን አእምሮ እና አካል የሚጎዳ በሽታ__ ይባላል፡፡

(ሀ) የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ

(ለ) ሙስና

(ሐ) የግብር ስወራ

ትእዛዝ ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶቻቸውን በመፃፍ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ

1) ለህግ ተገዥነት ማለት ምን ማለት ነው?

2) ለህግ የሚታዘዙ ዜጎች ጥቂት ባህሪያትን ዘርዝሩ፤

3) በማህበረሰብ ውስጥ ለህግ ተገዥነት ስላለዉ አስፈላጊነት ተወያዩ ፤

4) ለሕግ ተገዥ አለመሆን ስለሚያስከትላቸው ችግሮች ከጓደኞችሁ ጋር ተወያዩ።.

# ምዕራፍ ሦስት
# መልካም ባህሪ

የመማር ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- መልካም ባህሪ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታስረዳላችሁ፤
- የመልካም ባህሪ ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች ያላቸውን ባህሪያት ትገልጻላችሁ፤
- መልካም ባህሪ የመያዝ አስፈላጊነትን ዋጋ ትረዳላችሁ፤
- መልካም ባህሪን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ታሳያላችሁ፤
- መልካም ባህሪ ያለመያዝ አስከፊ ውጤቶችን ትገልጻላችሁ፤

## መግቢያ

ጥሩ ባህሪ ማለት ምን ማለት ነው? የትኞቹ ግብዓቶች ጥሩ ባህሪ ለማሳደግ ያግዛሉ? በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ ጥሩ ባህሪ ማስተማር ለምን አስፈለገ? ይህ ምዕራፍ ስለ ጥሩ ባህሪ ምንነትና ጥቅሞች ለተማሪዎች ለማስተማር ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡ ምዕራፉ በዋናነት የሚያተኩረው ጥሩ ባህሪ ያለው ሰው የሚኖረው ባህሪና መለያዎች ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም እንዴት መልካም ባህሪን ማሳደግ እንደሚቻል ለማሳየት ይሞክራል፡፡ በምዕራፉ ማጠቃለያ ተማሪዎች የመልካም ባህሪ መጓደል በቤተሰብ፣ በትምህርት አካባቢ ውስጥ እና በማህበረሰብ ላይ የሚያመጣውን አስከፊ ውጤት ይረዳሉ፡፡

## 3.1 የመልካም ባህሪ ምንነት

ተግባር 3.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1) መልካም ባህሪ ማለት ምን ማለት ነው?

2) ጥሩ እንደሆኑ የሚታሰቡ ጥቂት ባህሪያትን ዘርዝሩ፤

የጥሩ ባህሪ ምንነትን ለመረዳት እንዲቻለን በቅድሚያ ባህሪ ማለት ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚቀረጽ ማወቅ ጠቃሚ ግብዓት ይሆናል። ባህሪ ሰዎች ነገሮችን በሚፈጽሙበት መንገድ በተለይም ከሌሎች ሰዎች ጋር መስተጋብር ውስጥ ሲገቡ ይገለጻል።



ምስል 3.1: ተማሪዋ ከክፍል ለመውጣት መምህር ስታስፈቅድ

መልካም ባህሪያት የሰዎች እምነትቶችና አስተሳሰቦች ውጤቶች ናቸው። ሰዎች በሚናገሩበት ወቅት አንድ ድርጊት ሲፈጽሙ እና ከሌሎች ጋር ግንኙነት ሲኖራቸው ባህሪያቸው አብሮ ይገለጣል። መልካም ባህሪ ያለው ሰው ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉለት የሚፈልገውን እርሱም ለሌሎች ያደርጋል። ይህን በተመለከተ ተቀባይነት ያለውና ለመከተል ቀላል የሆነ አንድ አባባል አለ።

## አስታውሱ!

“ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን አናንተም እንዲሁ አድረጉላቸው”

በመቀጠል የመልካም ባህሪ ጥቂት ምሳሌዎች ከታች እንደሚታዩት ተዘርዝረዋል።

### የመልካም ባህሪ ምሳሌዎች

- በራስ በተማመን።
- ትሁት መሆን።
- ፈቃድን መጠየቅ።
- ጥሩ ጓደኞችን መምረጥ
- ላላቸው ነገር አመስጋኞች መሆን
- ጠንካራ ሰራተኝነትን ማድነቅ
- ትክክል ለሆነው ነገር መወገን
- ለሰሩት ስህተት ይቅርታን መጠየቅ

መልካም ባህሪ የብዙ ምክንያቶች ድምር ውጤት እንደሆነ ይታሰባል። ከነዚህም መካከል ከታች የተጠቀሱት ግብዓቶች መሰረታዊ ተደርገው ይወስዳሉ፡

1) ቤተሰብ፡ ወላጆችና ታላላቅ ወንድሞች/እህቶች እድሚያቸው ለጋ ለሆኑ ወጣቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። እነርሱን እንደ ተምሳሌት ስለሚወስዱ የታላላቆቻቸውን ማናቸውንም ድርጊት እንደ ትክክል አድርገው ይወስዱታል። በመሆኑም በአቅራቢያቸው ያሉ ሰዎች ሲያደርጉ የሚያዩትን ድርጊቶች፣ልማዶችንና ንግግሮችን እንደሚኮርጁ ይጠበቃል።

2) ጊዜ፡ የለጋ ወጣቶች ባህሪ በጊዜ ቆይታ ውስጥ ይቀረጻል። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ወጣት ልጆች በአቅራቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን ባህሪ ይወርሳሉ። በጊዜ ሂደት ውስጥ ሲኮርጇቸው የቆዩት ባህሪያት ቀስ በቀስ የራሳቸው ባህሪ ወደ መሆን ይሸጋገራሉ። እነዚህ ተጽእኖዎች የሚመጡት ከቤተሰብ አባሎቻቸው ብቻ ሳይሆን በዙሪያቸው ከሚገኙ ሌሎች ግለሰቦችም ጭምር ነው።

3) ምርጫ፡ ባህሪ በምርጫ የሚመጣ ውጤት ነው። ተማሪዎች መረዳት የሚገባቸው ነገር ቢኖር መሆን የሚፈልጉት ማንነት መምረጥ እንደሚችሉ ነው። እያንዳንዱ ሰው መጥፎ ወይም ጥሩ ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል የመምረጥ ብቃት አለው።

## 3.2 መልካም ባህሪ ያለዉ ሰው መገለጫዎች

**ተግባር 3.2**

ከታች ለተሰጡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ። ከተቻለ መልሳችሁን ከወላጆቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1) መልካም የሆነ ሰው የሚያሳያቸው ባህሪያት የትኞቹ ናቸው?

2) በትምህርት ቤታችሁ የጥሩ ባህሪ መገለጫ መሆን የሚችሉ ምሳሌዎችን መጠቀስ ትችላላችሁ?

መልካም ባህሪ ያለው ሰው ለሌሎች ደግነትን በማሳየት እና ድጋፍ በመስጠት ይታወቃል። የመልካም ሰው ባህሪያት ጠቃሚ የሆኑ ልዩ መገለጫዎች አሉት። የመልካም ባህሪን ምንነትን የሚያሳዩ የተለመዱ ምሳሌዎች አሉ።

- <u>ምሉዕነት</u>፡ ጠንካራ የግብረ ገብ መርሆች ያሉትና እውነት የሚከተል፤
- <u>ሀቀኝነት</u>፡ ታማኝነትና ሀቀኝነትን መተግበርና ውሸት መናገርን፣ አጭበርባሪነትን እና ሌብነትን ማስወገድ መቻል፤
- <u>ታማኝነት</u>፡ እምነት የሚጣልበት፤ ድርጊቶችን እና ውሳኔያችን በእምነት መምራት መቻል፤
- <u>ተጠያቂነት/ ሃላፊነት መውሰድ:</u> ከተግባራችንና ከሃላፊነታችን የሚመነጩ ተጠያቂነቶችንና ውጤቶችን በሃላፊነት ለመውሰድ ዝግጁ መሆን። ተጠያቂነት ማለት ለፈጸምነው ተግባር ሃላፊነትን ለመውሰድ መገደድን፣ማብራሪያ መስጠትንና የድርጊታችንን ትክክለኛነት ማስረዳትን ይጨምራል።
- <u>ራስን መቆጣጠር</u>፡ አላስፈላጊ ውስጣዊ ግፊትን፣ ስሜትን እና ምኞትን የመቆጣጠር ብቃት፤

የመልካም ሰው መለያ የሆኑ ባህሪያትን የበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ አስገቡ።

### 3.2.1 የሌሎችን ንብረት ማክበር/መጠበቅ

> ማክበር ማለት ሌሎች እንዲያደርጉልህ በምትፈልገው መንገድ ለሌሎችም እንደዚሁ ማድረግ ማለት ነው። ሰዎች እርስ በእርሳቸው ሲከባበሩ ንግግራቸው በትህትና የተሞላ ይሆናል። ተማሪዎች ማስታወስ የሚገባቸው ነገር ቢኖር ክብር ከአንደኛው ወገን ብቻ የሚጠበቅ ሳይሆን ከሁለቱም አካለት መምጣት ያለበት መሆኑን ነው። አንድ ተማሪ ሌሎች እኩዮቹን ማክበር እስካልቻለ ድረስ ከእነርሱ ክብር ማግኘት አይቻለውም።

**ተግባር 3.3**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ። ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

1) ማክበር የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?
2) የሌሎችን ንብረት ማክበር ማለት ምን ማለት ነው?



ምስል 3፡2 ተማሪው ጠፍቶ የተገኘን ንብረት ለባለቤቱ ሲመልስ

ህግ አክባሪነት ሌላው ክብር የመስጠት መገለጫ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ነገር ቢኖር ህጉን ላወጡት አካላት ክብር መስጠት ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ተማሪ ለትምህርት ቤቱ ህጎች ተገዥ ከሆነ ለትምህርት ቤቱ ክብር አለው ማለት ነው፡፡

ከአንተ ጋር የሚገኙ ነገሮች ሁሉ የአንተ ንብረት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ መልካም የሆነ ሰው ሌሎች ንብረቱን እንዲያከብሩለት እንደሚፈልግ ሁሉ የሌችንም ንብረት በማክበር ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ቤት፣የህዝብ እና የማንኛውንም ሰው ንብረት ማክበር ይኖርባችኋል፡፡ በሌሎች ሰዎች ንብረት ስትገለገሉ ጉዳት እንዳይደርስበት ወይም እንዳይጠፋ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በክብር መያዝና ስራችንን ከጨረስን በኋላ ለባለቤቱ አስታውሰን መመለስ ይኖርብናል፡፡

## 3.2.2 ሀቀኝነት

**ተግባር 3.4**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ

1) ከሚከተሉት ተግባራት ውስጥ የሀቀኛ ሰው ባህሪን የሚያሳዩት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

(ሀ) የክፍል ጓደኛህ በፈተና ወቅት ከአንተ ለመኮረጅ ጠየቀህ ፤ሆኖም አንተ በሀሳቡ አልተስማማህም፤

(ለ) የቤት ስራህን እንደምትሰራ ለናትና ለአባትህ ቃል ገብተህ ነበር፡፡ ሆኖም በምትኩ ቴሌቪዥን አየህ ፤

(ሐ) ከጓደኛህ በውሰት እስክርቢቶ የወሰድክ ቢሆንም አልመለስክለትም፤

ሀቀኝነት ማለት በእውነት ላይ የተመሰረተ ንግግር መናገርና ተግባር የመፈጸም ብቃት ነው። ከዚህ በፊት ቀደም ብለን እንዳየነው ሀቀኝነት ማለት የሚያመጣው ውጤት ምንም ሆነ ምን ሁልግዜ እውነትን መናገር ማለት ነው። በተጨማሪም አንድ ሰው በታማኝነት እንዲታወቅ ከፈለገ ንግግሩ ብቻ ሳይሆን ተግባሩም እውነተኛ መሆን ይኖርበታል።

አንድ ተማሪ የሚያድረጋቸውን ነገሮች በድብቅ የሚፈጽም ከሆነ ሀቀኝነት ይጎድለዋል። ሀቀኛ ሰዎች እውነተኛ በመሆናቸው አይዋሹም፣ አያጭበረብሩም ወይም አይሰርቁም።

ከዚህ በታች ቀጥሎ የሚታዩት የመልካም ሰው መገለጫ ባህሪያት ናቸው፡

## የሀቀኛ ሰዎች መለያ ባህሪያት

- የገቡትን ቃል ማክበርና ሌሎች እውነትን እንዲናገሩ ማበረታታት
- እውነትን መናገር
- አለማጭበርበር ወይም አለመስረቅ
- ስህተትን መቀበል
- ነገሮችን ከሆኑት በላይ አድርጎ ለማቅረብ አለማጋነን

ሀቀኝነት የራሱ የሆኑ ብዙ ጥቅሞች አሉት። በህዝቦች መካከል አድናቆትንና ፍቅርን ያሳድጋል። ሀቀኛ ሰዎች እምነት የሚጣልባቸው፣አስተማማኝና የተከበሩ ሰዎች ናቸው። እውነትን መናገር፣ቃልን መጠበቅና እምነት የሚጣልበት መሆን በሌሎች ዘንድ እውቅናን ያሰጠናል። የሀቀኝነት መጓደል በሌሎች ዘንድ ውግዘትና ድርጊታችን ላይ ተቃውሞ ሊያስከትል ይችላል።

## 3.2.3 ክብር መስጠት

**ተግባር 3.5**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወላጆቻችሁን በመጠየቅ መልስ ስጡ

1) ወላጆችን ማክበር ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?
2) ወላጆቹን የማያከብር ልጅ ሊያጋጥመው የሚችሉ አስከፊ ውጤቶችን ግለጹ፤
3) አክብሮት መስጠት የት መጀመር ይኖርበታል?

የአክብሮት ጽንሰ ሃሳብ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡

### ለራስ ክብር መስጠት

አክብሮት ከራስ መጀመር ይኖርበታል፡፡ ራስን ማክበር ማለት ራስን መንከባከብና ስለራስ መልካም ስሜት መያዝ ማለት ነው፡፡ ተማሪዎች ሌሎች ሰዎችን ለመምሰል መጣጣር የለባቸውም፡፡ በራሳቸው መኩራትና ከሌሎች የተለዩ መሆን ችግር አለመሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡ተማሪዎች ለሚከተሉት ነገሮች ክብር መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

### ለአካላዊ ሰውነታችሁ ክብር መስጠት

ይህ ማለት ሰውነታችንንና ተፈጥሯዊ ውበታችን ጉዳት ከሚያስከትሉበት ማናቸውም ነገር መጠበቅና ባለበት ማቆየትን ያሳያል፡፡

### ለጤናችሁ ክብር መስጠት

ይህ ማለት የሰውነታችን ጤና እንዳይቃወስና ጉዳት እንዳያጋጥመው ተገቢውን ትኩረትና እንክብካቤ መስጠትን ያመለክታል፡፡

### ለአስተሳሰባችሁ ክብር መስጥት

አምሯችሁ ውስጥ ስለምታስቡት ነገር ትኩረት ስጡ፡፡ ይህን ማድረግ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት የምንፈጽማቸው ነገሮች የሚመሩት በሃሳቦቻችን በመሆኑ ነው፡፡

### ለጓደኞቻችሁ ክብር መስጠት

ሁሉም ሰው መከበርን፣ ፍቅርን፣አድናቆትን፣እውቅና ማግኘትን፣ተፈላጊነትን፣ከፍ ያለ ግመትንና በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን ይፈልጋል፡፡ ግብረ ገብ እንዳለው ሰው ደግ፣አሳቢና ለሌሎች ክብርን የምትሰጡ ሁኑ፡፡ ልክ እናንተ ከሌሎች አድናቆት ማግኘትን እንደምትፈልጉት ሌሎች ተማሪዎችም መደነቅ ይፈልጋሉ፡፡

### ለወላጆቻችሁ ክብርን መስጠት

ለወላጆች ክብር መስጠት እና የሚሰጧችሁን ምክር መስማት የመልካም ሰው መለያ የሆኑ ባህሪያት ናቸው፡፡ አስታውሱ! ከወላጆቻችሁ በላይ አብልጦ የሚወዳችሁ ሰው የለም፡፡ የሚያስፈልጋችሁን ክብር ይሰጧችኋል፣ስለራሳችሁ ጥሩ ስሜት እንዲኖራችሁ፤ ጥሩ ሰው እንድትሆኑና በህይወታችሁ ስኬታማ እንድትሆኑ ይፈልጋሉ፡፡

### በኃላፊነት ላይ ለተቀመጡ ሰዎች ክብር መስጠት

ከወላጆቻችን በተጨማሪ ማህበራዊና መንግስታዊ ኃላፊነት ላይ የሚገኙ አገልጋዮች የተቀዳሚ መረጃ ምንጮች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ መምህራንና የሃማኖት መሪዎች በህይዎት ዘመናችን ከምናገኘው እውቀት ውስጥ አብዛኛውን ድርሻ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ አስተማሪዎች ተማሪዎች ማወቅ የሚገባቸውን ነገሮች ያስተምሯቸዋል፡፡ ለተማሪዎች ዕድገት አስፈላጊ የሆነ ድርሻ አላቸው፡፡ አስተማሪዎች የእውቀት ኣባቶች/እናቶች ሲሆኑ የሚሰጡት ምክርና መመሪያዎች ተማሪዎች የተሻሉ ሰዎች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

## ለከባቢያችን ክብር መስጠት

አካባቢ ማለት በዙሪያችን ያለው አለም ማለት ነው። አካባቢያችንን መንከባከብ በጣም አስፈላጊ ነው። የዚህ ዋነኛ ምክንያቱ እኛ ሰዎች ምግብ፣ ንጹህ ውሃ፣ ንጹህ አየር፣ እና ሌሎች አሰፈላጊ ግብዓቶችን ለማግኘት በአካባቢያቸን ላይ ጥገኞች በመሆናችን ነው። ለምሳሌ የተተከሉ ዛፎች ካደጉ በኋላ የምንተነፍሰው ንጹህ አየር፣ የምንመገበው ፍራፍሬ እና ከፀሀይ የሚከላከል ጥላ ስለሚሰጡን ዛፎችን መትከል በጣም አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም አካባቢያችንን መጠበቅ ማለት በሌላ አነጋገር የራሳችንን ደህንነት መጠበቅ ማለት ነው። ንጹህና ጤነኛ አካባቢ እንዲኖረንና ደህንነታችን ተጠብቆ መኖር እንድንችል አካባቢያችንን ጠብቀን ማቆየት ይኖርብናል።ውሃ፣እጽዋት እና እንስሳት በሌሉበት ሁኔታ የሰው ልጅን ቀጣይነት ማረጋገጥ የማይታሰብ ነው። በመሆኑም የተፈጥሮ ሃብቶችንና የሰው ልጅን የሚያካትተው አካባቢያችንን መጠበቅና ማስቀጠል በጣም እስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ለአካባቢያችን ክብር መስጠት በሁሉም መልካም ባህሪ ባለው ሰው መከወን ያለበት ግብረገባዊ ሃላፊነት ነው።

## 3.3 መልካም ባህሪ የመላበስ ጠቀሜታ

**ተግባር 3.6**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው

1) የመልካም ባህሪ ባለቤት መሆን ምን ጥቅም አለው?
2) ሰዎች እንዲያደርጉልን በምንፈልገው መንገድ እንደዚያው ማድረግ ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?

መልካም ባህሪ መያዝ ቀን ተቀን ለምንመራው ህይወታችን እጅግ ጠቃሚ ነው። የጥሩ ባህሪ ባለቤት የሆኑ ተማሪዎች ከቤተሰበቦቻቸው፣ከአስተማሪዎቻቸው እና ከጓደኞቻቸው ጋር የተከበረና ትሁት የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

የመልካም ባህሪ መኖር በአግባቡ በስነ-ምግባር ተኮትኩቶ ማደግን ያመለክታል። በህይዎት ውስጥ ጠቃሚ ለውጦችን ለማምጣት እጅጉን አስፈላጊ ነው። ሌሎች በእኛ ላይ እንዲተማመኑና ወደኛ እንዲሳቡ እድሉን ይሰጠል።

መልካም ባህሪ ማህበረሰብ ውስጥ ክብርን፣ ታማኝነትንና ጓደኝነትን ይፈጥራል። በአግባቡ መልካም ባህሪ መላበስ ማለት ከሰዎች ጋር በተገናኘን ቁጥር እውቅና ልንሰጣቸው፣ ስማቸውንና ስለነሱ አንዳች ነገር የማስታወስና ራሳችንን በአሳቢነት መንፈስ መገለጽ ማለት ነው። በተጨማሪም መልካም ባህሪ መያዝ በቤተሰብ ውስጥ ፣በጓደኞች ዘንድ፣በትምህርት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ እናም በሌሎች ሁኔታዎች እጅግ ላቅ ያለ ጥቅም አለው።



ምስል 3.3 በጥሩ ስሜት ውስጥ ያለ ተማሪ

ከታች በዝርዝር እንደሚታየው ጥሩ ባህሪን መላበስ ወደ ሚከተሉት ውጤቶች ይመራል፡

**የሀቀኛ ሰው መለያዎች**

- በራስ መተማመን
- ለራስ ዋጋ መስጠት እና ውስጠዊ ጥንካሬ
- ደስተኛነት፣ውስጣዊ ሰላም እና እርካታ
- በቤተ-ዘመድ ዘንድ አወንታዊ ምስል መፈጠር
- ከጓደኞች ጋር ውጤታማ ተግባቦት መኖር
- ፍቅር፣ሞገስ፣ እውቅና እና ስኬታማነትን ማግኘት
- የሌሎችን ክብር ማግኘት

እነዚህ ብቃቶች በስተመጨረሻ የተሻለና ውጤታማ የማህበረሰብ አባል እንድንሆን ያግዙናል፡፡

## 3.4. የመልካም ባህሪ ማሳደጊያ ዘዴዎች

**ተግባር 3.7**

በፊት ከነበራችሁ እውቀት ተነስታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1) መልካም ባህሪን ማሳደግ ይቻላል ብላችሁ ታምናላችሁ?

2) መልካም ባህሪ ማሳደግ የሚቻልባቸውን 5 መንገዶች ዘርዝሩ

መልካም ሰው የግጭት ዝንባሌዎችን በማስወገድ መልካም ባህሪያትን እንዲያሳድግና በተግባር እንዲያሳይ ይጠበቅበታል። መልካም ማንነት ሊገለጽና ሊያድገ የሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ። የሚከተሉትን ጥቂት ምሳሌዎች እንመልከት፡

- የግብረ ገብ መርሆችን ለመተግበር የሚስችል ብቃትን ማሳደግ
- ታማኝ መሆንና የገቡትን ቃል መጠበቅ የሚያስችል ብቃት ማሳደግ
- ኃላፊነትን መወጣትና ራስን ለተጠያቂነት ማዘጋጀት
- አላስፈላጊ ከሆኑ ምኞቶች፣ ስሜቶች፣ውስጣዊ ግፊቶችን እና የመሳሰሉትን በመግታት ራሳችንን መቆጣጠር

ከዚህ በመቀጠል መልካም ባህሪን ማሳደግ የሚቻልባቸውን መንገዶች በጥልቀት እንመለከታለን

## 3.4.1 ራስን መቆጣጠር

**ተግባር 3.8**

ቀጥለው ለተሰጡት  ጥያቄዎች የራሳችሁን መልስ ለመስጠት ሞክሩ። ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት።

1) ራስን መቆጣጠር ማለት ምን ማለት ነው?
2) አንድ ሰው እንዴት መልካም ባህሪን ማሳደግ ይችላል?
3) ራስን መቆጣጠር አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ራስን መቆጣጠር ለህይወት ስኬት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ራስን መቆጣጠር የአንድ ሰው ሀሳቡን፣ስሜቱን፣ምኞቱን፣ፍላጎቱንና ልምዶችን የመቆጣጠር ብቃት ነው ብለን ትርጉም ልንሰጠው እንችላለን። በተጨማሪም መጥፎ ባህሪያት መቋቋም የምንችልበትና ራሳችንን አደብ የምናስገዛበት ችሎታ ነው ማለት ይቻላል። ራስን የመቆጣጠር ብቃትን መተግበር የሚችል ሰው ግቡን ማሳካት በሚያስችል መንገድ ባህሪውን መቆጣጠር ይችላል።

ራስን መቆጣጠር መቻል ወጣቶችን ራሳቸውን ከሚጎዳና ከግትር ባህሪ ያድናቸዋል። ራሳቸውን ለመምራት በአስቀመጡት መርህ መሰረት ድርጊቶቻቸውን እንዲፈጽሙ ያበረታታቸዋል። ራሳቸውን መቆጣጠር የቻሉ ልጆች የተሻለ የትምህርት ብቃት የሚኖራቸው ሲሆን ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር የተሻለ ግንኙነት ይኖራቸዋል። በተጨማሪም አስቸጋሪ ባህሪ የመያዝ አዝማሚያና ከትምህርት የማቋረጥ ዝንባሌያቸው ዝቅ ያለ ነው።

የሚቀጥለውን ታሪክ አንብቡና ለተከታዮቹ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

ውስን ጥናት፡

ቶማስ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን እድሜው 13 ነው፡፡ በት/ቤት ውስጥ በስርዓት አልበኝነትና በግልፍተኛ ባህሪው ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ የክፍሉ ተማሪዎች የቤት ስራውን እንዲሰሩለት ያስገድዳቸዋል፡፡ የሚላቸውን ካላደረጉለት እንደሚመታቸው ይዝትባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የያዙትን ምሳ እንዲያከፍሉት ያለፍላጎታቸው ያስገድዳቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ባህሪያት በቶማስ ላይ መጥፎ ውጤት ማስከተላቸው አልቀረም፡፡ ከቶማስ በስተቀር ሁሉም ልጆች የሚቀርቧቸው ጓደኞች አላቸው፡፡ የእኩዮቹን፣ የመምህራኑን እና የቤተሰቡን እምነት ማግኘት አልቻለም፡፡ በመሆኑም ባህሪውን ለመቀየር እና ጥሩ ሰው በመሆን የተለየ ባህሪ ለማሳየት ወሰነ፡፡

1) ይህ ተማሪ ያጋጠመውን ችግር መወጣት እንዲችልና ውሳኔውን እንዲያሳካ ምን ያስፈልገዋል?
2) ቶማስ መጥፎ ባህሪውን ተቋቁሞና በትምህርት ቤት ውስጥ ራሱን ከመጥፎ ባህሪ አቅቦ መቀጠል እንዲችል ምን ምክር ትሰጡታላችሁ?

### 3.4.2 ለህግ ተገዥ መሆን

ተግባር 3.9

በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1) ለህግ ተገዥ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
2) በክፍል ውስጥ ቢታዩ ተገቢ ተብለው የሚታሰቡ ባህሪያትን ዘርዝሩ፡፡
3) ለህግ ተገዥ ከሆኑ ተማሪዎች የሚጠበቁ ተግባራትን ዘርዝሩ ?

ህግ ማለት በህዝቦች ስምምነት ላይ ተመረኩዞ በመንግስት አካላት የተዘጋጀ የደንብና መመሪያ ስብስብ ነው፡፡ ሰላምን ለማረጋገጥና በህዝቦች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ሲባል በህግ አውጭ አካላት ይዘጋጃል፡፡

ህግን ማወቅና ለህግ ተገዥ መሆን ለቀን ተቀን ህይወታችን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ለህግ ተገዥ እንድሆን የሚያደርገን ያለብን ህጋዊ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግብረገባዊ ግዴታችንም ስለሆነም ጭምር ነው፡፡ የሚከተሉት ምክንያቶች ለህግ ተገዥ መሆን አስፈላጊነትን ያሳያሉ፡

- ህግ አጠቃላይ ደህንነታችንን ስለሚያስጠበቅልን፤
- ህግ ሰዎችን ከጉዳት ስለሚከላከል፤
- ህግ የህዝቦችን መልካም ፈቃድ ስለሚያንጸባርቅ፤
- የህግ መጣስ በህዝቦችና በሀገረ መንግስት መካከል ያለውን መተማመንና አንዱ በአንዱ ላይ መመካትን ስለሚሸረሽር፤
- ለህግ ተገዥነት ንብረት የመያዝ፣በህይዎት የመኖርና፣ግለሰባዊ ነጻነቶች እና ሌሎች መሰል ግለሰባዊ መብቶች እንዲጠበቁ ስለሚያስችል፤

### 3.4.3 የማህበረሰቡን ዕሴቶችንና መርሆችን ማክበር

**ተግባር 3.10**

ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በክፍል ውስጥ ለመምህራችሁ አሳወቁ

1) የግብረ ገብ እሴቶች ስንል ምን ማለታችን ነው?

2) በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የተለመዱ የግብረ ገብ እሴቶችን ግለፁ ?

3) እስካሁን በት/ቤት ባላችሁ ቆይታ ድርጊቶቻችሁ ጥሩ ናቸው ወይስ መጥፎ ነበሩ ብላችሁ ታስባላችሁ?









ምስል 3.4 ታላላቆችን ማክበር፣ ሰላምታ መለዋወጥ፣ ወላጆቻችንን ማክበር

**ተግባር 3.11**

የሚከተለውን ጥያቄ ከላይ በሚታዩት ምስሎች መሰረት መልሱ፡፡

1) ከላይ በምስሉ ላይ የሚታዩት የወጣቶች ድርጊት ክብርን መስጠታቸውን የሚያሳይ ይመስላችኋል? ለምን?

ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ፍጹም የተለየና የጋራ የሆነ ከማህበረሰቡ ባህላዊ እሴቶችና ልማዶች እያደጉ የመጡ የግብረ ገብ እሴቶች አሏቸው፡፡ ከዚህ በታች የሚታዩት በኢትዮጵያውያን ውስጥ ያሉ የግብረ ገብ እሴቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡

## በኢትዮጵያውያን መካከል የሚገኙ የግብረ ገብ እሴቶች ምሳሌዎች

- ከጎረቤት ጋር ሞቅ ያለ ሰላምታ መለዋወጥ
- ለአረጋውያን ክብርና ቅድሚያ መስጠት
- የወላጆችን ህጎች ማክበርና መገዛት
- ሁሉንም ሰው በእኩል አይን ማየት
- እውነትን መናገር
- እንግዳ ተቀባይነት
- ለሚደረግላቸው መስተንግዶ አመስጋኞች መሆን
- ስርዓት ያለው አለባበስ
- ስጦታን በሁለት እጅ መስጠትና መቀበል.

## 3.4.4 የትምህርት ቤት ህግና ደንብ ማክበር

**ተግባር 3.12**

ከታች ለተሰጡት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክሩ፡፡ ከተቻለ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

1) የት/ቤታችሁን ህግና ደንቦች ተረድታችኋል?

2) ከላይ ለተሰጠው ጥያቄ መልሳችሁ አዎን ከሆነ ቢያንስ 5 የት/ቤታችሁን ህግና ደንቦችን ዘርዝሩ?

የትምህርት ቤቶቻችን ህግና ደንቦች ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የት/ቤቱ አባል ምን ማድረግ እንዳለበትና ማድረግ እንደሌለበት መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ተማሪ አንድ ጊዜ ወደ ት/ቤቱ ከገባ በኋላ የት/ቤቱን ህጎችና ደንቦች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ ህጎች አላስፈላጊ የሆኑ ሥርዓት አለበኝነቶችን ለማስወገድ ያግዛሉ፡፡ ሁሉም ተማሪ በት/ቤት ወስጥ የሚያከናወናቸው ተግባራት ህግና ደንቦችን የተከተሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ከዚህ በታች በተከታይነት የተዘረዘሩት በትምህርት ቤት ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ህግና ደንቦች ምሳሌዎች ናቸው፡፡

## የት/ቤቶች ህግና ደንብ

- ሁሉም ተማሪዎች በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሰዓቱ መድረስ አለባቸው
- ተማሪዎች ያለ አስተማሪ/የት/ቤቱ ርዕሰ-መምህር/የክፍል ተቆጣጣሪ ፍቃድ ያለሰዓቱ ከት/ቤት መውጣት አይፈቀድላቸውም
- ሁሉም ተማሪ በእያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ መገኘት ይገበዋል
- ያለ ት/ቤቱ ፍቃድና እውቅና ማንኛውም ተማሪ ከክፍል መቅረት አይፈቀድለትም
- ተማሪዎች ውድ ጌጣጌጦችን መልበስ የለባቸውም
- በትምህርት ሰዓት ተንቀሳቃሽ ስልክ መጠቀም አይፈቀድም
- ተማሪዎች የት/ቤቱን ንብረት መጠበቅ አለባቸው
- ማንኛውም ተማሪ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ እስከተገኘ ድረስ የት/ቤቱን የተማሪዎች የደንብ ልብስ መልበስ ይጠበቅበታል
- ሁሉም ተማሪዎች ለብሔራዊ መዝሙርና ባንዲራ ክብርና ቅድሚያ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 3.5 መልካም ባህሪ ያለመላበስ ዉጤቶች

**ተግባር 3.13**

አምስት አባላት ያሉት ቡድን ከመሰረታችሁ በኋላ በአብዛኛው ስተለመዱ ብልሹ ባህሪያት አይነቶች በተመለከተ እያንዳንዳችሁ በግላችሁ ለወላጆቻችሁ ቃለ መጠየቅ በማድረግና በቡድናችሁ ውስጥ ከተወያያችሁበት በኋላ ለክፍላችሁ ተማሪዎች ያገኛችሁትን ውጤት አሳውቁ፡፡ በመቀጠልም መምህራችሁ የማጠናከሪያ ሃሳቦችን ይሰጧችኋል፡፡

1) የመልካም ባህሪ አለመኖር የሚያስከትለውን አስከፊ ውጤቶች ዘርዝሩ

1) ________________ 5) ________________ 9) ________________

2) ________________ 6) ________________ 10) ________________

3) ________________ 7) ________________

4) ________________ 8) ________________

የመልካም ባህሪ አለመኖር በህይዎታችን ውስጥ አሉታዊ ውጤቶች ያስከትላል፡፡
መልካም ባህሪ አለመላበስ የሚከተሉትን ውጤቶች ያስከትላል፡

## መልካም ባህሪ አለመላበስ የሚያስትላቸው ውጤቶች

- በተማሪዎች መካከል አለመከባበርን ማምጣቱ
- የግል እና የት/ቤት ንብረትን በአግባቡ አለመያዝ
- የት/ቤት ንብረትን ማውደም
- በሰዓት አለመገኘት
- በክፍል ውስጥ አለመገኘት
- የፈተና ኩረጃ
- ያልተገባ አለባበስ
- መዋሸት
- የእርስ በዕርስ ግጭት
- ስርቆት
- ታማኝ አለመሆን

## 3.6 የምዕራፉ ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ በዋናነት የተማሪዎች መልካም ባህሪያት ምንነትና መለያቸውን በተመለከተ ለማብራራት የቀረበ ነው፡፡ በተጨማሪም የጥሩ ሰው መለያ ባህሪያት ላይ ያተኩራል፡፡ የመልካም ሰው መገለጫዎች ከመልካም ባህሪ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይህም ማለት ከሀቀኝነት፣ እውነተኛነት፣ ተጠያቂነት፣ ራስን መቆጣጠር፣ክብር መስጠት እና የመሳሰሉትንጋር የሚገኛኝ ይሆናል፡፡ መልካም ባህሪ መያዝ በአንድ ሰው ህይወት ላይ የራሱ የሆኑ እሴቶች አሉት፡፡ ከነዚህ እሴቶች መካከል በራስ የመተማመን ችሎታ ለማሳደግ፣ለራስ ዋጋ ለመስጠት፣ለደስተኛነት እና የአእምሮ ሰላምና እርካታ ለማግኘት ማስቻሉን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም አወንታዊ ገጽታን፣ መወደድን፣ ተመራጭነትን፣ ክብርን፣ ዕውቅናን እና ከቤተ-ዘመድ ጋር መዋሃድ መቻልን ይፈጥርልናል፡፡ መልካም ባህሪ ማሳደግ የምንችልባቸው መንገዶችም

ተብራርተዋል፡፡ መልካም ባህሪ የምናሳድግባቸው መንገዶች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡ ራስን መቆጣጠር፣ ለሰዎችና ሰዎች ላልሆኑ ነገሮች ክብርን መስጠት፣ለት/ቤት ማህበረሰብ ህጎችና ደንቦች አክብሮ መስጠት እና ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ለተገኙ ግብረገባዊ እሴቶች ዋጋ መስጠት፡፡

በተጨማሪም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የመልካም ባህሪ በበቂ አለመኖር የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ትኩረት ተሰጥቶታል። እንደዚህ አይነት ጥሩ ያልሆኑ ባህሪያት ሌሎችን ወደ የግልንም ሆነ የህዝብ ንብረቶች በአግባቡ አለመጠቀም ሊያመሩ ይችላሉ። ተማሪዎች በሰዓቱ እንዳይገኙና ከትምህርት ቤት ቀሪ እንዲሆኑ ያበረታታቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች ሀቀኞች እንዳይሆኑ፣ወደ ስርቆት እንዲያመሩ፣ወደ ተለያዩ አላስፈላጊ ጥፋቶች እንዲገቡና ግጭትን እንዲመርጡ ሊያነሳሳቸው ይችላል።

## ቁልፍ ቃላት

- **ባህሪ፡** አንድ ሰው የሚያስብበት፣ ስሜቱን የሚያስተናግድበት እና ነገሮች የሚከውንበት መንገድ ማለት ነው
- **ራስን መቆጣጠር፡** ውስጣዊ ስሜቶችን መቆጣጠር/ማቀብ
- **ዋጋ፡** ጠቃሚነት ወይም አስፈላጊነት

## መልመጃ 3.1

ትዕዛዝ አንድ: **የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1) የተማሪዎች መልካም ባህሪ የሚገኘው ከተፈጥሮ ስጦታ ነው።

2) የወላጆች ፣ የመምህራን እና የጓደኞች ባህሪዎች በተማሪዎች ባህሪ ላይ ቀጥተኛ ሚና/ተፅኖ አለው።

3) አንድ ጊዜ መጥፎና ጠበኛ ባህሪ የያዘ ሰው ጥሩ ባህሪ ማሳደግ የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ የለውም

4) የት/ቤት የግብረ ገብ እሴቶችንና ደንቦችን ማክበር መልካም ባህሪን የምናሳድግባቸው መንገዶች ናቸው።

5) ለህግ ተገዥ መሆን አንድኛው የግብረ ገብ መገለጫ ነው።

ትዕዛዝ ሁለት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡ አማራች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘዉን ፊደል ምረጡ።

1) ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?

(ሀ) እንግዶችን በወዳጅነት ስሜት አለማየት

(ለ) የገባነውን ቃል አለማክበር

(ሐ) ክብር መስጠትና እንግዳ ተቀባይነት

(መ) የመምህራን ትዕዛዝ አለመፈጸም

1) ከሚከተሉት መካከል መልካም ባህሪን ለማሳደግ የሚያስችለን የትኛው ነው?

(ሀ) ራስን መቆጣጠር

(ለ) የማህበረሰባችንን የግብረ ገብ ስነ-ልቦና ከግምት ውስጥ ማስገባት

(ሐ) የት/ቤት ህግና እና ደንቦች ማክበር

(መ) ሁሉም መልስ ይሆናሉ

3) ከሚከተሉት ውስጥ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የግብረ ገብ እሴት ያልሆነው የትኛው ነው?

(ሀ) ለአረጋውያን ክብር መስጠት

(ለ) ለወላጆች ክብር መስጠት

(ሐ) ምቀኝነት

(መ) እንግዳ ተቀባይነት

4) ከሚከተሉት መካከል የት/ቤት ህግና ደንብ የሆነው የትኛው ነው?

(ሀ) በሰዓት መድረስና አርፍዶ ወደ ት/ቤት አለመምጣት

(ለ) የት/ቤቱን የደንብ ልብስ በአግባቡ መልበስ

(ሐ) ለብሔራዊ መዝሙርና ባንዲራ ክብር መስጠት

(መ) ሁሉም መልስ ናቸው

5) ለሌሎች ክብር መስጠት ማለት ምን ማለት ነው?

(ሀ) ለሌሎች አድናቆት መስጠት

(ለ) ለሌሎች ሰዎች ንብረት እውቅና መስጠት

(ሐ) ሌሎችን እንደራስ መመልከት

(መ) ሁሉም መልስ ናቸው

ትዕዛዝ ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር ማብራሪያ ስጡ።

1) ቢያንስ አራት ከተማሪዎች የሚጠበቁ የግብረ ገብ እሴቶችን ዘርዝሩ፤

2) መጥፎና ግልፍተኛ የሆነ ባህሪ ማሳየት የለሌብን ለምንድን ነው?

3) መልካም ባህሪ ያለው ግለሰብ ሰብዓዊ ለሆኑና ሰው ላልሆኑ ነገሮች ክብር እንዲሰጥ ይጠበቅበታል።

በቡድን በመሆን ከታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ከተሰጠው መረጃ በመነሳት እያንዳንዱ ተማሪ በሚሰጠው ግምት መሰረት መልስ ስጡ።

| ተ.ቁ | መቼት | ለራስ ክብር መስጠት | ለሌሎች ክብር መስጠት | ለአካባቢ ክብር መስጠት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መማሪያ ክፍል | | | |
| 2 | ቤተ-መጻህፍት | | | |
| 3 | የት/ቤት ቅጥር ግቢ | | | |
| 4 | ቤተሰብ | | | |
| 5 | ጎረቤት | | | |
| 6 | ማህበረሰብ | | | |

# ምዕራፍ አራት

## በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማድረግ

የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:

- ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታብራራላችሁ፤
- የበጎ ፍቃድ/ማህበረሰብ አገልግሎት ተሳትፎን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣለችሁ፤
- የትርፍ ጊዜ ሰዓትን እንዴት ለጋራ ጥቅም ሊዉል እንደሚችል ታሳያላችሁ፡፡
- የታማኝ ግብር ከፋዮችና የቁጠባ ባህል ለማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ያላቸውን ሚና ትገልጻላችሁ፡፡

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በማህበረሰቡ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ለማህበረሰቡ ጥሩ ማህበራዊ መስተጋብርና የኑሮ ሁኔታ ጠቀሜታ ያላቸው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት ያደርጋል፡፡ በበጎ ፈቃደኝነት፣የማህበረሰብ ተሳትፎ፣የትርፍ ጊዜን ለጋራ ጥቅም ማዋል በሚሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ንግድ፣ግብር ክፍያ፣መዕዋለ-ንዋይ፣ባንክና ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡

ተግባር 4.1

1) ማህበራዊ-ኢኮኖሚን እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው ?

2) ኢኮነሚያዊ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው ?

1) ማህበራዊ-ኢኮኖሚን እንቅስቃሴዎች በህይወት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው ?

የማህበራዊ ኢኮኖሚን ትርጉም መረዳት ወሳኝ ጉዳይ ነው። ማህበራዊ ተግባር ማለት በአንድ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ያለና ለማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣትና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንቅስቃሴ ነው። ማህበራዊ እንቅስቃሴ የማህበረሰቡን አባላት ወደ አንድ የሚያሰባስብ ተግባር ነው። በተጨማሪም ማህበራዊ እንቅስቃሴ በቡድን ወይም ማህበር የሚተገበር ተግባር ነው።




ስዕል 4.1: ተማሪዎችን በተለያዩ ተሳትፎዎች ላይ የሚያሳይ ምስል። (በስተግራ የቡድን ጥናት እና በስተቀኝ በሙዚቃ መሳሪያ እየተጫወቱ።)

**ተግባር 4.2**

1) ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ከላይ ባሉ ስዕሎች ምን እንደተረዳችሁ ተወያዩ።

የሚከተሉት ጥቂት የማህበራዊ ተግባራት ምሳሌዎች ናቸው።

- ለበጎ ፈቃድ በአንድ ላይ ቡድን መመስረት
- የጥናት ቡድኖች ክበባት
- ሙዚየም መጎብኘት ስርዓት
- የማህበረሰብ ቦታዎችን ማልማት
- ከጓደኞች ጋር መጫወት መዝፈን
- በዓል አከባበር
- የትምህርት ቤት
- የቡና አፈላል ስነ-
- የባህል ትዕይንቶች
- በቡድን ዘፈን

## 4.1. የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ፅንሰ ሃሳብ

የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት የገንዘብ ልዉዉጥ፣ እንዲሁም ምርትና አገልገሎት የሚከናወንበት ተግባር ነው። የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ገቢ ለማግኘት፣አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለመቀበል፣ ወይም ንብረት ለማፍራት የምናደርገው ተግባር ነው። አንዱና ዋነኛው የኦኮኖሚ ተግባር ምርትና አገልግሎቶችን አምርቶ ለተጠቃሚው ማቅረብ ነው። ገቢ ለማግኘት፣ ለፍጆታ፣ ለቁጠባ፣ ለመዕዋለ-ንዋይ፣ ሃብት ለማፍራት የሚደረግ እንቅስቃሴ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይባላል። ስለዚህ ህይወታችን ለመምራት የምናደርገው ሁሉም እንቅስቃሴ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይባላል።

## ተግባር 4.3

ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ከክፍል ጓደኞቻቹ ጋር ተወያዩ

1) ቢያንስ አምስት የኢኮኖሚ ተግባራት ምሳሌዎች ዘርዝ

2) ስድስት የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ተግባራት ዘርዝሩ

## ተግባር 4.4
ተግባር 4

ወላጆቻችሁን ጠይቃችሁ ከክፍል ጓደኞቻቹ ጋር ተወያዩ

1) ከሚከተሉት ስዕል የተረዳችሁትን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ



ስዕል 4.2 ልጅቱ ጫማ በመጥረግ ስራ ላይ

**ከዚህ በታች ያሉት ጥቂት የኢኮኖሚ አንቅስቃሴዎች የሚደረግባቸው ናቸው።**

- በእርሻ፣
- በከብት ጥበቃ፣
- ሱቅ ላይ እቃ በመሸጥ፣
- ምግብ በማብሰልና
- ጫማ በመጥረግ ናቸው።

በሌላ በኩል ሁሉም ሃማኖታዊ፣በጎ አድራጎት፣የአርበኝነት ስራ፣እንዲሁም የመዝናናት ተግባራት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አይደሉም።

**ማህበራዊ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት በአንድ ማህበረሰብ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት መሻሻል ሲባል በማህበሰቡ አባላት የሚሰራ ተግባር ማለት ነዉ። ይህ ማለት በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ ጥሩ የሆነ ግንኙነትንና ተግባቦትን የሚፈጥር ተግባር ማለት ነዉ። በይበልጥ ይህ ተግባር ገቢ፣ሀብት፣መዋለ-ንዋይና ጥሩ የኢኮኖሚ ህይወት እንዲኖር ያስችላል።**

## 4.2 በበጎ ፈቃድ ተግባራት ተሳትፎ ማድረግ (ማህበራዊ አገልግሎት)

ተግባር 4.4

ተተግባር 4.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው

1) ማህበራዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው

2) ማህበራዊ አገለግሎት ማለት ምን ማለት ነው

3 (በጎ ታግባራት ማለት ምን ማለት ነው

ማህበረሰብ ማለት የጋራ ማንነት ያላቸው የህዝቦች ስብስብ ማለት ነው ፡፡ ህዝቦች የጋራ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ ግዛትና ቋንቋ ወ.ዘ.ተ ይጋራሉ ;; በተጨማሪም የማህበረሰቡ አባላት ተመሳሳይ የህይወት ገፅታን ይጋራሉ



ስዕል 4.3: አቅመ-ደካሞችን በመርዳት ላይ



ስዕል 4.4: ዜጎች ለኢኮኖሚ ችግረኞች መጠለያ በመገንባት ላይ



ስዕል 4.5: ዛፎችን መትከልና አረንጓዴ ልማት

ተግባር 4.6 ውድ ተማሪዎች

ለሚከተለው ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1) ከላይ ካሉት ስሥዕሎች ምን ተረዳቹ

2) ቢያንስ አራት የማህበረሰብ አገለግሎቶችን ዘርዝሩ

**በጎ አድራጎት ማለት ለማህበረሰቡ ጥቅም የራስን ስዓትንና ጉልበትን በሙሉ ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነት ማዋል ማለት ነው። ገንዘብና ሽልማት ሳይጠብቁ በነፃ የሚፈፀም ተግባር ነዉ። ማንም ሰዉ በበጎ አድራጎት ስራ መሳተፍ ይችላል፡ ፡ ሰዎች ጊዜያቸዉንና ሃብታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ለበጎ አድራጎት ስራዎች ማዋል ምክኒያቶቹ፡- ድሃ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመርዳት፣ለአካበቢ ጥበቃ ስራ፣ ማህበረሰቡን ስለ ህገ-መንግስታዊ መብቶቻቸዉ ለማስተማር ወ.ዘ.ተ**

በጎ ፈቃድ የማህበረሰብ አገልግሎት ማለት በበጎ አድራጊዉ ሙሉ ፈቃድ እና ምርጫ ለማህበረሰቡ የሚሰጥ ነፃ አገልግሎት ማለት ነዉ። በጎ ፈቃድ የማህበረሰብ አገልግሎት የአካባቢዉን ማህበረሰብ ኑሮ ለማሻሻል የሚሰራ ተግባር ነዉ። ይህ አገልግሎት ለግል፣ ለድርጅትና ለአካባቢዉ መንግስት ትርፍ ወይም ጥቅም መሆን የለበትም። የበጎ አድራጎት ተግባር ለማህበረሰቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለዉ። ይህም ለማህበረሰቡ ማህበራዊ፣አካባቢያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ አዎንታዊ ጠቀሜታ አለዉ።

የሚከተሉት ጥቂት የማህበረሰብ አገልግሎት ምሳሌዎች ናቸው።

**የማህበራዊ በጎ አገልግሎት ምሳሌዎች፡-**

- በማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉትን አቅመ-ደካሞች መርዳት፤
- መጠለያቸውን መጠገንና የተራቡትን ምግብ ማብላት፡፤
- ነፃ የህግ አገልግሎት መስጠት፤
- ከትምህርት ቤት በኋላ ተማሪዎችን ማሰጠናት፣ የቤት ስራቸውን እንዲሰሩ ማገዝ፤
- ዛፎችን መትከል፣በመጥፋት ላይ ያሉ ብርቅዬ እንስሳትን መጠበቅና ሰዎችን ማስተማ፤
- ቋንቋ የመረዳት ችግር ላለባቸውን ሰዎች በተርጓሚነት ማገልገል፤
- መጽሐፎችን በቤተ-መጽሐፍ ዉስጥ ማደራጀት፤
- ጎረቤቶችን በተለያዩ የጥገና ስራዎች መርዳት፤
- የቋንቋ ክህሎቶችንና የባህል እሴቶችን እርስ በርስ መለዋወጥ።

## 4.3 የትርፍ ጊዜን ለጋራ ጥቅም ማዋል

**ተግባር 4.7**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጀመሪያ ጥንድ ሆናችሁ በመቀጠልም በቡድን በመሆን ተወያዩባቸዉ።

1) ትርፍ ጊዜ ማለት ምን ማለት ነው ?

2) የጋራ ጥቅም ማለት ምን ማለት ነዉ?

የመዝናኛ ጊዜ ማለት ከሙያና ሌሎች ስራ ሰዓታችን ፣ ከአስገዳጅ ስራዎች ፣ ከንግድና ከትምህርት ሰዕት ነፃ የምሆንበት ጊዜ ማለት ነው፡፡ ሰዎች በመዝናኛ ጊዜያቸው ይዝናናሉ ፣ ከመዶቻቸውን ይጠይቃሉ ፣ መፅ ያነባሉ ፣ ሌሎች ሰዎችን ይረዳሉ ወ.ዘ.ተ

የጋራ ጥቅም ማለት የሁሉም ማህበረሰብ አባላት የጋራ ፍላጎት ማለት ነው ፡፡ ይህም ማለት ለማህበረሰቡ በጋራ የሚጠቀሙበት መገልገያ አቅርቦት ነው ፡፡

## የሚከተሉት ጥቂት የማህበረሰቡ የጋራ ጥቅም ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡

- የህዝብ መሰረተ-ልማት፡፡
- የህዝብ ትራንስፖርት፡፡
- የህዝብ ትምህርት ቤቶችና ቤተ-መጽሐፍት፡፡
- ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፡፡
- ንጹህ አካባቢ፡፡
- ሙዚዬሞችና የባህል ተቋማት





ስዕል 4.6: የተቋም አካባቢዎችን ማጽዳት፣ ሙዚዬሞችንና የባህል ተቋማትን መጎብኘት፡፡

ተግባር 4.8

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባለው ስዕል መሰረት መልሱ ፡፡

1) ባለፈው ረፍት የትርፍ ጊዜያችሁን የት አሳለፋቹ
2) የትርፍ ጊዜ ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው

## የኒከተሉትን የመዝናኛ ጊዜ ጠቀሜታዎች ናቸው

- የጤና ጥቅሞች ይሰጣል፡፡
- ማህበራዊ ግንኙነትን ያዳብራል፡፡
- የግል እርካታ ይሰጣል ፡፡
- ኑሮን ያሻሽላል ፡፡
- ለራሳችን ዋጋ እንድትሰጡና አዎንታዊ እይታ እንዱኖረን ያደርጋል፡፡
- አዎንታዊ የህይወት አኗኗር ዘዴን ያዳብራል
- ጭንቀትን ይቀንሳል

## 4.4 የሀቀኛ ግብር ከፋዮችና ቁጠባ ለማህበራዊ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ያላቸዉ ሚና

ተግባር 4.9

ቡድን በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1) ንግድ ማለተ ምን ማለት ነው

2) ገቢያ ማለት ምን ማለት ነው

ንግድ ማት በሰዎችና ሃገረፐች መካከል መገዛዛት ፣ መሻሻጥና ምርትና አገለግሎቶችን መለዋወጥ ማለት ነው ፡፡ ምርትና አገለግሎቶችን በገንዘብ መለዋወጥን ያስፈልጋል ፡፡ አምራቾ ምርታቸውን ለጅምላ አገፋፋዮች ያስረክባሉ ጅምላ አከፋፋዮችም ለቸርቻሪዎች ያሰራጫሉ ፡ ቸርቻሪዎችም በመጨረሻ ለተጠቃሚው ይሸጣሉ

ገቢያ ማለት ሸቀጦች የሚገዙበትና የሚሸጡበት ቦታ ማለት ነው ፡፡ ገበያውም በውስጡ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሱቆች ፣የልብስ መደብሮች ፣መጋዘኖች እና ወ.ዘ.ተ የያዘ ነው ፡፡

ተግባር 4.10

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወላጆቻችሁን ጠይቃአኑ በቡድን ተወያዩ

1) ግብር ማት ምን ማለት ነው

2) ሰዎች ለመንግስት ግብር ለምን ይከፈላል






ስዕል 4.7: ከዜጎች በተሰበሰበ ግብር የተገነቡ መሰረተ-ልማቶች

መብራት፣ መንገድ፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና ሌሎች አገልግሎቶችን ለህዝብ የሚያቀርብን አካል አድንቃችሁ ታዉቃላችሁ? መልሱ አዎ እናዉቃለን ነው፡፡ ማንኛዉም ሰራተኛ ግብር ለመንግስት ይከፍላል፡፡ ዜጎች በመንግስት አቅርቦት የሚፈልጓቸዉ ብዙ አገልግሎቶች አሉ፡፡ መንግስትም ለዜጎች የደህንነት፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የስራ እድልና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን አገልግሎት ለመስጠት ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ግብር ለመንግስት ዋና የገቢ ምንጭ ነው፡፡ መንግስት ግብር ከግለሰቦችና ድርጅቶች ሰብስቦ ለዜጎች የተለያዩ አገልግሎቶችን ያዳርሳል፡፡ በሌላ አነጋገር ግብርን መክፈል ለእያንዳንዱ ዜጋ ጠቃሚ ነው፡፡

> ግበር ግለሰቦች ወይም ደርጅቶች ከገቢያቸው በፐርሰንት ለመንግስት የሚከፍሉት ክፍያ ነው ፡፡
>
> ማንኛውም ሰው ከገቢው/ከገቢዋ ለመንግስት ግበር የመክፈል ግዴታ አለበት /አለባት ፡፡ ለየትኛውም
>
> መንገስት ግብር ዋነኛ የገቢ ምንጭ ነው ፡፡ መንግስት ከግለሰቦችና ከድርጅቶች ገቢ ግብር የመሰብሰብ ሃላፊነት አለበት ፡፡

ግብር የመክፈል ዓላማዉ የመንግስትን የፋይናንስ አቅም ለማጠናከር ነው፡፡ ግብር ካልተከፈለ የመንገድ፣ የመብራትና የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማቶችን ማቅረብ አይችልም፡፡ በይበልጥ ግብር ለጤና፣ ትምህርት፣ መከላከያ ሃይል ወ.ዘ.ተ ለሆኑ የህዝብ አገልግሎቶች ለማቅረብ በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡

ግብር የሚከተሉትን ጉዳዮች መሰረት አድርጎ ይሰበሰባል፡

- የፋይናንስ ገቢ
- ከግለሰቦች የንግድ ትርፍ
- ከቋሚና ዋጋ ካላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ወ.ዘ.ተ

ትንሽ መቆጠብ ሁሉን ነገር ከመጠቀም የተሻለ ነው፡፡

ተግባር 4.11

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1) ቁጠባ ማለት ምን ማለት ነው

2) በአካባቢያችሁ የሚገኙ የቁጠባ ተቋም መጥቀስ ትችላላችሁ

3) ቁጠባ በህይታችሁ ላይ የሚያመጣው ውጤት ምንድን ነው

ቁጠባ ማለት አንድን ነገር በሙሉ ወጭ ከማውጣት ወይም ከመጠቀም ርቆ ለወደፊት

ፍጆታ ማስቀመጥ ማለት ነው ፡፡ ነገር ግን ለሕይታችን አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ወጭ አለማውጣት ወይም አለመቀመጥ ማለት አይደለም ፡፡ ቁጠባ ገንዘብን ፣ ጊዜንና የተለያዩ ሃብቶችን አለማክበር ማለት ነው ፡፡

የቁጠባ ጥቅሞች እንደሚከተለው በጥቂቱ ተዘርዝረዋል፡፡

## የቁጠባ ጥቅሞች

- ለተማሪዎች የሙያ ትምህርት ያግዛል ፡፡
- ለድንገተኛ ወጭ ይጠቅማል ፡፡
- ለትምህርት ቤት ክፍያ ይውላል፡፡
- ለትምህርት መሳሪያ ወጭ ያግዛል ፡፡
- ተማሪዎች ነፃ እንዲሆኑና እንዳይጨነቁ ይራዳል ፡፡
- ከሰዎች በድር እነዳንጠይቅ ይረዳል ፡፡
- ለድህነትና ስሜትና ሰላማዊ አእምሮ እንዲኖረን ይረዳል

የቁጠባ ተቋማት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ዘመናዊና ባህላዊና የቁጠባ ተቋም ናቸው፡፡

ዘመናዊ የቁጠባ ተቋማት ፡ ይህ ተቋም ባንኮችን፣የመድህን ድርጅቶች፣ ጥቃቅን የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎችን ያካትታል፡፡ በኢትዮጵያ ብዙ የግልና የመንግስት ባንኮች አሉ፡፡







ባህላዊ የቁጠባ ተቋም፡ ‹‹ዕቁብ›› በኢትዮጵያ በዋናነት የሚጠቀስ ባህላዊ የቁጠባ ተቋም ነው፡ ፡ ሰዎች በፈቃደኝነት ቡድኑን በመቀላቀል በተቋሙ ህግና ደንብ መሰረት አስገዳጅ መዋጮ ያደርጋሉ፡፡

የታማኝ ግብር ከፋዮችና የሰዎች የቁጠባ እንቅስቃሴ ሚና ለአንድ ሃገር ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ አንቅስቃሴዎች ብዙ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ የገቢዎች ቢሮ ባስቀመጠው ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ግብር ካልተከፈለ ለእድገት እንቅፋት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቁጠባ ሰዎች የህይወታቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ ይረዳቸዋል፡፡

## 4.5 የምዕራፍ ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረዉ በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው፡፡ የማህበረሰቡን ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ አይተናል፡፡ ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነትና ተግባቦት እንዲኖር ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ማህበራዊ ህይወታቸዉን ለማጠናከር በማንኛዉም ማህበራዊ ተሳትፎ በበጎ አድራጎነት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ከትምህርት ሰዓት ዉጭ በትርፍ ጊዜያቸዉ መሆን ይችላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ማለትም እንደ ንግድ፣ ቁጠባ፣ ግብር መክፈል እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

ማህበራዊ -ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሰዎች ገቢ፣ ወጭና የቁጠባ ባህል ላይ ያተኩራሉ፡፡ ገቢያችን ማህበራዊ ሁኔታዎችንና የአኗኗር ዘይቤያችንን ይወስናል፡፡ የበጎ አድራጎት ተግባራት ራስን ለመጥቀምና ትርፍ ለማግኘት የሚሰራ ተግባር አይደለም፡፡ ነገር ግን የሌሎችን ፍላጎት ለማሟላት የታለመ ነዉ፡፡ ትርፍ ጊዜያችንን ለጋራ ጥቅም ማዋል ጠቃሚ ነዉ፡፡ የትርፍ ጊዜ ሰዓት ማለት የመዝናኛ ሰዓትና የሙያ ወይንም ማንኛዉንም ዓይነት ስራ የማንሰራበት ነፃ ጊዜ ማለት ነዉ፡፡

በማህበረሰቡ ጠንካራና ጥሩ ኢኮኖሚን ለመፍጠር ቁጠባና ግብር መክፈል አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸዉ። ቁጠባ ማለት ገንዘብ፣ ጊዜን፣ ንብረትን በአግባቡ መጠቀምና ለቀጣይ ፍጆታ ማቆየት ማለት ነዉ። ነገር ግን ለህይወታችን አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ወጭ አለማዉጣት ወይም አለመጠቀም ማለት አይደለም። ቁጠባ ገንዘብን፣ ጊዜንና የተለያዩ ሃብቶችን አለማባከን ማለት ነው። ቁጠባን ማሳደግ ማህበራዊ-ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ያጎለብታል። በገቢያችን መጠን ግብርን ለመንግስት መክፈል ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አወንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

## ቁልፍ ቃላት

ማህበራዊ-ኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች: የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ዉህድ ተግባራት

**ቁጠባ**: ገንዘብ፣ ጊዜን፣ ንብረቶችን በአግባቡ መጠቀምና ለቀጣይ ፍጆታ ማቆየት

### መልመጃ 4.1

ትዕዛዝ አንድ. የሚከተሉትን አረፍተ-ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆኑ “እዉነት” ትክክል ካልሆኑደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ።

1) ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በኢኮኖሚያዊ ህይወታችን ላይ ምንም ዓይነት ሚና የላቸዉም።

2) ባንኮችና የመድህን ድርጅቶች ዘመናዊ የቁጠባ ተቋማት ናቸዉ።

3) ግብር መክፈል ለአንድ ሀገር ልማት ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ የለዉም።

4) የትርፍ ጊዜ ሰዓት ማለት የሙያ ወይንም ማንኛዉንም ዓይነት ስራ የማንሰራበት ነፃ ጊዜ ማለት ነዉ።

5) ቁጠባ ማንኛዉም ሰዉ በህይወቱ ተግባራዊ ሊያደርገው የሚገባ ጠቃሚ ነገር ነው።

ትዕዛዝ ሁለት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1) ከሚከተሉት ዉስጥ ከኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ይልቅ ማህበራዊ እንቅስቃሴ የሆነው የቱ ነው?

(ሀ) ማንኛዉም ገቢ የሚያስገኝ እንቅስቃሴ

(ለ) የትኛዉም ሃብት መሰብሰብ የሚያስችል እንቅስቃሴ

(ሐ) ለግል ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ.

(መ) መልሱ አልተሰጠም።

1) ከሚከተሉት ዉስጥ ስለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ትክክል የሆነዉ የቱ ነው?

(ሀ) የገቢ መጠን

(ለ) የኢኮኖሚ አቅም

(ሐ) ግንዛቤና አመለካከት

(መ) ሁሉም መልስ ናቸዉ፡፡

2) ከሚከተሉት ዉስጥ የማህበረሰብ ተሳትፎ ምሳሌ ሊሆን የማይችለዉ የቱ ነው?

(ሀ) መስረቅና ማጭበርበር

(ለ) ደንን ማልማት

(ሐ) በመጥፋት ላይ ያሉን እንሰሳት መጠበቅ

(መ) ስለተፈጥሮና አካባቢ ለህዝቡ ግንዛቤ መፍጠር

4) ከሚከተሉት ዉስጥ ግብር የሚሰበሰብበት ከየትኛዉ ነዉ?

(ሀ) ከግለሰቦች ገቢ

(ለ) ከንግድ ገቢ ከሚገኝ ትርፍ

(ሐ) ተንቀሳቃሽ ንብረቶችና መሬቶች

(መ) ሁሉም መልስ ናቸዉ፡፡

ትዕዛዝ ሦስት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1) ቢያንስ አስር የማህበራዊ ተግባራት ምሳሌዎችን ዘርዝሩ፤

2) ቢያንስ አስር የኢኮኖሚያዊ ተግባራት ምሳሌዎችን ዘርዝሩ፤

3) ቁጠባ በአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ያለዉን ጠቀሜታ ተወያዩ፤

4) የትርፍ ጊዜ ለእናንተ እና ለማህበረሰቡ ያለዉን ቢያንስ አምስት ጠቀሜታዎች ዘርዝሩ፤

5) በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ቢያንስ አምስት ባንኮችን ጥቀሱ፤

6) በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ጥቂት የመድህን ድርጅቶችን መዘርዘር ትችላላችሁ?

# ምዕራፍ አምስት

## የሀገር ፍቅር

የመማር ውጤቶች፡-ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- የሀገር ፍቅር ምንነት ትርጉም ትሰጣላችሁ
- የሀገር ፍቅር ባህሪያትን እና አስፈላጊነትን ታብራራላችሁ
- ስለሀገር ኩራት ለምን ሊሰማችሁ እንደሚገባ ትረዳላችሁ
- የሀገር ፍቅርን ማሳየት የሚቻልባቸውን መልካም መንገዶች ታሳያላችሁ

## መግቢያ

ሀገርን መውደድ ምን ማለት ነው? ሀገር መውድንን እንዴት ማሳየት እንችላለን? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የሀገር ፍቅር ባህሪያትና ጥቅሞች መረዳት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው ሀገሩን ይወዳል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡

## 5.1 የሀገር ፍቅር ስሜት ምንነት

ተግባር 5.1

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ አሰላስሉና መልስ ስጡ፡፡ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡

1) ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሀገርን መውድድ ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ፡፡

2) የሀገር ወዳድነት ባህሪ መገለጫ የሆኑ ምሳሌዎችን ስጡ፡፡

ሀገርን መውደድ ማለት አንድ ሰው ለሀገሩ የሚኖረው ጥልቅ ፍቅር ማለት ነው። አንድ ሰው ለሀገሩ የሚኖረውን የፍቅርና ታማኝነት መንፈስ የሚያሳይ ነው። ይህ ማለት ህዝቦች በማናቸውም ሀገራቸውን በሚወክሉ ነገሮች ላይ በሚሰማቸው ኩራት ይገለጻል። ይህም የሚከተሉትን ነገሮች ይጨምራል፡- የሀገር ሰንደቅ ዓላማ፣ ብሔራዊ መዝሙር፣ ሀገራዊ ታሪክ፣ አርበኝነት ጀግንነት እና ሌሎች

የሀገር ፍቅር ለሀገር መሬትና የአኗኗር ዘዬ ፍቅርና ማሳደግን ይጠይቃል። ሀገር ወዳድነት ለተወለዱበትና ለአደጉበት ቦታ እውነተኛ ፍቅር መያዝን ያሳያል። በተጨማሪም ለትውልድ ቦታና ለማህበረሰቡ ትግሁ አገልጋይ መሆን ማለት ነው።

የሀገር ፍቅር አንድ ሰው ስለ ሀገሩ በሚናገርበት መንገድ፣ በሚፈጽመው ተግባር እና በሚያሳየው ስሜት ይገለጻል። ይህም በሀገር የጋራ ባህል፣ ታሪክ እና ዳር ድንበር ላይ የሚኖራቸውን ኩራት ነው። በተጨማሪም ህዝቦች ሀገራቸው በአሳካችው ውጤት ላይ ያላቸውን ኩራት የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። ሀገር ወዳድ ዜጎች የሀገራቸው ስኬት የራሳቸው ስኬት እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ። ከሁሉም በላይ ሀገር ወዳድነት ሌሎች ዜጎችን መውደድን ይጠይቃል፡ ፡ አንድ ሰው ለሀገሩ ዜጎች ፍቅር ሳይኖረው እውነተኛ ሀገር ወዳድ ዜጋ ሊሆን አይችልም።

የሀገር ወዳድነት ኃላፊትን ለመወጣት የሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶች አሉ። የሀገርን ጠላት በጦርነት መዋጋት ብቻ ተደርጎ መታሰብ የለበትም። ከዚህ በተለየ በሚከተሉት መንገዶች መግለጽ ይቻላል፡- ድህነትን ከማህበረሰቡ ጫንቃ ላይ ለማውረድ ጠንክሮ መስራት፣ የተሻለ አካባቢን ለመፍጠር እንዲቻል ዛፎችን መትከል እና ግብርን መክፈል የሀገር ወዳድነት ምሳሌዎች መሆን ይችላሉ።

ሀገር ወዳድነት በታሪክና ነጻነትን አስጠብቆ በማቆየት ምክንያት የክብር ስሜት በመያዝ ሊገለጽ ይችላል። ሀገር ወዳዶች የሀገራቸው ነጻነት ጠባቂዎች ናቸው። የሀገራቸውን ነጻነትን ላለማስደፈር ሲሉ ህይወታቸውን ለመሰዋት ፈቃደኞች ይሆናሉ። ሀገር ወዳድ ዜጎች ሀገራቸውን ለማስቀጠል ሲሉ መስዋዕትነት ለከፈሉ የአገሪቱ ህዝቦች ትልቅ ክብር አላቸው። ከቅድመ አያቶቻቸው መሰዋዕትነት ጀግንነትን ይወርሳሉ።

# የማነቃቂያ ጥያቄዎች

ተግባር 5.2

ተከታዩን ታሪክ አንብቡና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ቀጥሎ የሚመጡ ጥያቄዎችን መልሱ

ሻምበል አበበ ቢቂላ (1932-1974 ዓ.ም

ሻምበል አበበ ቢቂላ የኢትዮጲያዊ የረጅም ርቀት ሩጫ ተወዳዳሪ ነበር፡፡ የሻምበል አበበ ህይወት በብዙ አስደናቂ ታሪኮች የተሞላ ነበር፡፡ ከአፍሪካ የመጀመሪያው የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ እርሱ ነበር፡፡ የመጀመሪያው የሆነውን የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘው በሮም ኦሎምፒክ በ1956 ነበር፡፡ ማራቶኑን ከማሸነፉ በላይ አስደናቂ የነበረው ነገር አበበ ሩጫውን የሮጠው በባዶ እግሩ መሆኑ ነው፡፡ ኦሎምፒኩን ሲከታተሉ የነበሩ ሰዎች በሙሉ በጥንካሬው እጅግ ተገርመው ነበር፡፡

ሻምበል አበበ ሁለተኛ የኦሎምፒክ ወርቅ ያገኘው በቶኪዮ ኦሎምፒክ ላይ ነበር፡፡ ይህ በጣም አስገራሚ ነበር ምክንያቱም አበበ ሩጫውን ከማድረጉ ከሁለት ሳምንት በፊት ቀዶ ጥገና አድርጎ ነበር፡፡ አበበ ለሶስተኛ ጊዜ ኦሎምፒክን ለማሸነፍ ሙከራ አድርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ታሞ ስለነበር ሩጫውን መጨረስ አልቻለም፡፡ የሀገሩ ልጅ የሆነው ማሞ ወልዴ የአበበን መታመም አይቶ ሊረዳው ሞከረ፡፡ ሆኖም አበበ ለማሞ ሩጫውን እንዲቀጥልና ማራቶንን በማሸነፍ ኢትዮጲያዊያንን እንዲያኮራ ነገረው፡፡ እነዚህ የአበበ ቢቂላ ታሪካዊ ድሎች ዛሬ የኢትዮጲያዊያን የኩራት ምንጮች ናቸው፡፡

- የአበበ ቢቂላን ድሎች ግለጹ?
- የአሁኑ ትውልድ ከአበበ ቢቂላ ቆራጥነት ምን መማር ይችላል?

## 5.2 የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች

ተግባር 5.3

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ

1) ሀገር ወዳድ የሆኑ ዜጎች የሚያሳዩዋቸውን ባህሪያት ጥቀሱ
2) በዜጎች የሚወሰዱ ሀገር ወዳድ ዕርምጃዎችን ለማሳየት ምሳሌዎችን ተጠቀሙ

ሀገር ወዳድነት የሚከተሉት ባህሪያት ይኖሩታል፡

- <u>በሀገር መኩራት</u>፡- ሀገር ወዳዶች ያለ ቅድመ ሁኔታ የትውልድ ሀገራቸውን ይወዳሉ፡፡ ሀገራቸው ለሰጠቻቸው ነገሮች በሙሉ አመስጋኞች ናቸው፡፡ ሀገር ወዳዶች በሀገራቸው ስኬቶች ኩራት ይሰማቸዋል፡፡

- <u>የባለቤትነት ስሜት መያዝ</u>፡- ሀገር ወዳዶች ከትውልድ ሀገራቸውና ከህዝባቸው ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ይስማቸዋል፡፡ ለሀገራቸው ያላቸው የጋራ ፍቅር በመካከላቸው ያለውን ትስስር ይበልጥ ያጠናክረዋል፡፡

- <u>ለሀገር ራስን ለመሰዋት ዝግጁ ማድረግ</u> ፡- ሀገር ወዳዶች የሀገራቸውን አንድነት ለማስጠበቅ ሁልጊዜ ዝግጁ ናቸው፡፡ የሀገራቸውን ነጻነት ከሌሎች አገሮች በላይ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም ሀገራቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ህይወታቸውን ለመስጠት ፍቃደኞች ናቸው፡፡

- <u>ሙስናን መዋጋት</u>፡- ሙስና በህዝብ የተሰጠ ኃላፊነትን ለግል ፍላጎት ማሚያነት ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ነው፡፡ ሀገር ወዳድ ሰው ከሀገሩ ላይ አይሰርቅም፡፡ ይህም የሆነው ከሀገራቸው ላይ መስረቅ ሀገርን እንዳያድግ እድል መንፈግ እንደሆነ በመረዳታቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የሀገራቸውን ጥቅም ከራሳቸው ጥቅም አስቀድመው ያስቀምጣሉ ማለት ነው፡፡ ሀገር ወዳድ ዜጎች በሌሎች የተፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ይቃወማሉ፡፡ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካለት ጉዳዩን ያሳውቃሉ፡፡

- <u>ለሀገር ጀግኖች ክብር መስጠት፡-</u> ይህ ሀሳብ የሀገርን ጥቅም ከራስ ጥቅም ማስቀደም ላይም ተንጸባርቋል፡፡ ሀገር ወዳዶች ለሀገራቸው ጀግኖች ክብር ይሰጣሉ፡፡ ጀገና ለአንድ ዓላማ ሲል ራሱን መሰዋት አድረጎ ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆነ ነው፡፡ የሀገር ጀግኖችም ለሀገራቸው ሲሉ ህይወታቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ሀገር ወዳዶች ታላላቆቻቸው ሀገራቸውን ለማቆየት ሲሉ ከፍተኛ መሰዋትነት እንደከፈሉ ይረዳሉ፡፡ ቅድመ አያቶቻቸው የከፈሉት መሰዋትነት ለአዲሱ ትውልድ የጀግንነት ምንጭ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ታሪኮች ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ጥንካሬ ይሰጣቸዋል፡፡

## 5.3 ሀገር ወዳድ የመሆን ጠቀሜታ

ተግባር 5.4

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶቻቸውን አስቡና ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት

- ሀገር ወዳድ ዜጋ መሆን ያለውን ጥቅሞች ግለጹ
- የዜጎች ሀገር ወዳድ መሆን ለሀገር ያለውን ጠቀሜታ ተወያዩ

ሀገር ወዳድነት የአገርን አንድነት ለማስጠበቅ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ዜጎች ሀገራቸው እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ ሀገርም ዜጎቿ ያስፈልጓታል፡፡ ሀገር ወዳድ የሆኑ ዜጎች የሌለው ሀገር ለውጭ ጥቃት የተጋለጠ ይሆናል፡፡ ሀገር ወዳድ ዜጎች የሀገራቸውን ፍላጎት ሁልግዜ ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ ሁሉም ትውልድ የአገርን አንድነት በማስጠበቅ ዙሪያ የራሱ የሆነ ሚና አለው፡፡

ሀገር ወዳድነት ለአንድ ሀገር ዕድገት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሀገር ወዳድ ዜጎች የሀገራቸውን ዕድገት ለማረጋገጥ ያላቸውን ሀይል አሟጠው ይጠቀማሉ፡፡ ለመሬታቸውና ለህዝባቸው ያላቸው ጥልቅ ፍቅር ጥረታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ያነሳሳቸዋል፡፡ በየትኛውም ሙያ ውስጥ ቢገኙም ምርጥ አቅማቸውን አውጥተው ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡

የሀገር ወዳድነት ባህሪ በመሪዎች ዘንድ እንዲኖር የሚፈለግ ብቃት ነው፡፡ ሀገር ወዳድ መሪ ማለት ለመሬቱና ለህዝቡ ጥልቅ ፍቅር ያለው መሪ ማለት ነው፡፡ እነዚህ መሪዎች ያላቸውን ስልጣን ለሀገራቸው የተሻለ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡ ሀገር ወዳድ መሪ በፍጹም በሙስና ላይ አይሳተፍም፡፡ ከላይ እንዳልነው ሙስና በህዝብ የተሰጠን ስልጣንን ለግል ፍልጎት ማስፈጸሚያ ጥቅም ላይ ሲውል ነው፡፡

ሀገር ወዳድ መሪዎች የተሰጣቸውን ህዝባዊ ኃላፊነት የግል ሃብት ለማካበት አይጠቀሙበትም፡፡ የራሳቸው የሆነን ጠባብ ፍላጎት ከህዝባቸው በፊት አያስቀድሙም፡፡ በሀገራቸው የሚገኘውን ሀብት ት/ቤት፣ ሆስፒታል፣ መንገድ እና የመሳሰሉትን ለመገንባት ጥቅም ላይ ያውሉታል፡፡ ቀጣዩ ትውልድ ከእነሱ የተሻለ ህይወት እንዲኖረው ይፈልጋሉ፡፡

## 5.4 የሀገር ወዳድነት መገለጫዎች

**ተግባር 5.5**

1) በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ በዜጎች የሚታዩ ባህሪያት ላይ ተወያዩ

2) ሀገር ወዳድ የሆኑ ዜጎች ለማህበረሰባቸው የሚያሳዩአቸውን ባህሪያት ግለጹ

# የማነቃቂያ ጥያቄዎች

የሚከተለውን ታሪክ አንብቡና በተከታይነት ለተሰጡት ጥያቄዎች ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን መልሱ ስጡ፡፡

አቶ በሪሁን ስኬታማ የንግድ ሰው ሲሆን ስለሀገሩ አዘውትሮ በብዛት ይናገራል፡፡ ለሀገሩ ታሪክና ለህዝቦቿ ስላለው ፍቅር ይናገራል፡፡ እሱ ባለበት ቦታ ስለ ሀገሩ መጥፎ ንግግር የሚናገር ሰው ካጋጠመው ከዚያ ሰው ጋር ወደ ጭቅጭቅ ውስጥ መግባቱ የተለመደ ነው፡፡ አቶ በሪሁን በወሩ መጨረሻ ከንግዱ ያገኘውን ገቢ ለመንግስት ያሳውቃል፡፡ ይሁን እንጂ አቶ በሪሁን ሁልጊዜ ገቢውን ባሳወቀ ቁጥር የትርፉን መጠን አሳንሶ ያቀርባል፡፡ ይህንን የሚያደርገው የሚከፍለው ግብር አነስተኛ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ ይህ ሀቀኝነት የጎደለው ተግባር ለሀገሩ ከግብር መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ ያሳጣል፡፡ ሰዎች ግብራቸውን በአግባቡ ካልከፈሉ ሀገር ለዜጎች ማቅረብ የሚገባትን አስፈላጊ አገልግሎቶች ልታቀርብ አትችልም፡፡ አቶ በሪሁን በሚናገሩት ንግግርና በሚፈጽሙት ተግባር መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡

1) በአቶ በሪሁን ንግግርና በሚፈጽመው ተግባር መሀል ያለውን ልዩነት አስረዱ፡፡

2) የሀገር ወዳድ ዜጎች መገላጫ ባህሪያት ላይ ተወያዩ፡፡

ሀገር ወዳድ ዜጎች የሀገራቸውን ባህልና ታሪክ ይወዳሉ፡፡ ነገር ግን ስለ ሀገር ፍቅር ማውራት ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ፍቅራቸውን በተግባር ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ ሀገር ወዳዶች ለሀገራቸው የሚያስፈልገውን ነገር ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፡ ከላይ እንዳየነው ሀገር ወዳድነት የሀገሪቱን ህዝቦችና በውስጡ የሚኖር እያንዳንዱን አባል መውደድን ይጨምራል፡፡ ይህም የተገኙበትን ማህበረሰብ መውደድን ያካትታል፡፡ ሆኖም ይህ መውደድ ከሀገሩ ሌሎች አካባቢዎች የተገኙ ህዝቦችን የሚጨምር መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀገር ወዳድነት በተለያየ መንገድ ሊንጸባረቅ ይችላል፡፡ አንድ ሰው ቤተሰቡን በሚይዝበት መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡ በመሆኑም ከቤት ይጀምራል፡፡ ሀገር ወዳድ ዜጋ ልጆቹ ስለሀገራቸው እንዲያውቁና እንዲወዱ አድረጎ ያሳድጋል፡፡ ደስተኛ የሆነ የልጅነት ጊዜ ሰዎች ስለሀገራቸው ለሚኖራቸው ስሜት አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡

ሀገር ወዳድ ዜጎች ማህበረሰባቸውን በመንከባከብ ይታወቃሉ፡፡ ማህበረሰቡ ፅዱና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚችሉትን በሙሉ ያደርጋሉ፡፡ የጎረቤቶቻቸውን ልጆች በመልካም መንገድ ይንከባከባሉ፡፡ በትርፍ ሰዓታቸው አትክልቶችን ይተክላሉ፤ ውሃ ያጠጣሉ፡፡ የሌሎችን ዕምነትና ባህል ያከብራሉ፡፡ ሁሉም ሰው በቤቱ እንዳለ እንዲሰማው ያደርጋሉ፡፡

እውነተኛ ሀገር ወዳድ ዜጎች በሀገርና በመንግስት መካከል ያለውን ልዩነት ይገነዘባሉ፡፡ ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር የማይቀያየር ነው፡፡ ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር በተለያየ መንገድ ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴም ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር በመንግስት የሚፈጸሙ ተግባራትን በመቃወም ሊገልጹ ይችላሉ፡፡ አንድ ሰው መንግስትን በመቃወሙ ምክንያት ሀገር ወዳድ እንዳልሆነ ተደርጎ መታሰብ የለበትም፡፡ የሚከተለው ታሪክ ለዚህ እንደ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል፡-

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒር (1929-1968)

እስኪ የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኔርን (MLK Jr.) ታሪክ እንመልከት፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኔር በአሜሪካ የሚኖር ለሰብዓዊ መብት መከበር የቆመ መሪ ነበር፡፡ በህይወት ዘመኑ በአሜሪካ የነበረው ህግ ጥቁሮችን ለማግለል ጥቅም ላይ መዋሉን ታዝቧል፡፡ የሀገሪቱ ህጎች የጥቁሮችን ብዙ መብቶች ነፍገዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ለመጥቀስ ያህል፡- የመምረጥ መብት፣ በስራ ቦታ የጥቁሮች በእኩልነት አለመታየት እና እንደ መጓጓዣ አይነት አገልግሎቶች በእኩልነት አለማግኘት ናቸው፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኔር እነዚህን ህጎች የተቃወመ ሲሆን የጥቁሮችን መብት ለማስጠበቅ ሲል ታግሏል፡፡ እነዚህን ህጎች ለመታገል ጥቁሮችን አደራጅቷል፡፡ የእሱ ተከታዮች ሰላማዊ የሆኑ የተቃውሞ ስልቶችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ተከታዮቹ ኢ-ፍትሀዊ ከሆኑ ህጎች ጋር እንዳይተባበሩ አስተምሯል፡፡ ያደረገው ትግል በስተመጨረሻ ብዙ ጠቃሚ ለውጦች አምጥቷል፡፡ የአሜሪካ መንግስት የሚከተሉትን ህጎች እንዲያወጣ ማስገደድ ችሎ ነበር፡- 'የሲቪል መብት አዋጅ' (Civil Rights Act ) በ1964 እ.ኤ.አ እና 'የመምረጥ መብት አዋጅ' ( The Voting Rights Act) በ1965 እ.ኤ.አ የወጡ ህጎች ናቸው፡፡ በ1964 እ.ኤ.አ የወጣው 'የሲቪል መብት አዋጅ' በዘር፣ በቀለም፣ በሀይማኖት ወይም የመጣበትን ሀገር መሰረት አድርጎ በማንኛውም ሰው ላይ አድልዎ መፈጸም ህገ-ወጥ መሆኑን ደንግጓል፡፡ በ1965 እ.ኤ.አ የወጣው 'የመምረጥ መብት አዋጅ' የጥቁሮችን የመምረጥ መብት ማስጠበቅ ችሏል፡፡

## 5.5 ገርን መዉደድ

ተግባር 5.6

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳቸውን ካሰባችሁ በኋላ በቡድን ሆናችሁ በመልሶቹ ላይ ተወያዩ

1) ሀገርን መወደድ ማለት ምን ማለት ነው?

2) ሀገር መውደድ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

አንድ ኢትዮጲያዊ ሯጭ የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያሸንፍ ስታዩ ምን ይሰማችኋል? የሀገር ፍቅር ሁሉም የሀገሩ ዜጎች የሚጋሩት ስሜት ነው፡፡ ይሄ ስሜት በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጊዚያት ይታያል፡፡ ይህም ማለት ሀገር በስኬት ሰትጓዝ እርካታን በመከራ ጊዜ ችግሮቿን የመጋራት ስሜት ማለት ነው፡፡

የሀገር ፍቅር በሀገር ታሪክና በትውልድ ሀገራቸው ባህል ኩራት መሰማትን ያሳያል፡፡ ኢትዮጵያ በማንም ቅኝ ባለመገዛት ደማቅ የሆነ አኩሪ ታሪክ አላት፡፡ የተለያየ የባህልና የቋንቋ ብዝሃነት ያላቸው ህዝቦች በስምምነት የሚኖሩባት ሀገር ነች፡፡ በተጨማሪም የሰው ዘር መገኛ የሆነች ሀገር ነች፡፡

የሀገር ፍቅር ብዙ አስፈላጊ የሆኑ ጥቅሞች አሉት፡፡ የሀገር ፍቅር ህዝቦችን ወደ አንድነት ያመጣል፤ከሌሎች ጋር የአብሮነት ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ለሀገራቸው የሚኖራቸው ፍቅር በመካከላቸው ትስስር ይፈጥራል፡፡ ይህም የሆነው አንድ አይነት ስሜትና ግብ ስለሚኖራቸው ነው፡፡

በተጨማሪም የሀገር ፍቅር ጠንካራ ሀገር ለመፍጠር ያግዛል፡፡ ሀገር ወዳድ ህዝቦች ለአንድ አላማ ይሰባበሰባሉ፡፡ ሀገራቸውን የተሻለ ለማድረግ እያንዳንዳቸው ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡ በስራቸው ትጉ እና ጠንካራ ናቸው፡፡ በመሆኑም የነሱ ጥረት ሀገራቸውን ጠንካራ ያደርጋል፡፡

እውነተኛ ሀገር ወዳዶች ትውልድ ሀገራቸውን ያለቅድመ ሁኔታ ይወዳሉ፡፡ ለሀገራቸው የሚመኙት ነገር ቢኖር ሰላምና እድገት ብቻ ነው፡፡ ይህም እንዲሳካ ያላቸውን ነገር በሙሉ መሰዋት ለማድረግ ፈቃደኞች ናቸው፡፡ ሀገራቸውን ከወራሪዎች ለመጠበቅ ራሳቸውን ለመሰዋት ፈቃደኞች ናቸው፡፡

## 5.6 የምዕራፍ ማጠቃለያ

ሀገር ወዳድነት ማለት አንድ ሰው ለሀገሩ የሚኖረው ጥልቅ ፍቅር ነው፡፡ ለሀገር ጥቅም ሲባል ራስን ለመሰዋት ፍቃደኛ መሆን ነው፡፡ ሀገር ወዳድነት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ሰዎች በአስተሳሰባቸው፣ስሜታቸውን በሚያሳዩበት መንገድ ስለአገራቸው በሚናገሩት ሊገለጽ ይችላል፡፡ ሀገር ወዳዶች ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር በሙያቸው ጠንክረው በመስራት ያሳያሉ፡፡

ሀገር ወዳድነት የሀገርን አንድነት ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሀገር ወዳድነት ሀገር የሚኖራትን ዓለማቀፋዊ ፍላጎት ለማስጠበቅ ያስችላታል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች በሙያቸው ዙሪያ የሚያደርጉትን ጥረት እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፡፡

ሀገር ወዳዶች የሚጋሯቸው ተመሳሳይ የሆኑ ባህሪያት አሏቸው፡፡ በሀገራቸው ኩራት ይሰማቸዋል፡፡ በሀገራቸው ጉዳይ ጠንካራ የሆነ የባለቤትነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ለትውልድ ሀገራቸው ጥቅም ሲሉ ራሳቸውን ለመሰዋት ፍቃደኞች ናቸው፡፡ ሙስናን ለመዋጋት ዝግጁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለሀገራቸው ሲሉ ህይወታቸውን መሰዋዕት ላደረጉ ሰዎች ትልቅ አክብሮት አላቸው፡፡

ሀገር ወዳዶች ለሀገራቸው ታሪክ እና ባህል ጥልቅ ፍቅር አላቸው፡፡ ለአንድ አላማ በጋራ ይሰራሉ፡፡ ለሀገራቸው ሁልጊዜ ሰላምና ዕድገትን ይመኛሉ፣

### ቁልፍ ቃላት

**ጀግና፡-** በደፋር ድርጊቱ ወይም ልዩ በሆነ ብቃቱ አድናቆትን ያተረፈ ሰው

**ኩራት፡-** ለራስ ክብር የመስጠትና በሌሎች መከበር የመፈለግ ስሜት መያዝ

**መሰዋዕት፡-** የበለጠ አስፈላጊ የሆነን ነገር ለማሳካት ሲባል ሌላ አሰፈላጊ የሆነን ነገር ማጣት

**ፍላጎት፡** ሰዎች ቢኖራቸው፣ ቢማሩት ወይም ቢያደርጉት የሚያስደስታቸው ነገር

### መልመጃ 5.1

ትዕዛዝ አንድ፡ ከታች የተሰጡትን ዓረፍተ-ነገሮች በማንበብ ትክክለኛ የሆኑትን “እውነት” በማለት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡

1) ሀገር ወዳዶች እንደ ሀገር ሳይሆን የመጡበትን የብሄራቸውን የጋራ ጥቅም ትኩረት በመስጠት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

2) አንድ ሰው በሙያው ዙሪያ ጠንክሮ መስራቱ የአገር ወዳድነት ባህሪን የሚወክል ሊሆን ይችላል፡፡

3) ሙስናን በመዋጋት አንድ ሰው የሀገር ወዳድነት ተልእኮውን ማሳየት ይችላል፡፡

4) ሀገር ወዳድነት የሀገርን አንድነት ለማስቀጠል አሰፈላጊ አይደለም፡፡

1) ለማህበረሰቡ የተሻለ አካባቢን ለመፍጠር በማሰብ ዛፎችን መትከል አንደኛው የሀገር ወዳድነት ስሜትን ማሳያ ነው፡፡

ትዕዛዝ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት መካከል ሀገር መውደድን የማያሳየው ባህሪ የትኛው ነው?
   (ሀ) የሀገር ፍቅር
   (ለ) በሀገር ታሪክና ባህል መኩራት
   (ሐ) ጀግኖችን አለማክበር
2. ከሚከተሉት መካከል የሀገር ወዳድ ዜጎች መለያ ያልሆነው የትኛው ነው?
   (ሀ) ራሳቸውን ለሀገራቸው ለመሰዋት ፈቃደኞች ናቸው
   (ለ) ሙስናን ይቃወማሉ
   (ሐ) ለሀገራቸው ዜጎች ምንም ዓይነት ፍቅር የላቸውም
3. ሀገር ወዳድ ለመሆን አንድ ሰው ለሀገሩ ስላው ፍቅር ማውራት እንጂ ፍቅሩን በተግባር ማሳየት አይጠበቅበትም
   (ሀ) እውነት
   (ለ) ሀሰት
4. ከሚከተሉት መካከል ሀገር ወዳድ ዜጎች የማያሳዩት ባህሪ የትኛው ነው?
   (ሀ) በባህላቸው መኩራት
   (ለ) የሀሳብ ልዩነቶችን ማስተናገድ
   (ሐ) በሙስና መሳተፍ

ትዕዛዝ ሦስት፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1) የሀገር ወዳድነት ትርጉምን አብራሩ
2) የሀገር ወዳድ ዜጋ በሚወጣቸው ሀላፊነት ዙሪያ ተወያዩ፡፡
3) ሀገር ወዳድነት በሀላፊት ላይ ላሉ ግለሰቦች የሚሰጠውን ጥቅም አብራሩ
4) የሀገር ወዳድ ዜጎች ባህሪያትን ዘርዝሩ

# ምዕራፍ ስድስት

# ሰላምና መተባበር

የመማር ዉጤቶች፡ ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- የሰላምን ፅንሰ ሃሳብ ትገልጻላችሁ፡፡
- የሰላምን ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡
- ሰላማዊ ባህሪን ታደንቃላችሁ፡፡
- ሰላማዊ ባህሪን ታሳያላችሁ፡፡
- ስለ መተባበር ፅንሰ ሃሳብ ትወያያላችሁ፡፡
- የመተባበርን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ፡፡

## መግቢያ

በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ ሰላም እንዲሰፍን የማድረግ ሃላፊነት ያለበት ማን ነው? እርስ በርስ አብሮ በማይሰራ ማህበረሰብ ዉስጥ ሰላም ሊሰፍን ይችላል ? በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስለሰላምና ትብብር ጠቀሜታ ሃሳባቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሰላምን መስፋፋት ለማረጋገጥ የሚጫወተዉን ሚና ይገነዘባሉ፡፡



ስዕል 6.1፡ በዓለማቀፍ ደረጃ የታወቀ የሰላም ምልክት

ተግባር 6.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩባቸው

1) ሰላም ከሚለው ቃል ምን እንደተረዳችሁ ግለፁ

2) ተማሪዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ ሚና አላቸው መልሳችሁ አዎ ከሆነ ጥቂቶችን ግለፁ

3) በህብረተሰቡ ውስጥ ሰላም መጥፋት ምንያህል ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መገመት ትችላላችሁ

ከሰላም ፣ አለመረጋጋት ብጥብጥ አለመኖሩን መረዳት ይቻላል ፡፡ ሰላም የዕለት ተዕለት ተግባራትን ለማከናወንና ሰላማዊ ኑሮን በጣም ይጠቅማል አስፈላጊ የሰው ልጅ እንቅስቃሰዎች እንደ ትምህርት ፣ ቤተሰብ መምራትን ንግድ ስራ ያለ ሰላም ሊሳኩ አይችሉም

ተማሪዎች ስለሰላም ሊያዉቋቸው የሚገቡ ጠቃሚ ነገሮች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ሰላም የሰዎች ዉጤት ነው : ይህም ማለት ሰላምን ለማስጠበቅ ሁሉም ሰዉ የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል፡፡
- ሰላም ሂደት ነዉ: ሰላምን ማስጠበቅ የማያቋርጥ ሂደት ነዉ፡፡
- ሰላም የሰዉ ልጅ ባህሪና ዝንባሌ ነዉ ፡ የሰዉ ልጅ ለህይወቱ ሰላምና ደስታን ይፈልጋል፡፡

## 6.1.1 የሰላም ፅንሰ ሃሳብ

የተለያዩ የሰላም ደረጃዎች አሉ፡፡ እነሱም በግለሰብ ደረጃ፣ በማህበረሰብ ደረጃና በአለማቀፍ ደረጃ ተብለዉ ይከፈላሉ፡፡ የግል ሰላም ሊኖር የሚችለዉ ሰዎች ከጭንቀትና ፍርሃት ሲላቀቁ ነዉ፡፡ የግል ሰላም ያላቸዉ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ፍቅርና ሰላምን ይሰጣሉ፡፡ ሰላም ሊከበር የሚችለዉ ሃላፊነታቸዉን በሚወጡ ሰዎች ነዉ፡፡

ለምሳሌ የቤት ስራዉን በአግባቡ የሰራ ተማሪ ጠዋት ተነስቶ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ አይፈራም፡፡ ሰላም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ሰላም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሊፈጠር የሚችለዉ ሰዎች እርስበርስ ከመጣላት ይልቅ አብረዉ በጋራ መስራት ሲችሉ ነዉ፡፡ በማህበረሰቡ ዉስጥ ሰላም እንዲሰፍን እያንዳንዱ አባል ሃላፊነት እንዳለበት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰዎች አብረዉ እስከኖሩ ድረስ አንዳንድ ጊዜ አለመግባባቶች መፈጠራቸዉ አይቀሬ ነዉ፡፡ አለመግባባቶችን ለመፍታት፣ ሰዎች አንዳቸው ለአንዳቸዉ ልምድ፣ ትዕግስት፣ ደግነትና ይቅርባይነት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ሰዎች እንደነዚህ አይነት ባህሪያት ካላቸዉ ችግራቸዉን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡ የዓለም ሰላም የሚፈጠረዉ ሀገራት ከእርስ በርስ ጦርነት ሲታቀቡ ነዉ፡፡ ሁሉም ሃገራት የራሳቸዉ የሆነ ፍላጎትና ዓላማ አላቸዉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሃገራት በጋራ በመተባበር ከሰሩ በሃገሮች መካከል ሰላምና መረጋጋት ይኖራል፡፡ ሰላም በሁሉም የህብረተሰብ አካል ጥረት የሚፈጠር ነዉ፡፡ ስለዚህም ሁሉም ሰዉ የራሱን ሚና መጫወት እንዳለበት ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

በህብረተሰቡ ዉስጥ ሰላምን ለማረጋገጥ መጀመሪያ መታወቅ ያለበት ነገር የግለሰቦች ሰብዓዊ ክብር ነው፡፡ የሰዉ ልጆች ሁሉ ሊያሳኩት የሚፈልጉት ህልምና ዓላማዎች አሏቸዉ፡፡ ተማሪዎች ወደፊት ሀኪም፣ አዉሮፕላን አብራሪ፣ ወይም ነጋዴ እንደሚሆኑ ህልም ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡ በይበልጥ እኛ ደስተኛ እና በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የተከበርን እንድንሆን እንፈልጋለን፡ ፡ ይህ ፍላጎታችን በሌሎች እንዲከበርና ተቀባይነት እንዲያገኝ እኛም ሌሎች ሰዎች ከእኛ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎቶች እንዳሏቸዉ ማወቅ ይኖርብናል፡፡

## 6.1.2 የሰላም ጠቀሜታ

ሰላም ለተማሪዎች በርካታ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ ከሁከትና መገለል ነፃ የሆነ ህይወት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል፡፡ የትምህርት፣ የጤና እንክብካቤ እና የመጫወቻ ስፍራዎች አገልግሎት አቅርቦት ያለ ሰላም ሊሳካ አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት ሰላምን በሚያስጠብቁ እንቅስቃሴዎች ላይ የወጣቶች ተሳትፎ ጠቃሚ ነዉ፡፡ ሰላምን በሚያስጠብቁ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ ለተማሪዎች በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከነዚህም ዉስጥ ተማሪዎች የችግር አፈታት ዘዴ ክህሎታቸዉን ያዳብራሉ፣ በራስ የመተማመን ስሜታቸዉ ይጨምራል፣ እንዲሁም የተግባቦት ክህሎታቸዉን ይሻሻላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተሳትፏቸዉ በአካባቢያቸዉ የሚፈጠሩ ሁከትና ብጥብጦችን ይቀንሳል፤ ለትምህርታቸዉ እንቅፋት የሆነዉን ያለ አቻ ጋብቻ ተግባርን ይቀንሳል፤ ወላጆችና መምህራን የወጣቶችን ሃሳብ እንዲያከብሩም ይረዳል፤ በትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ላይ አካላዊ ቅጣት እንዳይኖርና ስለሰላም እና የህፃናት መብቶች ግንዛቤ እንዲፈጠር ያስችላል፤ ከዚህም ባሻገር ለወደፊት የጉልምስና እድሜያቸዉ ጥሩ ባህሪ እንዲኖራዉ ያደርጋል፡፡ በዚህም የሁሉንም ሰዎች መልካም ክብርና ዝና የሚያከብሩ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በአካባቢያቸዉ የሚፈፀሙ ሁከትና አድሎአዊ አሰራሮችን ለመዋጋት ድፍረቱና ችሎታዉ ይኖራቸዋል፡፡

## 6.1.3 ሰላማዊ ባህሪን ማሳየት

• ክብር መስጠት: እኛ የምንጠቀማቸዉ ቃላትና የምናደርጋቸዉ ተግባራት በሌሎች ሰዎች ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖራቸዉ ቀድሞ ግምት ዉስጥ የማስገባት ችሎታና ፈቃደኝነት ማለት ነዉ፡፡ ሰዉን የሚያከብሩ ሰዎች ስለሌሎች ሰዎች ስሜት ይጠነቀቃሉ፡፡ በተናደዱ ጊዜ ቢሆንም የትህትና መገለጫ የሆኑ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

ሰውን የሚያከብሩ ሰዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸዉ፡፡

— ሩህሩህ ናቸዉ፡፡

— ሁሌም ተራቸዉን ጠብቀዉ ይስተናገዳሉ፡፡

— "እባክህን/ሽ እና "አመሰግናለሁ" የሚሉ ቃላት ይጠቀማሉ፡፡

— በሌሎች ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ያደርጋሉ፡፡

ሰውን የሚያከብር ተማሪ ጓደኞቹን ለመጉዳት አይሞክርም፡፡ ምክንያቱም ስለ ሌሎች ሰዎች ስሜት ይጨነቃል፡፡ ክብር መስጠት ከሰዎች ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር ያስችለናል፡፡ እኛ ሰዎችን በአክብሮት ስንይዝ ሌሎችም እኛን እንደሚያከብሩን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እኛ ያላከበርናቸዉ ሰዎች እንዴት እኛን እንዲያከብሩን እንጠብቃለን?

- **ስምምነት**: በአንድ ህብረተሰብ ዉስጥ ስምምነት አለ ማለት የምንችለዉ ማህበረሰቡ በሰላም አብሮ መኖር ሲችል ነዉ፡፡ ተስማምቶ የሚኖር ህብረተሰብ እርስ በራሱ የሚረዳዳና የሚደጋገፍ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ሙዚቃን እንዉሰድ፣ በሙዚቃ "ክራር" ከ"ከበሮ" የተለየ ድምፅ አለዉ፤ "ከበሮም" እንዲሁ ከ "ዋሽንት" የተለየ ድምፅ አለዉ፡፡ እነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአንድ ላይ ሲሰሩ ለጆሮአችን ተስማሚ ሙዚቃ ይፈጥራሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በባህል እና በመሳሰሉት ልዩነት ያለዉ ማህበረሰብ በስምምነት ተዋህዶ አብሮ በመስራት ለህብረተሰቡ ልማትን ያፋጥናል፡፡
- **ትዕግስት**: ትዕግስት ማለት ችግር በሚገጥምበት ጊዜ የመረጋጋት ችሎታ ማለት ነው፡፡ ትዕግስተኛ ሰዎች የሚያደርጓቸዉ ተግባራት የሚያስከትሉትን ጥሩና መጥፎ ዉጤቶች አስቀድመው ያመዛዝናሉ፡፡ ይህ ማለት ስሜታዊ ሲሆኑ ጠቃሚ ዉሳኔዎችን ከመወሰን ይታቀባሉ፡፡ ትዕግስተኛነት ሰዎች ቆይተዉ የሚቆጩበትን ዉሳኔ እንዳይወስኑ ይረዳቸዋል፡፡ ይህም ሰዎች ያልተፈለገ ስሜትን ማለትም ንዴትና ጭንቀትን እንዲያስወግዱ ያግዛቸዋል፡፡ ትዕግስተኛነት ከሌሎች ሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረን ያስችለናል፡፡
  - **ማጋራት**: ይህ ማለት ነገሮችን ከሌሎች ሰዎች ጋር የመጠቀም ችሎታ ማለት ነው፡ ፡ ማጋራት ሰዎች የፍትሃዊነትን ዋጋ እንዲረዱ ያግዛል፡፡ ተማሪዎች ጓደኞችን እንዲያፈሩና በጓደኝነት አብረዉ እንዲቀጥሉ ያስችላል፡፡ እኛ ያለንን ለሌሎች ስናጋራ ሌሎችም ያላቸዉን እንደሚያጋሩን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ያላቸዉን ነገር ማጋራት በተግባር በልጅነታቸዉ ከተለማማዱት በጉልምስና ጊዜያቸዉ ለጋስና ሰዎችን የሚንከባከቡ ይሆናሉ፡፡
  - **ዉይይት** :ይህ ማለት ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለ የተግባቦት ችሎታ ማለት ነው፡፡ ዉይይት የሌሎችን ሰዉ ሃሳብ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ ዉይይት ተማሪዎችን ከወላጆቻቸዉና ቤተሰቦቻቸዉ ጋር የተሻለ ተግባቦት እንዲኖራቸዉ ይጠቅማል፡፡ ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች፣ ቋንቋዎችና ጎሳዎች ያሏት ትልቅ ሀገር ናት፡፡ ይህ ብዝሃነት ለዕዉቀት ትልቅ ምንጭ ነዉ፡፡ ነገር ግን ዕዉቀቱን ለማግኘትና ለመጠቀም ምክንያታዊ ተግባቦት ያስፈልጋል፡፡
- **ሁከት የለሽነት**: ሁላችንም የህብረተሰቡ አካላት ነን፡፡ በህብረተሰቡ ዉስጥ የሚፈጠሩ ነገሮች በህይወታችን ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ እንደ አንድ የህብረተሰብ አባል፣ በህብረተሰቡ ዉስጥ ስላምና ዕድገት ሲኖር ከሰላምና ዕድገቱ ተጠቃሚ እንሆናለን፤ በተመሳሳይ ግጭት ሲኖር የግጭቱ ሰለባ እንሆናለን፡፡ በህብረተሰቡ ዉስጥ የሚከሰቱ ማናቸዉም ጉዳዮች በህይወታችን ላይ ተፅዕኖ አስካላቸዉ ድረስ ሰላምንና ልማትን ማስጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነት ነዉ፡፡

## 6.2 ክፍለ-ትምህርት 2: መተባበር

ተግባር 6.2

1)ከሌሎች ሰዎች ጋር የመተባበር ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው

2) ስለመተባበር በክፍል ውስጥ በምሳሌ መለየት ትችላላቹ

መተባበር ሊኖር የሚችለዉ ሰዎች በጋራ ሲሰሩና እርስበርስ ለመረዳዳት ፈቃደኛ ሲሆኑ ነዉ፡፡ መተባበር አዲስ ሰዎችን እንድንተዋወቅና ጓደኝነትን እንድንመሰርት ይረዳናል፡፡ መተባበር ተማሪዎችን የሌሎችን ደስታና ሀዘን ተካፋይ እንዲሆኑ ያግዛል፡፡ ይህ ማለት ተማሪዎች እርስ በራሳቸዉ ይተዛዘናሉ ማለት ነዉ፡፡ መተባበር ለተማሪዎች የሚያስፈልገዉ ተራቸዉን ጠብቀዉ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ ከሌሎች ጋር አገልግሎቶችንና ጥቅሞችን እንዲጋሩ ነዉ፡፡ ተባባሪ ተማሪዎች ከወላጆቻቸዉ፣ መምህሮቻቸዉና ከጓደኞቻቸዉ ጋር ችግር አይገጥማቸዉም፡፡

መተባበር በተደጋጋሚ በሚደረግ ልምምድ የሚዳብር ክህሎት ነዉ፡፡ በየቀኑ የምናደርገዉ ልምምድ የነገ ስብዕናችን ይገነባልናል፡፡ ተማሪዎች ለወደፊት መምህር፣ መሃንዲስ፣ ሃኪም ወ.ዘ.ተ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ከባድ ሃላፊነት ያለባቸዉ ትልቅ ሙያዎች ናቸዉ፡፡ እነዚህን ሃላፊነቶች ለወደፊት በብቃት ለመወጣት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸዉና በዙሪያቸዉ ካሉ ሰዎች ጋር ጥሩ የስራ ግንኙነት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ ማንም ሰዉ በነዚህ ሁሉ ሙያዎች ብቻዉን ሰርቶ ዉጤታማ የሆነ የለም፡፡ ተማሪዎች በአሁን እድሜያቸዉ ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነትን የማዳበር ችሎታ ከሌላቸዉ ቀጣይ የህይወት ዘመናቸዉ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፡፡

### የመተባበር ፅንሰ-ሃሳብ

ምቹና ሰላማዊ በሆነ አካባቢ ለመኖር፣ ሰዎች እርስ በርሳቸዉ መተባባር አለባቸዉ፡፡ እዉነተኛ ትብብር መተማመንን ይፈልጋል፡፡ መተማመን ማለት በጓደኝነት ደረጃ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የእርስ በርስ መረዳዳት ማለት ነዉ፡፡ ለምሳሌ በጓደኛችሁ ታምናችሁ ሚስጥር ቢነገራችሁ፣ ያንን ሚስጥር የመጠበቅ ሃላፊነት አለባችሁ፡፡ ሚስጥሩን ለሌላ ሰዉ ከተናገራችሁ ለወደፊት ጓደኞቻችሁ አያምኗችሁም፡፡ መተማመን ለመተባበር በጣም አስፈላጊ ነገር ነዉ፡፡

### 6.2.1 የመተባበር ጠቀሜታ

የመተባበር ዋጋን መረዳት በህይወት ዉስጥ አንዱና በጣም አስፈላጊዉ ትምህርት ነዉ፡፡ በህይወታችን የምንፈፅመዉ ማንኛዉም ተግባር ዉጤታማ የሚሆነዉ ከሌሎች ጋር አብረን ስንሰራ ነዉ፡፡ መተባበር ከሌሎች ጋር እንዴት አብረን እንደምንሰራና ሰዎችን እንደምናከብር ያስተምረናል፡፡

የመተባበር ጠቀሜታዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ሌሎችን እንዴት ማዳመጥ እንዳለብን ያስተምራል**: ማዳመጥ ሃሳብን እንድንገነዘብ ይረዳናል፤ የሌሎችን ሰዎች ሃሳብ እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ እንዲሁም እዉቀት እንድናገኝ ያስችለናል፡፡

- **በሰዎች ፊት እንዴት ንግግር ማድረግ እንደምንችል ያስተምራል**: በቡድን ዉስጥ የኛ ተሳትፎ ጠቃሚነት እንዳለዉ ማወቅ አስፈላጊ ነዉ፡፡ መተባበር ከሌሎች ጋር ያለንን የተግባቦት ክህሎት እንድናዳብር ይረዳናል፡፡ ተማሪዎች ከሌሎች ጋር ንግግር ሲያደርጉ ግልፅና አክብሮት በተሞላው መልኩ መሆን አለበት፡፡

- **በራስ መተማመንን ያዳብራል**: ሃሳባችሁን ጓደኞችሁ ሲያደንቅላችሁ እንዴት እንደሚሰማችሁ አስቡ፣ የቡድን ተግባቦት የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ብቃትን ያዳብራል፡፡

- **በጥልቀት እንዴት ማሰብ እንደምንችል ያስተምራል**: መተባበር ችግሮችን ለመፍታት ይጠቅማል፡፡ ነገር ግን ችግሩ ከመፈታቱ በፊት ወደ መፍትሄ ለመምጣት ተማሪዎች በጥልቀት ማሰብ አለባቸዉ፡፡

### የመተባበር ዕሴቶች

አብሮነት: በቡድን ዉስጥ የጋራ ዓላማና ፍልጎትን መሰረት ያደረገ የአንድነት ስሜት ማለት ነዉ፡፡ ይህ አንድነት መከባበርን፣ እኩልነትንና ብዝሃነትን በማክብር ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ አብሮነት እርስ በርስ የመረዳዳት ፈቃደኝነት ፣ ከአደጋ እርስ በእርስ በመጠባበቅ፣ የሌሎችን ሰዎች ስሜት በመጋራት ወ.ዘ.ተ ይገለፃል፡፡

ግልፅነት፡ ግልፅነት በብዙ ነገር ልንረዳዉ እንችላለን፡፡ ሃሳብና አስተያየታችን በታማኝነት መግለፅ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር ስሜትን የመደበቅ ወይም የመዋሸት ተቃራኒ ማለት ነዉ፡፡

> ግልፅነት አዲ ሃሳቦችን ለማዳመጥና ለመቀበል ዝግጁ መሆን ማለት እንደሆነም መረዳት እንችላለን ይሁን እንጂ ሁሉንም ሃሳብ እውነተኛ አድረጎ መቀበል ማለት አይደለ ፡፡ ነገር ግን ሁሌም አዲስ ነገር እንደምንማር ማስታወስ አለብን፡፡ ሰዎች ስለ አንድ ነገር ከተወያዩ በኃላ የራሳቸውን አስተያየት ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል ፡፡ ተማሪዎች ስለ አንድ ጉዳይ ያሉን እውነታዎች ሳያውቁ አስተያየት ማቅረብ የለባቸውም

ሌሎችን መንከባከብ: ሌሎችን መንከባከብ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ባህሪያችን የምንሰራዉ ስራ ዉጤት ነዉ፡፡ ሌሎችን መንከባከብ የደግነትና ፍቅር ተግባር ነዉ፡፡ ብዙ ደግነትና ፍቅር ለሰዎች ባሳየን ቁጥር እነዚህ ጥሩ ተግባራት ባህሪያችን ይሆናሉ፡፡ ደግ ነገሮችን ስናደርግ ደግ ሰዎች እንሆናለን፡፡ ስለዚህ ሌሎችን መንከባከብ እነሱን ብቻ ሳይሆን እኛንም ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም ለሌሎች ሰዎች እንክብካቤና ትኩረት ከሰጠን እነሱም ተመሳሳይ ፍቅርና እንክብካቤ ያሳያሉ፡፡ ይህ ማለት ከሰዎች ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ይረዳል፡፡ ለሌሎች ሰዎች እንክብካቤ ማድረግ የተሻለ ሰዉ ያደርገናል፡፡

## 6.3 የሰላምና መተባበር ግንኙነት

ተግባር 6.3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሶቻቸውን አስቡና አራት በመሆን ተወያዩባቸው ፡፡

1) የሰላምና መተባበር ግንኙነት ምንድን ነው ?

2) ተማሪዎችን ትብብር የሚጠይቁ ተግባራትን በምሳሌ መጥቀስ ትችላላችሁ ?

3) ሰላም ለህገራቹ ያለውን ጥቂት ጠቀሜታዎች ግለፁ ?

በታሪኩ የሰዉ ልጅ በርካታ ግጭቶችንና ጦርነቶችን አድርጓል፤ እነዚህ ግጭቶች መንግስታትን ጥለዋል፤ ሰፊ ግዛቶችን አስቁመዋል፤ እንዲሁም የሃገራትን ካርታ ቀይረዋል፡፡ ነገር ግን ግጭቶችና ጦርነቶች ሊታሰብ ወደ ማይችል ደረጃ ሰዎችን ለሞትና ስቃይ ዳርገዋል፡፡ እነዚህ ግጭቶች  በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን ህይወት፣ ክብርና ደህንነት አዉድመዋል፡፡ በማህበረሰቡ ዉስጥ የሚነሱ ማንኛውንም አለመግባባቶች ጨርሶ ማጥፋት ባይቻልም ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታትና ቀጣይ ግጭትና ጦርነት እንዳያስከትሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ምንም አንኳ እነዚህ ግጭቶች አስከፊ ቢሆኑም በታሪክ ለሰዉ ልጅ አንድ እዉነተኛ ነገርን ያስታዉሳሉ፤ እዉነተኛ ነገሩም ሰላም ለጥሩ ህይወት ያለዉን ጠቀሜታ ነዉ፡፡ ቀጣዩ ጥያቄ በህብረተሰቡ ዉስጥ ሰላምን እንዴት እናመጣለን የሚል ነዉ፡፡ ሰላምና መተባበር የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ ሰላምን በህብረተሰቡ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ወሳኝ ሚና መጫወት አለበት፡፡ ሰላም በጥቂት ሰዎች ርብርብ ብቻ አይረጋገጥም፤ ሊረጋገጥ የሚችለዉ ሁሉም ሰዉ ሃላፊነቱን በአግባቡ ሲወጣ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም እንደምታዉቁት ፖሊስ፣ ዳኞች፣ እና ወታደሮች ሰላምን በማህበረሰቡ ለማስጠበቅ በጣም ከባድ ሃላፊነት አለባቸዉ፡፡ ይሁን እንጅ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ሰላምን ለማስጠበቅ ትልቅ ሚና መጫወት እንዳለበትም ማወቅ ይገባል፡፡

## 6.4 የምዕራፍ ማጠቃለያ

ሰላም ጥሩ ህይወት ለመኖር ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡ ያለ ሰላም ምንም ነገር ሊፈፀም አይችልም፡፡ ሌላዉ መታወቅ ያለበት ጠቃሚ ነገር ሰላም የሰዉ ልጅ የተፈጥሮ አካል መሆኑ ነዉ፡፡ የሰዉ ልጅ ብዙ ጥሩ ባህሪያትን ለምሳሌ ለሌሎች አዛኝነትን፣ ፍቅርን፣ ትብብርንና ወ.ዘ.ተ ይዞ ይወለዳል፡፡ መተባበር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ እነዚህ ጠቀሜታዎችም በትምህርት ቤት፣ በቤተሰብ፣ እና በማህበረሰብ ደረጃ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መተባበር ለተማሪዎች የእርስበርስ ግንኙነታቸዉን ያጠናክርላቸዋል፤ ችግሮችንም ለመፍታት ያስችላቸዋል፤ እንዲሁም ከታላላቆች ዕዉቅና እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

ቁልፍ ቃላት

- እምነት: ስለአንድ ሰዉ ተጨባጭነት፣ታማኝነትና ጥሩነት ያለን ግንዛቤ
- ግልፅነት: ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን፤ በርካታ ዕዉቀቶችንና አስተያቶችን ለማወቅ ፈቃደኛ መሆን፡፡
- ዝንባሌ: የተለየ አመለካከት ወይም ፍላጎት
- ዉይይት: ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች የሚደረግ ንግግር

## መልመጃ 6.1

ትዕዛዝ አንድ ፡ የሚከተሉትን ዓረፍተ-ነገሮች በማንበብ ትክክል ከሆኑ "እዉነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

1) ሰላምና መተባበር በሰዉ ልጆች የእለት ከእለት እንቅስቃሴዎች ላይ ጠቀሜታዉ የጎላ አይደለም፡፡

2) አንዱ የመተባበር ጠቀሜታ ችግርን በጋራ ለመፍታት መማር መቻል ነዉ፡፡

3) ዉይይት ማለት ችግር በሚገጥምበት ጊዜ የመረጋጋት ችሎታ ማለት ነው፡፡

4) የትምህርት ፣ የጤና እንክብካቤና መጫወቻ አካባቢ ሰላም ቢኖርም ባይኖርም አገልግሎቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡

5) ሰላም የሰዉ ልጅ ዝንባሌ ሲሆን ምቹ በሆነ ጊዜ ብቻ የሚፈልገዉ ጉዳይ ነዉ፡፡.

ትዕዛዝ ሁለት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1) ከሚከተሉት ዉስጥ ስለሰላም ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

(ሀ) ሰላምን የማስጠበቅ ሂደት መቋጫ የለዉም

(ለ) ሰላም ሊረጋገጥ የሚችለዉ በመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ነዉ

(ሐ) ሁሉም የሰዉ ልጆች ሰላም ለህይወታቸዉ ያስፈልጋቸዋል

2) ሰላም ለሰው ልጆች ከሚሰጠው ጥቅም ውስጥ ያልሆነው የትኛው ነው?

(ሀ) ከሁከት ነፃ መሆን

(ለ) ሌሎችን የመጨቆን ነፃነት

(ሐ) ሁሉም መልስ ናቸዉ

3) ከሚከተሉት ዉስጥ ለሰላማዊ ባህሪ ምሳሌ የማይሆነዉ የቱ ነዉ?

(ሀ) አብሮነት

(ለ) ትዕግስት

(ሐ) ዉይይት

(መ) መልሱ አልተሰጠም

4) ከሚከተሉት ዉስጥ የመተባበር ጠቃሚ ዕሴት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

(ሀ) አንድነት

(ለ) ግልፅነት

(ሐ) ሌሎችን መርዳት

(መ) መልሱ አልተሰጠም

ትዕዛዝ ሦስት: ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችን አስቡና ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።

1) መተማመን ለመተባበር ያለዉን ጠቀሜታ ተወያዩ።

2) በትምህርት ቤት ሊታዩ የሚችሉ የሰላማዊ ባህሪያት ምሳሌዎች ዘርዝሩ።

3) ስለመተባበር ጠቀሜታ ተወያዩ።